# በሀረማያና በአዴሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና


አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋክሊቲ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል


የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በ


መሠረት ጣፋ


መጋቢት 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋክሊቲ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በሀረማያና በአዴሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና

በ

መሠረት ጣፋ

መጋቢት 2003 ዓ.ም

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## የቋንቋዎች ጥናት ፋክሊቲ
## የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በሀረማያና በአዴሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና

በ

መሠረት ጣፋ

መጋቢት 2003 ዓ.ም

<u>የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ</u>

<u>ቶለማሪያም ፋፋ (ዶ/ር)</u> ____________

አማካሪ ፊርማ

<u>ጌታሁን አማረ (ዶ/ር)</u> ____________

ፈታኝ ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ADDIS ABABA UNIVERSITY ቋ.ጥ.ተ. ቤተ መጻሕፍት ILS LIBRARY

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሞ ምህረቱ በዝቶልኝ በሰላም ትምህርቴን እንዳጠናቀቅ ለረዳኝ ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይድረሰው።

በመቀጠል ይህ ጥናት ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ስለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ ከርዕስ ማስተካከል ጀምሮ ያላሰለሰ የሙያ ድጋፍና ምክራቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ዶ/ር ቶለ ማሪያም ፉፋ ልባዊ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ከሁሉም በላይ ሀላፊነቱን በሙሉ ተሸክሞ እኔንም ሆነ ልጆቼን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ለዚህ ደረጃ ማብቃቱ ሳያንስ በፅሁፉ ውስጥ የሚገኘውን የሂሳብ ስራ በመስራት ድጋፉ ያልተለየኝ ባለቤቴ ወርቅአለማሁ ማናዬ በኔ የከፍተኛ ትምህርት ህይወት ውስጥ ትልቁን ስፍራ ይይዛል። ስለዚህ ማመስገኑ ቀረቤታዬን የሚቀንስብኝ ስለመሰለኝ ዝምታን መርጫለሁ።

እንዲሁም የእናት ፍቅር በሚያስፈልጋቸው ወቅት የተለየኊቸው ልጆቼ ካሌብ እና ኢዮአብ ይጎድልብናል ይቸግረናል ሳይሉ እንድማር ስላደረጉኝ ባለውለታዎቼ ናቸውና ምስጋና ይገባቸዋል።

በሞራል፣ በገንዘብ፣ በጉልበታቸው እንዲሁም ውድ ጊዜያቸውን ሰጥተው ከጎኔ ሳይለዩኝ ለረዱኝ ቤተሰቦቼ ለአባቴ ለአቶ ጣፋ ኦባ ለእናቴ ለወ/ሮ ወርቅነሽ አለሙ ለእህቴ ለሲስተር ሮማን ጣፋ ለወንድሞቼ በላይና ዮሴፍ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው።

በተጨማሪም ለአቶ ዘሪሁን መንገሻ ለአክስቴ ወ/ሮ አበራሽ አለሙ ለጓደኛዬ ለተዋበች ተክሌ በሞራልና አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ሁሉ ድጋፋቸው ስላልተለየኝ ሳላመሰግናቸው አላልፍም።

በመጨረሻም ጥናታዊ ፅሁፌን በኮምፒውተር በማስተካከልና በመፃፍ የረዳችኝ ወ/ሪት ዙሪያሽወርቅ ሙሉጌታ አክብሮትና ምስጋናዬ ይድረሳት።

# ማውጫ


ርዕስ ገጽ

ምስጋና ..... i
ማውጫ ..... ii
የሠንጠረዥ ማውጫ ..... V
አጠቃሎ ..... vi

## ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ ..... 1
1.2. የጥናቱ ዓላማ ..... 3
1.3. የጥናቱ ጠቀሜታዎች ..... 4
1.4. የጥናቱ ወሰን ..... 4
1.5 የጥናቱ አወቃቀር ..... 5
1.6. የቃላትና የሀረጋት ትርጓሜ ..... 5

ምዕራፍ ሁለት

2. ክለሳ ድርሳን /Review of Related Literature/ ..... 7
2.1. የስህተት ምንነት ..... 7
2.2. የስህተት ትንተና ታሪካዊ ዳራ ..... 10
2.3. የስህተት ምንጮች ..... 12
2.3.1. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ..... 14
2.3.2. የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ..... 17
2.3.3. የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶችና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት ..... 19
2.3.4. ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ..... 21
2.4. የስህተት ትንተና ዘዴዎች ..... 23
2.4.1. የስነ ልሳን ክፍሎችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል ..... 23
2.4.2. የዓረፍተ ነገር ቅርፆችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል ..... 24

2.4.3. ንፅፅራዊ ክፍፍል 25

2.4.4. ተግባቦታዊ ተፅዕኖ መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል 25

2.5. የስህተት ትንተና ጠቀሜታ 27

2.6. በሀገራችን በስህተት ትንተና ዙሪያ የተሠሩ ስራዎች 29

ምዕራፍ ሶስት

የአጠናን ዘዴ 34

3.1. የትምህርት ቤቶች አመራረጥ 34

3.2. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ 34

3.3. የመምህራን ናሙና አመራርጥ 35

3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች 35

3.4.1. መጠይቅ 35

3.4.1.1. የተማሪዎች መጠይቅ 35

3.4.1.2. የመምህራን መጠይቅ 36

3.1.2. ድርሰቶች 36

3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ 37

3.5.1. የድርሰት መልመጃዎች አተናተን 37

3.5.2. የመጠይቆች አተናተን 38

ምዕራፍ አራት

የመረጃ ትንተናና ውጤት 39

4.1. መግቢያ 39

4.2. በድርሰቶቹ ውስጥ የታዩ ዋና ዋና የስህተት አይነቶች 41

4.2.1. የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች 44

4.2.1.1. የቃላት አመራረጥ ስህተቶች 46

4.2.1.2. ተደጋጋሚነት (ድግግሞሽ) 51

4.2.1.3. ግድፈት 52

4.2.1.4. ጭመራ 53

4.2.1.5. ኢ-መደበኛ ቃላትና ሀረጋት 54

4.2.2. የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች 55

4.2.2.1. የዐረፍተ ነገር ስምምነት ........ 57
4.2.2.2. የመስተአምር እና የተሳቢ አገባብ ........ 60
4.2.2.3. የአጣማሪዎች አገባብ ስህተቶች ........ 62
4.2.2.4. የመስተዋድድ አገባብ ስህተቶች ........ 63

4.2.3. የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ........ 64
4.2.3.1. የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ........ 67
4.2.3.2. የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ስህተቶች ........ 68
4.2.4. የፅንስ ሃሳብ ግንዛቤ ስህተቶች ........ 70
4.3. የስህተት ምንጭ መላ ምቶች ........ 70
4.3.1. የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ........ 71
4.3.2. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ........ 74
4.3.3. የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶችና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት ........ 76
4.3.4. ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ........ 85
ምዕራፍ አምስት
ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳብ ........ 87
1.1. ማጠቃለያ ........ 87
1.2. የመፍትሄ ሃሣብ ........ 90
ዋቢ መፃህፍት ........ 92
አባሪዎች
አባሪ ሀ የድርሰት አፃፃፍ መመሪያ ክፍል አንድ ........ 99
አባሪ ለ የተማሪዎች መጠይቅ ........ 100
አባሪ ሐ የመምህራን መጠይቅ ........ 107
አባሪ መ በተማሪዎቹ የተፃፉ ናሙና ድርሰቶች ........ 117

# የሠንጠረዥ ማውጫ


ገጽ

ሠንጠረዥ 1 ድርሰቶቹ የተፃፉባቸው የቃላት ብዛት የስህተት ብዛት መቶኛ፣ አማካይ ስህተትና የስህተት ድግግሞሽ ........ 40

ሠንጠረዥ 2 በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ በዋና የስህተት አይነት ምድቦች ውስጥ የተፈፀሙት ስህተቶች ብዛት መቶኛ አማካይ ስህተት እና አማካይ የስህተት ድግግሞሽ ........ 42

ሠንጠረዥ 3 የቋንቋ አጠቃቀም ንዑስ የስህተት አይነቶች ........ 45

ሠንጠረዥ 4 ከቋንቃ አወቃቀር ጋር በተያያዘ በድርሰቶቹ ውስጥ በዋነኛነት የተፈፀሙ የስህተት አይነቶች ........ 56

ሠንጠረዥ 5 ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ጉድለት የተነሳ የተፈፀሙ ስህተቶች ........ 66

ሠንጠርዥ 6 የክፍልና የቤት ስራ ልምምድን በሚመለከት ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ........ 78

ሠንጠረዥ 7 የፅህፈት ልምምድ አስመልክቶ ከተማሪዎቹ የተገኙ የመጠይቅ ምላሾች አማራጭ ........ 80

በሠንጠረዥ 8 በጽህፈት ልምምዱ ጊዜ የመምህራኑ የትምህርት አቀራረብ በተመለከተ ለመምህራኑ የቀረበ መጠይቅ ምላሽ ........ 81

ሠንጠረዥ 9 ፅህፈትን ለማለማመድ መምህራኑ የሚጠቀሙባቸውን ማቴሪያሎች በተመለከተ የመምህራን መጠይቅ ምላሾች ........ 84

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የተደረገው በሀረማያና በአዴሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸው በፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ላይ ነው፡፡ ጥናቱ ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ ተብሎ የተዘጋጀ ነው፡፡ እነሱም በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ የሚከሰቱት ስህተቶች ምን ምን ናቸው? የድግግሞሽ መጠናቸውስ ምን ያህል ነው? የሚለው የመጀመሪያው ሲሆን ለስህተቶቹ ምንጭ ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱት እነማን ናቸው? የሚለው ጥያቄ ደግሞ ሁለተኛው ነው፡፡

ለጥናቱ አላማ በናሙናነት የተመረጡት ሁለት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ በነዚህ ትምህርት ቤቶች በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ ከሚማሩ 550 የኦሮሞኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎች መካከል 275 ተማሪዎችን በጥናቱ አሳትፏል፡፡ አስፈላጊው መረጃም በድርሰትና በመጠይቅ አማካይነት ተሰብስቧል፡፡

ለጥናቱም የሚያስፈልጉት መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ በስህተት ትንተና የአተናተን ዘዴ መሰረት ስህተቶቹ በአይነት ተለይተውና ተቆጥረው ተተንትነዋል፡፡ በተገኘው ውጤት መሰረትም በአጠቃላይ ድርሰቶቹ የተፈፀመው የስህተት መጠን 18087 ሲሆን አማካይ ድግግሞሹም 57.67% ሆኗል፡፡ በዚህ የስህተት መጠንና አማካይ የስህተት ድግግሞሽ አራት ዋና ዋና የስህተት አይነቶች የተፈፀሙ ሲሆን እነዚህም የቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ብዛት 42.86% አማካይ ድግግሞሹ 24.72% ፣ የቋንቋ አወቃቀር ስህተት 20.93 በመቶ አማካይ ድግግሞሹ 12.07%፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት 20.78 በመቶ አማካይ ድግግሞሽ 11.98% እና የፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተት 15.42 በመቶ አማካይ የስህተት ድግግሞሽ 8.89% ሊሆኑ እንደቻሉ ጥናቱ አመልክቷል፡፡ ለእነዚህ ሁሉ ስህተቶች ምንጭ ይሆናሉ ተብለው የታመኑት ውስጠ ቋንቋ ተፅእኖ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የመማር ማስተማር ሂደትና የስነ-ልቦናዊ ተፅዕኖ፣ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በመጨረሻም ማጠቃለያና የተከሰቱትን ስህተቶች ለመቅረፍ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የመፍትሔ ሀሳቦች ቀርበው ጥናቱ ተጠናቋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ስድስት ንዑስ ክፍሎች አሉት፤ እነሱም፡- የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታዎች፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ አወቃቀርና የቃላትና የሐረጋት ትርጓሜ ናቸው፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ከአራቱ የቋንቋ መሰረታዊ ክሂሎች መሀከል አንዱ የጽህፈት ክሂል ነው፡፡ የመጀመሪያ ቋንቋ ተናጋሪዎችም ሆኑ የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በመደበኛው ትምህርት ቤት ውስጥ ይማሩታል፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ወቅት ጽህፈትን ተጠቅሞ ሀሳብን ለመግለጽ የቋንቋውን ሰዋስውና ማህበራዊ የቋንቋ አጠቃቀም ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ጽህፈት እንደማዳመጥና መናገር ክሂሎች ለቋንቋ ተጋላጭ በመሆን ብቻ የሚገኝ ሳይሆን አፈ ፈትም ሆኑ ኢአፈ ፈት ተናጋሪዎች በሚያደርጉት ተደጋጋሚ ልምምድና ትምህርት የሚዳብር ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የጽህፈት ክሂልን የሚማሩ ተማሪዎች በርካታ ስህተቶችን ይፈጽማሉ፡፡ በተጨማሪም አንድ ሰው በጽህፈት አማካኝነት ለመግባባት ሲያስብና የሚፈልገውን መልእክት ለተቀባዩ ለማስተላለፍ ሲፈልግ እንደመናገርና ማዳመጥ ክሂሎች አጋዥ ስሜታዊና አካላዊ መግለጫዎችን ለምሳሌ የፊት ገጽታ፣ ፈገግታ፣ ቁጣ፣ ሀዘን፣ የድምጽ ጫና፣ድግግሞሽ የመሳሰሉትን ነገሮች መጠቀም አይችልም ደብሬ (1990)፡፡ ከዚህም የተነሳ ፀሐፊው የሚያስተላልፈው መልእክት ለተቀባዩ ግልጽ እንዲሆንለትና የሚያሻሙ ነገሮችን ለማስቀረት ተማሪዎቹ ጽህፈት ከመጻፋቸው በፊት በጥንቃቄ የተሞላ ዝግጅትና በቂ ልምምድ እንደሚያስፈልጋቸው ይታመናል Norrish (1992)፡፡

ይሁን እንጂ ጽህፈት ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ቢታዩበትም የሰው ልጅ ሐሳቡን ለሌሎች ቀርጾ ለማቆየትና ለማስተላለፍ ይችል ዘንድ የጽህፈት ክሂል ትምህርት እንደሚያስፈልገው ይታመናል፡፡ በጽህፈት አማካይነት የሚደረግ የቋንቋ ግንኙነትም በዋነኛነት የትምህርት ውጤት በመሆኑ ከፊደል አጣጣል ጀምሮ የቃልን፣ የሀረግን፣ የአረፍተ ነገርን፣ የአንቀጽንና የድርሰትን አወቃቀር በየደረጃው መማር ክሂሉን

ጠንቅቆ ለመረዳት አስፈላጊ ነው። የጽሁፍ ክሂል የቋንቋ ትምህርቶች አብይ ትኩረት የሆነውም በዚህ ምክንያት ነው።

የአማርኛ ቋንቋም ስርአተ ትምህርት ተነድፎለት ከወጣበት ከ1944 ዓ.ም ጀምሮ የአማርኛ የድርሰት ትምህርት ሲሰጥ የቆየ ለመሆኑ በትምህርት ሚኒስቴር (1970) የአማርኛ ቋንቋ ስርአተ ትምህርት ከዘጠነኛ እስከ አስረኛ ክፍል በአማርኛ ዋና ቡድን ከተዘጋጁ ጽሁፎች መረዳት ይቻላል። ይሁን እንጂ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ አቀናብረው መልእክት ለማስተላለፍ የተለያዩ ችግሮች ያለባቸው መሆኑ በስፋት ይነገራል። ይህንኑ የጽህፈት ችግር በማስመልከትም ባዬ (1987) ቀደም ሲል ይሰጥ የነበረው የቋንቋ ትምህርት በሰዋስው ላይ ያተኮረ እንደነበረና በአሁን ጊዜ ደግሞ በክሂል ዘርፎች ላይ እንዳተኮረ ገልጸው ሆኖም ግን የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ጽህፈት ሰሚታይበት ጊዜ እንኳንስ ትምህርታቸውን ያልጨረሱት ቀርቶ አስራ ሁለተኛን ያጠናቀቁትም ቢሆኑ ሌላው ቢቀር የማመልከቻ ደብዳቤ መፃፍ እማይችሉበት ደረጃ እንደደረሱና በጥቅሉም ተማሪዎች ከቋንቋው ስርኣትም ሆነ ከክሂሉ እንደሌሉበት ገልጸዋል።

ይልማ (1956: 3-5) ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን በፈቱ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ጽሕፈት ላይ በሚታዩ ስህተቶች ጥናት ባደረጉበት ጊዜ ተማሪዎቹ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች የሳልስና የሳድስ የግዕዝና የሃምስን ቦታ ማለዋወጥ፣ የመስተዋድዶችንና የተሳቢ ምልክቶችን አገባባቸውን አለማወቅ፣ የባለቤትና ግሶች አለመስማማት ስህተቶች እንደሆኑና የስህተቶቹ ምንጮችም ያፍ መፍቻ ቋንቋ እንደሆነ ገልፀዋል።

ሰለሞን (1987) በተማሪዎች ብዛት የተነሳ በተማሪዎች የድርሰት መልመጃ ላይ የሚከሰቱ ስህተቶች ባፋጣኝ ከመምህራኑ ምላሽ ባለማግኘታቸው የተማሪዎቹ የጽህፈት ችግር በየጊዜው እየታየ መሄዱን ጠቅሰው ይሄንኑ ችግር ለማቃለል የቢጤ እርማት ስልትን በተጠኝነት በተመረጡ የናሙና ተማሪዎች ላይ ሙከራ አድርገዋል።

Johansson (1975) እና Norrish (1992) የስህተት ትንተናን አላማ መሰረት ያደረጉ በርካታ ጥናቶች መካሄዳቸውን በጥናቶቹ ከተደረሰባቸው ውጤቶች በመነሳትም በቋንቋ ትምህርት መስክ አስተዋጽኦ ያደረጉ አዳዲስ ሀሳቦችን ለመከተል

ማስቻሉን ይገልጻሉ። በዚህም መሰረት ቀደም ሲል የቀረቡትንና መሰል ንድፈ ሐሳባዊ መሰረቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ጥናት አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የሐረማያና የአደሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ በሚፈጽሟቸው ዋና የስህተት ምንጮች ላይ ያተኩራል።

የሐረማያና የአደሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች እስከ ስምንተኛ ክፍል ትምህርታቸውን የተከታተሉት አፍ በፈቱበት ኦሮምኛ ቋንቋ ነው። የአማርኛ ቋንቋንም በመደበኛ ትምህርትነት መማር የሚጀምሩት ከአምስተኛ ክፍል ስለሆነና አብዛኞቹ የወረዳው ተማሪዎች ደግሞ የአማርኛ ቋንቋን በትምህርት ቤት ውስጥ ከሚማሩትና ከሚናገሩት ሌላ በእለት ተእለት ህይወታቸው ውስጥ የሚያጋጥማቸው ቋንቋ ባለመሆኑ ድርሰት ሲጽፉም ሆነ ሲናገሩ የተለያዩ ስህተቶች ሲፈጽሙ ይታያል። ጥናቱ በሚካሄድበት በሀረማያ እና አዴሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉትን ተማሪዎች በመምህርነት በማገለግልበት ወቅት ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ለመፃፍ ሲሞክሩም ሆነ ሲናገሩ ያስተዋልኳቸው ተጨባጭ ችግሮች ለጥናቱ መነሻ ሆነውኛል። ለምሳሌ ተገቢ ያልሆነ የፊደላት አፃፃፍ፣ የቃላትና የሀሳብ አላስፈላጊ ድግግሞሽ፣ የጾታ አለመስማማት፣ የባለቤት እና የግስ አለመስማማት፣ የቃላት አለቦታቸው መግባት፣ የስርኣተ ነጥብ አጠቃቀም ችግር፣ የቁጥር አለመስማማት የአረፍተ ነገርን ትክክለኛ አሰካክ ጠብቆ አለመፃፍና የሀሳብን ፍሰት አለመጠበቅ ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው።

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አቢይ አላማ በሀረማያ እና በአዴሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች በስህተት ትንተና ዘዴዎች አጥንቶ ዋናዋና የስህተት አይነቶችን መለየት እና ለስህተቶቹ መፈፀም ምክንያት የሆኑ ምንጮችን መጠቆምና ማብራራት ነው። ጥናቱ ከዚህ አጠቃላይ አላማ በመነሳት የሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል።

ሀ. ተማሪዎቹ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸው፡-

- ዋና ዋና የስህተት አይነቶች ምንምን ናቸው?

- የስህተቶቹ መጠን ወይም አይነት ምን ያህል ነው?
- ድግግሞሻቸውስ?

ለ. ለነዚህ ስህተቶች መከሰት የስህተት ምንጮች ይሆናሉ የተባሉት ነገሮች ምንምን ናቸው?

ሐ. ተማሪዎቹ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅሟቸውን የስህተት አይነቶች ለመቆጣጠር የሚረዱ የመፍትሄ ሀሳቦች ምንድን ናቸው?

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታዎች

የተማሪዎችን የፅሁፍ ስህተቶች ማጥናት ተማሪዎቹ ትምህርት የሚቀስሙበትን ብልሀት መገንዘብ እንደሆነ Corder (1967) እና Littlewood (1986) ይገልፃሉ። በመሆኑም ይህ ጥናት ቀጥሎ የተገለፁትን ጥቅሞች ያስገኛል ተብሎ ይታመናል።

- አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚያስተምሩ መምህራን በተማሪዎቻቸው ሊፈፀሙ የሚችሉትን ስህተቶች አስቀድመው እንዲያውቁ ወይም እንዲገምቱ ይረዳቸዋል ።
- ከጥናቱ ውጤት በመነሳትም ለኦሮምኛ ቋንቋ አፍ ፈት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ተሻሽለው የሚዘጋጁበትን መንገድ ይጠቁማል።
- በዚህ ርእስ ዙሪያ ወደፊት ሰፊ ጥናት ለሚያካሂዱ አጥኚዎች እንደ መነሻ ሀሳብ በመሆን ሊያገለግል ይችላል።

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በሀረማያ እና በአዴሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ2003 ዓ.ም. የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ በሚፅፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የስህተት አይነቶችን በመመልከትና ከስህተት ምንጭ መላምቶች አንፃር በተማሪዎቹ ድርሰት ውስጥ ያሉትን የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርአተ ነጠብ አጠቃቀም እና ከፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ጋር የተያያዙ ስህተቶችን በመተንተን ላይ ያተኮረ ነው። ትኩረቱም በተለይ በድርሰት ውስጥ ከሚፈፀሙ ስህተቶች ውስጥ ከፍተኛ የተደጋጋሚነት መጠን ያላቸውን ስህተቶች

በመተንተን ዋነኛ ናቸው ተብለው የሚገመቱ የስህተት ምንጮችን በማብራራት ላይ ይወሰናል፡፡

## 1.5. የጥናቱ አወቃቀር

ጥናቱ አምስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ ስለጥናቱ ስራ መንስኤ አላማና ጠቀሜታ ሀሳብ የሚሰጥ፣ ሁለተኛው ምዕራፍ ለጥናቱ ተዛማጅ የሆኑ ክለሳ ድርሳናት የቀረቡበት፣ ሶስተኛው የጥናቱ የአጠናን ዘዴ ማለትም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ የአሰባሰቡ ሂደት፣ የተሰበሰቡት መረጃዎች የአተናተን ስልት የተገለፁበት፣ በአራተኛው ምዕራፍ የተሰበሰቡት መረጃዎች ውጤት በመተንተንና ማብራሪያ በመስጠት በጥናቱ ለተነሱት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥበት ሲሆን አምስተኛውና የመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ ከጥናቱ ውጤት በመነሳት አስተያየትና ማጠቃለያ የሚሰጥበት ነው፡፡

## 1.6. የቃላትና የሐረጋት ትርጓሜ

ስህተት፡- ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የተፈፀሙትን የቋንቋ አጠቃቀም የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም እና የፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተቶችን የሚመለከት ነው፡፡

የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት፡- ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በቃላት አመራረጥና አመሰራረት፣ በቃላት አደራደር፣ በቃላት አውዳዊ አገባብና በቃላት ፍቺ ምክንያት ያለውን የአረፍተ ነገር መዛባት የሚያመለክት ነው፡፡

የቋንቋ አወቃቀር ስህተት፡- በዚህ ጥናት ውስጥ የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ሲባል በአረፍተ ነገር ስምምነት (ባለቤትና ግስ፣ ፆታ መደብ፣ የቁጥር መዛባት በአያያዦች አጠቃቀም ጉድለት) የተነሳ የሚከሰቱ የአረፍተ ነገር ቅንብር ወይም ቅደም ተከተል መፋለስ ነው፡፡

የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት፡- በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ በይበልጥ የተለመዱትን የአራት ነጥብ፣ የነጠላ ሰረዝ፣ የጥያቄ ምልክት ወዘተ በዓረፍተ ነገር ውስጥ በተገቢ ስፍራ አለመዋልን የሚመለከት ነው፡፡

የፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተት፡- የሚያመላክተው የቃሉን ወይም የአገባቡን ምንነት ካለመገንዘብ የተነሳ የተለየ ትርጓሜ የሚሰጥበት ሁኔታ መሆኑን ነው፡፡

አማካይ ስህተት፡- በድርሰቶች ውስጥ የተቆጠሩት ስህተቶች ለድርሰቶቹ ጠቅላላ ድምር ተካፍሎ የሚገኘውን ውጤት የሚያሳይ ስሌት ነው፡፡

አማካይ የስህተት ድግግሞሽ፡- በድርሰቶች ውስጥ የተቆጠሩት ስህተቶች ለድርሰቶቹ ጠቅላላ ድምር ተካፍሎና በመቶ ተባዝቶ የሚገኘውን ውጤት የሚያሳይ ስሌት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን /Review of Related Literature/

ይህ ምዕራፍ ስድስት አብይ ክፍሎች አሉት፡፡ እነሡም የስህተት ትንተና፣ የስህተት ትንተና ታሪካዊ ዳራ፣ የስህተት ምንጮች፣ የስህተት ትንተና ዘዴዎች፣ የስህተት ትንተና ጠቀሜታና በሀገራችን በስህተት ትንተና ዙሪያ የተሰሩ ስራዎች ናቸው፡፡

### 2.1. የስህተት ምንነት

የአፍ መፍቻንም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋን ለመልመድ ጥረት ስናደርግ ስህተቶችን እንፈፅማለን፣ ከተፈፀሙት ስህተቶች በመማርም ቋንቋን እንለምዳለን Dulay et.al. (1982:138)፣ Brown (1994፡ 254-255)፡፡

ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ ለመልመድ በሚያደርጉት ጥረት የተነሳ በሚፈፅሙት ስህተቶች ላይ አብዛኞቹ ምሁራን የተለያዩ ምርምሮችን አካሂደዋል፡፡ ከምሁራኑ የጥናት ውጤትም መረዳት እንደሚቻለው ከስህተት ምንነት አንስቶ እስከ የስህተት አይነቶችና ምንጮች ድረስ ተቀራራቢ የሆነ አስተያየትና ብያኔ ተሰጥተዋል፡፡

አብዛኞቹ ምሁራን ስህተት የሚፈፀመው በተማሪዎች ድክመት እንደሆነ አድርገው የሚገምቱ ሲሆን ይህም ትምህርቱ በሚሰጥትበት ጊዜ በሚገባ ካለማዳመጥ፣ ለትምህርት ምንም አይነት ትኩረት ካለመስጠት ከመምህሩ የትምህርት አሰጣጥ ወይም ደግሞ ለተማሪዎቹ በቂ የልምምድ ጊዜ ካለመስጠት የተነሳ የተከሰተ ነው የሚሉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ግድፈትና ስህተት መፈፀምን በትክክል የትምህርቱ የመጀመሪያ አካል እንደሆነ አድርገው ይወስዱታል፡፡ በመሆኑም ስህተት የድክመት ምልክት ተደርጎ መታየት የሚገባው ሳይሆን የተማሪው የቋንቋ ለመዳ ስርአታዊ እድገትና ተማሪዎቹ ቋንቋውን በሚጠቀሙበት ጊዜ ያለው ሂደት እንዴት እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት የሚፈፅሙትን ስህተቶች እንደ ጉድለት በሚቆጥሩና መወገድ ያለባቸው መሆኑንም በሚያምኑት ዘንድ ተማሪዎች ስህተት መፈፀማቸው በመምህሩም ሆነ በተማሪዎች ዘንድ ዋጋ የሚያሳጣ ተደርጎ የሚወሰድ ስለነበር በርካታ ስህተቶችን መፈፀማቸውም ተግሳፅና ቁጣን ያስከትልባቸው እንደነበር ይገልፃሉ Littlewood (1986፡225)፣ Norrish (1992፡1)፡፡

በዚህም የተነሳ ተማሪዎቹ ግድፈትን ወይም ስህተትን ለመፈፀም ይፈራሉ። የፍርሃታቸው ምንጭም ተማሪዎቹ ግድፈት ወይም ስህተት በሚፈፅሙበት ጊዜ በቋንቋው አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች እንዲሁም በክፍል ጓደኞቻቸውና በመምህራቸው ይሳቅብናል ከሚል ፍርሃት የተነሳ በትምህርቱና በተማሪዎቹ ላይ ጥላቻ ያድርባቸዋል Norrish (1992፡1)።

Negara (1983፡35-36) እንዳስቀመጡት ስህተትን የአፈፃፀም ችግር ስህተት (Performance error) እና የብቃት ማነስ ስህተት (Competence error) ብለን ለሁለት መክፈል እንችላለን። የአፈፃፀም ችግር ስህተት የምንለው ግድፈትን ሲሆን ይህም ማዳጥን፣ የተወሰኑ ቃላት ወይም የሆሄያት ግድፈትን፣ ድግግሞሽን ወዘተ ያጠቃልላል። ተማሪው እነዚህን ስህተቶች የሚፈፅመው ቋንቋውን ባለማወቁ ሳይሆን በችኮላ፣ በስሜት (በጭንቀት) ውስጥ ሆኖ በመናገር ወይም በመፃፍ አሊያም በግዴለሽነት ነው። እነዚህን ግድፈቶች አፈፊቶችም ሆኑ ኢአፈ-ፈት ተናጋሪዎች ሊፈፅሟቸው ስለሚችሉ ተማሪዎቹ የሚማሩትን ቋንቋ ምን ያህል እንዳዳበሩ ሊገልፁ አይችሉም። የብቃት ማነስ ስህተት የምንለው ደግሞ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ላይ ያላቸውን ብቃት የሚያመለክተውን ነው። እነዚህም ስህተቶች በትክክል የተማሪውን ስህተት የሚያሳዩ ሲሆን ተማሪ በታላሚው ቋንቋ የት ቦታ ችግር (ጉድለት) እንዳለበት የሚጠቁሙ ናቸው። ግድፈትን (የአፈፃፀም ችግር ስህተትን) ለትክክለኛነትና ለጥንቃቄ ትኩረት በማድረግ መቀነስ ሲቻል የብቃት ማነስ ስህተትን መቀነስ የሚቻለው ግን ለታላሚው ቋንቋ ትምህርት ትኩረት በመስጠት እንደሆነ እኚሁ ምሁር ይገልፃሉ።

Brown (1994:205-206) ስህተትን፣ ግድፈት እና ስህተት በማለት ለሁለት ከፍለው ይመለከቱታል። ምሁሩ የተማሪዎቹን የቋንቋ ችሎታ በተገቢ ሁኔታ መተንተን ካስፈለገ በስህተትና ግድፈት መካከል ያለውን ልዩነት በሚገባ ማጤን እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ። ግድፈት የሚወክለው በአፈፃፀም ችግር የሚከሰት ስህተትን ሲሆን በይሆናል ግምት እና በማዳጥ (Lapse) የሚፈጠር ስህተትም በዚህ ውስጥ የሚጠቃለል ነው። እንደ Brown ገለፃ ግድፈት በማንኛውም ሰው የሚፈፀም አፈፈት እና ኢአፈፈትን የማይለይ ነው አፈፈት ተናጋሪዎች ይህን ማዳጥ ወይም ግድፈት ወዲያውኑ ተገንዝበው ሊያስተካክሉት ይችላሉ። ስለዚህ ለአፈፈቶች የብቃት

ማነስ ችግር ሳይሆን በአፍልቆት ሂደት የተወሰነ ክፍተት ማመላከቻ ነው፡፡ ይህ ክፍተትም ምናልባት ጭንቀት፣ አፍ ማዳጥ ዘፈቀዳዊ የቋንቋ አጠቃቀም እና ወዘተ ነው፡፡

ስህተት የምንለው ግን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርአት የተለየ ስርዓት ባለው መንገድ አፈንግጠው የሚፅፉትን /የሚናገሩትን/ ሲሆን የተማሪዎቹን የቋንቋ ብቃት የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ ለምሳሌ በአማርኛ ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርአት ግሶች የሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባዕታይ ፆታ ቦዝ ቅርፅ የመጨረሻ ድምፅ 'ኦ' ነው፡፡ ይህም ሰበረ ብሎ ሰብሮ፣ ሄደ ብሎ ሄዶ፣ መነዘረ ብሎ መንዝሮ በማለት ይገልፃል፡፡ ይህን የተረዳ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማር ተማሪ 'ፈነጨ' የሚለውን ግስ ወደ ቦዝ ለመለወጥ "ፈንጮ" ቢል ስህተት ሰራ እንለዋለን፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ስህተት ይሁን ወይም ግድፈት ለመረዳት በጥንቃቄ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህም ተማሪው 'ሰለቸ' ን እና 'አገኘ' ን ወደ ቦዝ ለመለወጥ በቅደም ተከተል "ሠልቆ" እና "አግኞ" ብሎ ከተጠቀመ በትክክል ስህተት ነው ብለን መደምደም ያስችለናል Brown (1994:200)፡፡

Lindmann (1996፡112) እንደሚሉት ስህተት የመማር ሂደት አንዱ አካልና ትምህርቱም በንቃት ለማካሄድ ጠቃሚ ምልክት ነው፡፡ ስህተት ቀደም ሲል በልማዳዊ ሁኔታ በተለያዩ ምክንያቶች/ቃላትን በማጥበቅ፣ በንቃት ባለመከታተል፣ ወይም በእውቀት ማነስ/ከትክክለኛው የቋንቋ አጠቃቀም ማፈንገጥ እንደሆነ ተደርጎ ይገለፅ ነበር፡፡ ሆኖም በውጭ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ከተካሄደ ምልከታዊ ጥናት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ከታላሚው ቋንቋ አገባብ አለማፈንገጥም ስህተት ላለመፈፀም ዋስትና ሊሆን አይችልም፡፡ ለምሳሌ የጀርመንኛ ቋንቋን የሚማር አንድ ኖርዌጅያዊ ተማሪ በሰዋሰው በኩል ትክክለኛ የሆነ ዐ.ነገር ሊመሰርት ይችላል፡፡ ነገር ግን ስለ ፃፈው ጉዳይ እንደገና ዓረፍተ ነገር እንዲፅፍ ቢጠየቅ የሚሰጠው ምላሽ ከበፊቱ የተለየ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም ሊከሰት የቻለው ሃሳብን በትክክል ካለመገንዘብ የተነሳ ይሆናል፡፡ በእያንዳንዱ የቋንቋ ተማሪ የሚፈፀሙ ስህተቶችም የተማሪው ዕድገት አመልካቾች እንደሆኑ ተደርገው መቆጠር ያለባቸው ናቸው፡፡

Corder (1974:24) እንዳስቀመጡት ስህተቶችን ስርዓት ያላቸው እና ስርአት የሌላቸው በማለት በሁለት መክፈል ይቻላል። አፈፊት አዋቂዎች በንግግራቸው መሀከል ለስህተት ሊጋለጡ ይችላሉ ይህም በማስተዋል ችግር በአካላዊ ሁኔታ ማለትም በድካም፣ በጭንቀት፣ በተመስጦ ወዘተ… የተነሳ ሊሆን ይችላል። በእንደዚህ አይነት ሁኔታ የሚፈፀም ስህተት የስህተት ፈፃሚውን እውቀት እና የቋንቋ ብቃት አያመለክትም:: ስህተት ፈፃማው ወዲያውኑ ሊያስተካክለው ይችላል። እንደዚህ አይነቱን ስህተት ግድፈት እንለዋለን የቋንቋ ተማሪው ስርዓታዊ በሆነ መንገድ የሚሳሳተውን ስህተት "ስህተት" ብለን ስንጠራው ተማሪው እስኪታረም ወይም አፈፊት ተናጋሪዎች እንደዚያ እንደማይሉ እስኪገነዘብ ድረስ ትክክል ነው ብሎ በስህተት ይቀጥላል ይህንንም ለይቶ ማወቅ ለቋንቋ ትምህርት ትልቅ ፋይዳ እንዳለው እኚህ ምሁር ያስገነዝባሉ።

ከላይ በተደጋጋሚ ከቀረቡት ሃሳቦች የምንረዳው የቋንቋ መማር ሂደት ከስህተት ሙሉ በሙሉ ፀድቶ የተቀመጠ ሳይሆን ለተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ተፅዕኖዎች የተጋለጠ ስለሆነ መታሰብ ያለበት ትልቁ ጉዳይ ስህተት ለምን ይፈጠራል? በሚል የማስተማሪያ ዘዴውን መኮነን ሳይሆን ይልቁንም በተለያዩ ምሁራን እንደተጠቆመው ተማሪዎቹ በሚፈፅሟቸው በርካታና የተለያዩ ስህተቶች ላይ ጥናት በማድረግና የስህተት ትንተና በማካሄድ የሚገኘውን ውጤት ለመማር ማስተማር ሂደት ስኬታማነት የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ስለሚኖረው ተከታታይነትና ቀጣይነት ያለውን የስህተት ትንተና ማካሄድ ተገቢ ነው።

## 2.2. የስህተት ትንተና ታሪካዊ ዳራ

የስህተት ትንተና ከንፅፅራዊ ትንተና ቀጥሎ የመጣና በንፅፅራዊ ትንተና ድክመት ላይ ተንተርሶ ብቅ ያለ የቋንቋ ጥናት ዘርፍ እንደሆነ ምሁራን ይገልፃሉ። የስህተት ትንተና የተማሪዎችን ስህተት መሰረት አድርጎ ስህተትን ግልፅ በሆነ አላማ አመቺና ውጤታማ በሆነ መንገድ የመተንተን ሂደት ነው፤ የስህተት ትንተና የስህተት አይነቶችን እና ምንጫቸውን ለመተንተን የምንጠቀምበት ሰፊ ተቀባይነት እያገኘ የመጣ የጥናት መስክ ነው Ellis (1989:51)፣ Sharma (1986:76)።

እስከ 1960ዎቹ መጨረሻ ድረስ በቋንቋ መማር ውስጥ የሚስተዋሉት ስህተቶች ይጠኑ የነበረው በንፅፅራዊ ትንተና ዘዴ ነበር፡፡ የንፅፅራዊ ትንተና ይካሄድ የነበረው የተማሪውን አፍ መፍቻ ቋንቋ እና ለትምህርት በቀረበው (በታላሚው ቋንቋ) መካከል የሚስተዋሉ ስነ-ልሳናዊ ልዩነቶችን በማነፃፀር የስህተት ምንጩን ለመጠቆም ይሞክራል፡፡ በንፅፅራዊ ትንተና በሁለተኛ ቋንቋ የመማር ሂደት ውስጥ ለሚከሰተው ስህተት ምንጩ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት (አሉታዊ ሽግግር) ብቻ እንደሆነ በመግለፅ ሌሎቹን የስህተት ምንጮች ለማጥናት ባለመቻሉ ምክንያት ይህንን አብይ ድክመት ለመቅረፍ የስህተት ትንተና ዘዴ እንደ አንድ የቋንቋ ጥናት መስክ ብቅ ያለ ስህተትን አስመልክቶ የሚካሄድ የስህተት ትንተና ዘዴ ነው Richards (1974:4)፡፡

የስህተት ትንተና በ1967 (Coder) በተባለ ምሁር እንደተጀመረ ድርሳናት ያወሳሉ፡፡ የስህተት ትንተና ዘዴ ወደ ጥናቱ መስክ ብቅ ማለት በቋንቋ ትምህርት ሂደት የሚያጋጥሙ ስህተቶች ምንጫቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ብቻ እንዳልሆነና ሌሎች በርካታ የስህተት ምክንያቶች መኖራቸውን የሚያመላክት አዲስ እና በአይነቱ ልዩ የሆነ የጥናት ውጤት እውን የሆነበት ነው፡፡ በመሆኑም የስህተት ትንተና የአፍ መፍቃ ቋንቋ ተፅዕኖን የሚመለከተው እንደ አንድ የስህተት ምንጭ እንጂ እንደ ብቸኛ የስህተት ምንጭ አድርጎ አይደለም፤ ከዚህ በተጨማሪ የታላሚው ቋንቋ ውስብስብ ባህሪያት ቋንቋውን በመማር ሂደት የስህተት ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ የስህተት ትንተና ጥናት ይፋ ማድረጉ የበርካታ ባለሙያዎችን ትኩረት ሊስብ ችሏል Dulayetal (1982)፣ Spolsky (1989)፡፡

የስህተት ትንተና የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም በናሙናነት በመሰብሰብ ስህተቶችን ለይቶ ያወጣል፡፡ ከዚህም የስህተቶቹን ምንነት በመግለፅ ምንጫቸው ምን ሊሆን እንደሚችል መላምት ይመታል፤ አያይዞም የስህተቶቹን የክብደት ደረጃ ይለያል፡፡፡ በዚህም መሰረት Richards እንግሊዘኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ አፋቸውን በተለያዩ ቋንቋዎች የፈቱ ተማሪዎችን ስህተቶች ወስደው በማጥናት በሁለቱም ላይ የተንፀባረቁ አራት የስህተት አይቶችን መለየት ችለዋል፡፡ እነርሱም ስህተት የሆነ ድምዳሜን መከተል፣ የታላሚውን የቋንቋ ህግ ጠንቅቆ አለማወቅ፣ ህጉን ባልተሟላ ሁኔታ መተግበር እና የተሳሳተ ዘዴ ሲሆኑ ስህተቶቹም ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ውጭ የተፈጠሩ ናቸው Dulay et.al. (1982:138-141)፣

Ellis (1989:296)፣ Corder (1974:19) እና James (1996፡185)፡፡ በርግጥ ተማሪዎች ስህተትን ይፈፅማሉ፤ እነዚህ ስህተቶችም ምልከታ ሊደረግባቸው፣ ሊተነተኑ እና በየክፍላቸው ሊሰደሩ ይገባል፡፡ ይህ የተማሪዎች የስህተት ጥናትም የስህተት ትንተና ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ የስህተት ትንተና ለተማሪዎች ስህተት ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮች ለመለየት ሁሉንም አማራጮች ይጠቀማል Brown (1994:206)፡፡ ይሁን እንጂ የስህተት ትንተና ከድክመት የፀዳ ነው ልንል አንችልም፡፡ ከእነዚህም ድክመቶች አንዱ ለአንዱ ስህተት መፈፀም ከአንድ በላይ የሆኑ ምክንያቶች ሊኖሩት ቢችሉም ትንተናው በአንዱ ውስጥ ሲያካትተው ሌሎቹ ምንጮች ችላ ሊባሉ መቻላቸው ነው፡፡ ሌላው በንፅፅራዊ ትንተና አቀንቃኞች የሚነሳ ሲሆን አንድን ስህተት ሁለንተናዊ ነው ማለት ወይም ደግሞ ከታላሚው ቋንቋ ተፅዕኖ የተነሳ የተፈጠረ ነው ብሎ ለመፈረጅ የስህተት ትንተና የሚከተለው በተለያዩ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችን የጋራ ስህተት የመቀነስ አቅጣጫ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መጠናት አለበት መባሉ ነው Dulay et.al. (1982:197)፣ James (1996፡186-187)፡፡

የስህተት ትንተና ቢያንስ ሶስት መሰረታዊ ድክመቶች አሉበት፤

ሀ. በስህተት ትንተናው ሂደት ላይ በፅሁፍ ውስጥ የሚገኙትን ወይም የታዩትን ስህተቶች ለይቶ በግልፅ ለመናገር አለመቻልና ምንጫቸውን በተገቢ ሁኔታ ማስፈር አለመቻል፡፡

ለ. የስህተት አይነቶችን ግልፅ በሆነ ሁኔታ ያለማስፈር እና

ሐ. የተማሪዎችን ስህተቶች ቀላል በሆነ መንገድ መለያየት አለመቻል ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ ይህ የጥናት መስክ ድክመቶችን እያረመ በመምጣት ላይ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ ሰፊ ተቀባይነት ከማግኘቱም ባሻገር በተግባራዊ ስነልሳን እና በቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ትልቅ አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ እንደሆነ ምሁራን ይስማሙበታል Dulay et.al. (1982:141-146)፡፡

## 2.3. የስህተት ምንጮች

በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት ውስጥ ተማሪዎቹ ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች ፍንጭ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ በጣም በርካታ የሆኑ ምክንያቶች እንዳሉ

የሁለተኛ ቋንቋ መማርን አስመልክቶ ከተፃፉት ድርሳናት ውስጥ መመልከት ይቻላል፡፡ ቀደም ባሉት ክፍሎች ለመጠቆም እንደተሞከረው የስህተት ትንተና ዘዴ ከመጀመሩ በፊት የነበረው የንፅፅራዊ ትንተና ያተኩር የነበረው የታላሚውን ቋንቋ መዋቅር ከተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር በማነፃፀር የችግሩን ምንጭ ማሳየት ይቻላል በሚል ሀሳብ ላይ ነበር፡፡

Dulay et.al. (1982:144) ቋንቋን በመማር ወይም በመልመድ ሂደት የሚስተዋሉት የስህተቶች ምንጭ የውጫዊና ውስጣዊ ተፅዕኖዎች ድምር ውጤት እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህሩ የስልጠና ሂደቶች የተማሪው ባህላዊ አውዶች እና ለቋንቋው የሚኖረው ተጋልጦ እና የመሳሰሉት ውጫዊ እና እንዲሁም የአፍ መፍቻ ቋንቋ አሉታዊ ሽግግር የሁለተኛ ቋንቋን ህግጋት በተግባቦት ሂደት ለመተግበር ሲሞክር የሚጠቀምባቸው የተሳሳቱ መላምቶች ከተማሪው ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ውስጣዊ ጉዳዮች የተናጠልም ሆነ የጋራ ድምር ውጤት ናቸው፡፡ ምሁራን እንደሚገልፁት የስህተት ምንጮች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በአንድ በኩል በርካታ ስህተቶች ከአንድ የስህተት ምንጭ ሊመጡ እንደሚችሉና በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ስህተት የበርካታ የስህተት ምንጮች ውጤት ሊሆን ይችላል፤ በመሆኑም ስህተቶችን ከምንጫቸው አኳያ ለመመደብ ሙከራ የሚያደርግ ተመራማሪ አስቸጋሪና ዘፈቀዳዊ ውሳኔዎችን የማሳለፍ እድል እንደሚገጥመው ምሁራኑ ጨምረው ይገልፃሉ፡፡

Ellis (1994:62-23) የስህተት መንስኤን አስመልክቶ እንደሚገልፁት፤ በስህተት ትንተና ሂደት የአንድን ስህተት ምንጮች በእርግጠኝነት መናገር በጣም አስቸጋሪና አሻሚ ሊሆን ይችላል፤ የስህተት ምንጮች መላምታዊ መሆናቸውን Dulay et.al. (1982:144) ይጠቁማሉ፡፡ በምሁራኑ ከተገለፁት ሀሳቦች መገንዘብ እንደሚቻለው አንድን ስህተት መንስኤው አንድና ነጠላ የሆነ የስህተት ምንጭ ነው ብሎ በድፍረት መግለፅ ከተሳሳተ ማጠቃለያ ላይ እንድንደርስ ሊያደርገን እንደሚችል ነው፡፡ በመሆኑም የአንድን ስህተት ምንጭ መጠቆም ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሻ ጉዳይ መሆኑን እንድንገነዘብ ያደርገናል፡፡

ይህ ጥናት በሁለተኛ ቋንቋ የመማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው በበርካታ የመስኩ ባለሙያዎች

ተዘውትረው የሚጠቀሱ መላምቶችን ማለትም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የውስጥ ቋንቋ ተፅዕኖ የመማር ማስተማር ሂደት ድክመትና ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ይቀርባሉ።

### 2.3.1. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ከስህተት ምንጮች ውስጥ አንዱ ነው። የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት አዲስ ቋንቋን ለመልመድ ጥረት ስናደርግ የቀደመው ቋንቋ ጣልቃ የሚገባበት ሂደት ነው Jackson (1987:101)፣ Norrish(1992:22)፣ Dulay et.a. (1982:171)። ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን በሚማሩበት ጊዜ የተወሰነ ክፍተት ሲያጋጥማቸው ያን ክፍተት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ተጠቅመው ሊሞሉት ይሻሉ። ይህ ጣልቃ ገብነት ብዙ ጊዜ ሳይታሰብ የሚከሰት ሲሆን ጎልቶ የሚታየውም ተመሳሳይነት ባላቸው ቋንቋዎች መሀል ነው።

ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት ላይ የተማሪ የአፍ መፍቻ ቋንቋ አሉታዊ ተፅዕኖ ተማሪው ለሚፈፅማቸው ስህተቶች እንደ አንድ ምክንያት ሊቆጠር እንደሚችል በርካታ ምሁራን ይስማሙበታል፤ እንደ Dulay et.al. (1982:96) በአፍ መፍቻነት የዳበረ የቋንቋ ልምድ አንድን አዲስ ቋንቋ በመማር ሂደት ጣልቃ እየገባ በሚያደርሰው አሉታዊ ተፅዕኖ የተነሳ ስህተት ሊፈፅም ይችላል። ከነዚሁ ሀሳብ ጋር በተያያዘ Norrish (1992፡22) ሲገልፁ ቋንቋን የመማር ሂደት የልምድ ክምችት ውጤት በመሆኑ የተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልምድ ጣልቃ በመግባት የስህተት ምንጭ ሊሆን ይችላል። የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው የድምፅ፣ የቃላት አጠቃቀም፣ የሀረግ እና የዓረፍተ ነገር አወቃቀር ውስጥ ሊስተዋል የሚችል ቢሆንም ስህተቱ ጎልቶ የሚታየው ግን በንበት በመሆኑ ከንግግር ቅላፄ (ቃና) በመነሳት የተናጋሪውን ማንነት ማወቅ እንደሚቻል Edge (1989:7-9) በምሳሌ በማስደገፍ ያብራራሉ።

Negera (1983:36) እንደሚገልፁት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች መሰረታዊ የስህተት ምንጭ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ተፅዕኖ ሲሆን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ የታላሚውን ቋንቋ ቅርፅ ከአፍ መፍቻ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ወይም ተቀራራቢነት ባለው መንገድ ያመነጫል። ይህ ከአፍ መፍቻ ቋንቋው መዋቅር ጋር

ተቀራራቢነት ያለው አጠቀቀም ከታላሚው ቋንቋ ትክክለኛ መዋቅር ያፈነገጠ ሲሆን ተማሪውን ለስህተት ይዳርጋል፡፡

ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ እየተማረው ሲሄድ የአፍ መፍቻ ቋንቋው ከታላሚው ቋንቋ ጋር ይበልጥ እየተዋሀደ የሚሄድ በመሆኑ የሚፈጠሩ ስህተተቶችም ቀስ በቀስ እየቀነሱ ይሄዳሉ ተብሎ ይገመታል፤ Brown (1994:213-214) እንደሚያስረዱት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ በሚማሩበት መጀመሪያ ደረጃ ላይ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ምንጭ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ እንደሆነ በብዙ ምሁራን ተረጋግጧል፡፡ በነዚህ የመጀመሪያ ደረጃዎች የሁለተኛ ቋንቋውን አጠቃቀምና ስርአት ከመልመዳቸው በፊት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ብቸኛው ልምዳቸው ነው፡፡ ይህ በመሆኑ ተማሪዎቹ አፍ ከፈቱበት ቋንቋ ሀሳብ እየወሰዱ በታላሚው ቋንቋ ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡ አጠቃቀማቸውም አወንታዊም አሉታዊም ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡ አወንታዊ የምንለው የታላሚው ቋንቋ እና የተማሪ የአፍ መፍቻ ቋንቋ አንድ አይነት ባህሪ ሲኖረው ሲሆን በዚህ ጊዜ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ አሉታዊ ተፅዕኖ የተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ እና ታላሚው ቋንቋ የተለያየ ስርአት ይኖራቸውና ታላሚው አፍ የፈታበትን ቋንቋ ስርአት በታላሚው ቋንቋ ሲጠቀምበት ከታላሚው ቋንቋ ስርአት ስለሚያፈነግጥ ለስህተት ይዳረጋል፡፡ ስለዚህ አሉታዊ ተፅዕኖ ለስህተት ምንጭ እንደሆነ ይታመናል፡፡

Lado (1964) በበኩላቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ የአፍ መፍቻ ቋንቋውን የድምፅ፣ የቃል ወይም የዓረፍተ ነገር ስርዓት በሁለተኛ ቋንቋ የአጠቃቀም ስርዓት ጣልቃ መግባትን የሚገልፅ ፅንሰ ሃሳብ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

በተጨማሪም የታላሚውን ቋንቋ ትክክለኛ የሆነ ቃል ወይም ፅንሰ ሃሳብ በማይታወቅበት ጊዜ የአፍ መፍቻ ቋንቋን የተለያዩ ስነ-ልሳናዊ ባህሪያት ቃል በቃል በመተርጎም ለመጠቆም ሙከራ በሚደረግበት ጊዜ ስህተት ሊከሰት ይችላል Norrish (1992፡42)፡፡ በመሆኑም የአንድን ቋንቋ ፍፁም አቻ የሆነን መዋቅር ማግኘት አስቸጋሪ ሲሆን ታላሚውን ቋንቋ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መተርጎም የስህተት ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ Dulay etal (1982:119)፣ Lott (1983:259)፣ Sharma (1979:75) እና Corder (1978:266) በአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርአት እያሰቡ በታላሚ ቋንቋ ለመጠቀም ሙከራ ሲደረግ የትርጉም ስህተት ሊከሰት እንደሚችል ይጠቁማል፤. በመሆኑም ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ የተነሳ የሚከሰቱ ስህተቶች ታላሚውን ቋንቋ በአፍ መፍቻ ቋንቋ በቀጥታ ከመተርጎም ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ስህተቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ምንም እንኳን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ለስህተት መከሰት በምንጭነት ሊጠቀስ የሚችል ቢሆንም ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት ዋነኛና ብቸኛ የስህተት ምንጭ ሊሆን እንደማይችል እና ከአፍ መፍቻ ጣልቃ ገብነት ውጭ የሆኑ በርካታ የስህተት ምንጮች እንዳሉ ምሁራን ይጠቁማሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ Johanson (1976፡322-336)፣ Lott (1983፡255-260) እንደሚገልፁት በተለይ ከ1960ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ቋንቋን የመማር ሂደትን ከቋንቋ ለመዳ ንድፈ ሀሳብ አንፃር ማጥናት መጀመሩና የተሻለ መረጃ መገኘቱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልምድ ዋነኛው የስህተት ምንጭ ነው የሚለው እምነት እንዲቀየር ምክንያት ሊሆን ችሏል። እንዲያውም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚፈፅሟቸው አብዛኞቹ ስህተቶች ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ጋር ግንኙነት የሌላቸው እንደሆኑና ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ የተነሳ የሚከሰቱ ስህተቶች እጅግ አናሳ እንደሆኑ Dulay et.al. (1982:140)፣ Broughton (1978:136) በጥናት ላይ የተመሰረተን መረጃ በማስደገፍ ገልፀዋል።

Ellis (1989:24)፣ Negera (1983:36):: እንዳስቀመጡት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት የተነሳ ከተፈጠሩት ስህተቶች በተጨማሪ በግምታዊ መልስ በቂ ልምምድ ባለማድረግ የታላሚውን ቋንቋ ህግ ህጉ በማይሰራባቸው ቦታዎች በመጠቀም የተነሳ የሚፈጠሩ ስህተቶች እንዳሉ አመልክተዋል። እኚሁ ምሁር እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር ከ1971-1983 ድረስ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ የተሰሩ ሰባት ጥናቶችን መሰረት አድርገው እንዳስቀመጡት ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃገብነት ምክንያት የሚፈጠሩ ስህተቶች ከሶስት በመቶ እስከ ሃምሳ በመቶ እንደሚደርሱ ጠቁመዋል። ይህም የሚያሳየን ቢያንስ ግማሽ ያህሉ ስህተቶች ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃገብነት ውጭ በሆኑ ምክንያቶች የሚፈጠሩ መሆናቸውን ነው።

### 2.3.2. የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ

ሌላው የስህተት ምንጭ ነው የሚባለው የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ሲሆን ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት የአፍ መፍቻ ቋንቋን ጣልቃ በማስገባት የሚፈፀም ስህተት ሳይሆን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ታላሚው ቋንቋ ውስብስብ በመሆኑና ስለታላሚ ቋንቋ ህግጋት እና ስርአት በቂ የሆነ ግንዛቤ ባለማግኘታቸው የተነሳ በተሳሳተ መንገድ በንግግርም ሆነ በፅሁፍ አማካኝነት መልዕክት ለማስተላፍ በሚሞክሩበት ጊዜ የሚስተዋል የስህተት ምንጭ እንደሆነ ምሁራን ይገልፃሉ። ተማሪው ለታላሚው ቋንቋ በተወሰነ ደረጃ ከመጋለጡ የተነሳ ያገኛቸውን ጥቂት ወይም የተወሰኑ የቋንቋውን ስርዓቶች በመጠቀም በንግግር ወይም በፅሁፍ ሀሳቡን ለመግለፅ ሙከራ በሚያደርግበት ጊዜ ስህተት ሊፈፅም ይችላል። እንደዚህ ያሉ ስህተቶች ምንጫቸው የታላሚዎች ቋንቋ ውስብስብ ባህሪይ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ ስህተቶች በመሆናቸው ስህተቶቹ በውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ምክንያት የሚመነጩ ሊሆኑ ይችላሉ (Norrish 1992፣ Littlewood 1984፣ James 1991 እና Brown 1994)።

በምሁራኑ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው በውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ምክንያት የሚፈፀሙ ስህተቶች የሚከሰቱት ከታላሚው ቋንቋ ውስብስብ ባህሪይ የተነሳ ሊሆን ይችላል። እነዚህን የቋንቋውን ውስብስብ ስርአቶች ለተግባቦታዊ ተግባር ለማዋል ሙከራ በሚያደርግበት ወቅት ተማሪው ስህተት ሊፈፅም ይችላል (Richards 1974፣ Dulay et.al. 1982 እና Littlewood 1984)። በውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ የተነሳ የሚከሰቱ ስህተቶች የታላሚውን ወይም ለትምህርት የቀረበውን ቋንቋ ስርዓት በማፋለስ የሚፈጠሩ ስህተቶች መሆናቸውን ይገልፃሉ። በውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ምክንያት የሚከሰቱ ስህተቶች ተማሪው በታላሚው ቋንቋ የሚያሳያቸውን መሻሻሎችና እድገትን የሚጠቁሙ ፍንጮች በመሆናቸው እድገታዊ ስህተቶች ሊባሉ እንደሚችሉ ምሁራኑ ይጠቁማሉ። በስህተት ትንተና ላይ የተሰማሩና ጥናታቸውን ያካሄዱ ተመራማሪዎች በጥናታቸው እንዳረጋገጡት አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ቀድሞ ከነበረው እምነት በተፃራሪ እድገታዊ ስህተቶች ወይም ውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ የተነሳ የሚከሰቱት ስህተቶች ናቸው ሲሉ Dualay et.al. (1982:164) ይገልፃሉ። ይህ ማለት ግን ከተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ የተነሳ የሚፈፀሙ ስህተቶች የሉም ማለት እንዳልሆነና በጣም ጥቂት

የሆኑ ስህተቶች ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት የተነሳ እንደሚከሰቱ ምሁራኑ አክለው ጠቁመዋል፡፡

ተማሪዎች በውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ የተነሳ ከሚፈፅሟቸው ስህተቶች ምንጭ አንዱ የተሳሳተ ማጠቃለያ ላይ በመድረስ የሚፈፅሟቸው ናቸው፡፡ የተሳሳተ ማጠቃለያ ስንል ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ እየለመዱ ሲመጡ የተማሩትን አዲስ ስርዓት መሰረት አድርገው በቋንቋው ለመጠቀም ሲሞክሩ የሚሳሳቱትን ማለታችን ነው፡፡ ይህም ታላሚው ቋንቋ በአብዛኛው የሚጠቀምበት የራሱ መዋቅር ይኖረውና ያመዋቅር በሁሉም የማይሰራ ከሆነ ተማሪዎች መዋቅሩን ባጠቃላይ ለቋንቋ እንደሚሰራ አድርገው ሲቀበሉትና ሲጠቀሙበት የሚፈጠረውን ስህተት ያሳያል፡፡ ለምሳሌ በአማርኛ ቋንቋ በላ ብሎ ብላ እንደሚባል የተረዳ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማር ተማሪ ‹‹መጣ›› የሚለውን ቃል መሰረት አድርጎ ‹‹ምጣ›› ቢል በተሳሳተ ማጠቃለያነት የተነሳ የተሳሳተው ነው ለማለት እንችላለን፡፡ (Norrish 1992:31-32፣ Littlewood 1986:23፣ Jackson 1987:101 እና Brown 1994:214)፡፡

የተሳሰተ ማጠቃለያ በየትኛውም የቋንቋው ክፍል ማለትም በንበት፣ በቃላት አጠቃቀም፣ በትርጉም፣ በነጠላና ብዙ ቁጥር አጠቃቀም፣ በእምር አመልካች ወዘተ ሊከሰት ይችላል፡፡ ይህ ስህተት ቋንቋውን በመማር ብዙ ከቆዩት ይልቅ በአዲስ ጀማሪዎች ላይ የበለጠ ይንፀባረቃል (Negera 1983:36)፡፡

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ለውስጠ ቋንቋ ስህተቶች የሚያጋልጣቸው የተሳሳተ ማጠቃለያ ብቻ አይደለም፡፡ ያልተሟላ ትምህርት፣ የተሳሳተ ተዛምዶ እና ቃላትን አለአግባብ መጠቀም በውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ መንስኤ ለሚፈጠሩ ስህተቶች ምክንያቶች ናቸው፡፡ እንደ Negara (1983:37-40) አገላለፅ ባልተሟላ ትምህርት የሚፈጠር ስህተት ስንል የቋንቋ ተማሪው የቋንቋውን መዋቅር ቃላት የአገላለፅ ስልት ወይም ሌሎች የታላሚውን ቋንቋ ባህሪያት በግማሽ በመማሩ የተነሳ የሚፈጠረውን ስህተት ማለታችን ነው፡፡ ስለዚህም ተማሪው በቋንቋው የሚገኙትን ፈሊጣዊ አነጋገሮችና ምሳሌያዊ ንግግሮች እንዲሁም ሰዋሰዋዊ ስርአቶች በከፊል በትክክል በከፊል ደግሞ በስህተት ሲያፈልቅ ይስተዋላል፡፡ እነዚህን ስህተቶች በብዙ ከፍሎ መመልከት እንደሚቻል እኚሁ ምሁር ይገልፁና ለምሳሌ ያህልም ያልተሟላ ሰዋሰዋዊ ህግ

የባለቤትና የግስ አለመጣጣም፣ ያልተሟላ የመስተዋድዳዊ ሀረጎች ትምህርት፣ ያልተሟላ የፈሊጣዊ አነጋገሮች ትምህርት እና ያልተሟላ የስነ-አገባብ ትምህርት ብሎ መክፈል ይቻላል።

በአጠቃላይ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ላይ የተደረጉት አብዛኞቹ ጥናቶች ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ይልቅ በውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ የሚፈጠሩት ስህተቶች አብላጫውን ቁጥር እንደሚይዙና ከዚህም የተነሳ የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የስህተት ምንጭ መሆኑን በርካታ ምሁራን ገልፀዋል (Dulay et. al. 1982፣ Broughton 1978 እና Norrish 1992)::

### 2.3.3. የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶችና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለስህተት ከሚዳረጉባቸው ምክንያቶች መካከል የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት ተጠቃሽ እንደሆኑ በርካታ ምሁራን ይገልፃሉ። እነዚህን የስህተት ምንጮች Negra (1983:40) ውጫዊ ተፅዕኖዎች ሲሏቸው Brown (1994:215-217) ደግሞ የትምህርት አውድ ችግር ይሏቸዋል። Brown አውድ የሚለው ቃል የመማሪያ ክፍልን ከመምህሩ እና ካሉት የትምህርት መሳሪያዎች ጋር አንድ ላይ የያዘ እንደሆነ ያስረግጣሉ። ይህም አውድ በትምህርት ሂደት ወቅት ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ማጠናከሪያነት ከማዋል ይልቅ በትምህርቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሲያሳድር ለስህተት መፈጠር ምክንያት ይሆናል።

Norrish (1992:12) ደካማ የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ተማሪዎቹ ስህተት እንዲፈፅሙ ምክንያት ስለሚሆን መምህሩ በቋንቋው ትምህርት ሂደት ሊፈጠሩ የሚችሉ ስህተቶችን ለመቅረፍ ተገቢ የማስተማሪያ ዘዴ በመምረጥና በመከተል በተማሪዎቹ ፍላጎቶች የቋንቋ ችሎታና ከመሳሰሉት ነጥቦች ጋር እያገናዘቡ የቋንቋ ይዘቶችን ማደራጀት እንዳለበት ያስገነዝባሉ። በተጨማሪም መምህሩ ተማሪዎች ቋንቋውን በመማር ሂደት ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች የሚሰጠው ምጋቤ ምላሽ ደካማ ከሆነ ተማሪዎቹ ስህተቶችን እራሳቸው በራሳቸው ለማረም የሚኖራቸው ዕድል ጠባብ

ስለሚሆን ቋንቋውን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ሊቀንስ ይችላል። ተማሪዎች ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች መምህሩ በተለያዩ ስልቶች ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ ስህተቱ በተማሪው ፅሁፍ ውስጥ ስር እየሰደደ ሊሄድ ይችላል (White 1994፡109)። መምህሩ የተማሪዎችን ስህተት ማረም አለበት ሲባል ግን ተማሪዎቹ የሚፈፅሟቸውን እያንዳንዱ ስህተት ቃል በቃል እየለቀመ ያስተካክለዋል ማለት አይደለም። ይልቁንም መምህሩ የተለያዩ ስልቶችን ተግባራዊ በማድረግ ተማሪዎችን በጥንድ በቡድን በማደራጀት በስህተቶቻቸውን ዙሪያ እንዲነጋገሩና ስህተቶቻቸውን እርስ በርሳቸው የሚተራረሙበትን መንገድ ማመቻቸት ሊሆን ይችላል።

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የመምህሩ ብቃት ሊለካባቸው ከሚችልባቸው መስፈርቶች መካከል የቋንቋ ትምህርቱ ሳቢና ማራኪ አድርጎ ማቅረብና የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ውጤታማነት ተጠቃሾች ናቸው። የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ ውጤታማ ካልሆነ ተማሪዎቹ ለስህተት የመጋለጣቸው እድል የሰፋ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም የቋንቋ መርሃ ትምህርቱ የይዘት አደረጃጀትና አቀራረብ የቋንቋውን ይዘቶች ሙሉ በሙሉ ማካተት አለማካተቱና የመሳሰሉት ሁኔታዎች አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማር ተማሪ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ቀላል እንደማይሆን ምሁራን ይጠቁማሉ። Broughton (1978፡134) በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ስህተት እንዲከሰት ምክንያት ሊሆን ከሚችሉ ነገሮች ውስጥ መርሃ ትምህርቱ የማስተማሪያ መሳሪያዎች መምህራንና ተማሪዎች ይጠቀሳሉ ሲሉ ይገልፃሉ።

ስህተቶች ከመማር ማስተማር ድክመት ከመርሃ ትምህርት የይዘት አመራረጥ አደረጃጀትና አቀራረብ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ልንገነዘብ እንችላለን። የመምህሩ የማስተማር ችሎታ የቋንቋ ትምህርቱን በጥራት ለማቅረብና ተማሪዎቹ ሊፈፅሟቸው የሚችሏቸውን ስህተቶች ለመቅረፍ የሚኖረው ፋይዳ ቀላል እንደማይሆን መገመት ይቻላል። በመሆኑም የቋንቋ መምህራን ቋንቋውን ለማስተማር ያላቸው ብቃት በትምህርቱ ሂደት አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ አይቀርም።

Alwright (1991:84) በብዙዎች የአለም ክፍሎች የሁለተኛ ቋንቋ የሚሰጠው በቋንቋው ኢ-አፈፊት በሆኑ መምህራን መሆኑን ጠቁመው እነዚህ በቋንቋው ኢ-አፈፊት የሆኑ መምህራን የታላሚውን ቋንቋ ትክክለኛውን ሞዴል ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቻቸው ማስጨበጥ ሊያዳግታቸው ስለሚችል ቋንቋውን የሚማሩ ተማሪዎች የመምህራቸውን የተሳሳተ ሞዴልነት በመከተል ስህተት ሊፈፅሙ ይችላሉ። በዚህም ምክንያት በታላሚው ቋንቋ ኢ-አፈፊት በሆኑ መምህራን የሚማሩ ተማሪዎች የሚለማመዱት ትክክለኛ ያልሆነ የቋንቋውን ሞዴል ስለሚሆን ተማሪው ቋንቋውን ለተግባቦታዊ ተግባር ለመገልገል ሲሞክር ስህተት ሊፈፅም ይችላል።

ከላይ በምሁራኑ ከቀረበው ሀሳብ እንደምንገነዘበው አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚያስተምር መምህር ለተማሪዎቹ በሁሉም ዘርፍ ትክክለኛ አርአያ መሆን ካልቻለ ተማሪዎችም የመምህሩን ፈለግ በመከተል ስህተት ይፈፅማሉ። ስለዚህ በቋንቋው ኢ-አፈፊት የሆነ መምህር ታላሚውን ቋንቋ ሲያስተምር በቋንቋው ክሂሎች ሆነ በእውቀት ዘርፎች የተሻለ ብቃት ያለውና ትክክለኛ ሞዴል ሆኖ መገኘት ይጠበቅበታል ምክንያቱም ተማሪዎች መምህሩ የሚያስተምረው የሚናገረው ማንኛውም የሚያከናውናቸው ነገሮች ትክክለኛ እና ተገቢ ነው ብለው የሚቀበሉና የሚተገብሩ በመሆናቸው ነው። ስለዚህ የቋንቋ መምህሩ ተማሪዎቹ በዚህ ምክንያት ለስህተት እንዳይዳረጉ በተቻለ መጠን እውነተኛ እና ትክክለኛ ሞዴል ሆኖ መገኘት ይኖርበታል።

### 2.3.4. ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች

Norrish (1992:19) እንደሚሉት ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የስህተት ምንጮች ከተጨማሪ ተማሪዎቹ ስህተቶቹን እንዲፈፅሙ የሚያደርጋቸው ስነልቦናዊ ምክንያቶች እንዳሉ ነው። ስነ ልቦናዊ ጉዳይ ሲባል የሚያያዘው ከተማሪዎቹ የግል ጉዳዮች ጋር ሲሆን ይህም ተማሪዎቹ ከክፍል ውጭ ስላለው ሁኔታ በአእምሮአቸው ውስጥ ይዘውት የመጡት ጉዳይ በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በደንብ እንዳይከታተሉ ስለሚያደርጋቸው ነው። የዚህ አይነቶቹ ስህተቶችም በCorder ‹‹ያላስፈላጊ ድግግሞሽ›› ተብለው መጠራታቸውን Norrish (1992) የገለፁት ሲሆን

እነዚህ ስህተቶች ከቋንቋ መማር ጠቃሚ ክፍሎች ከሚቆጠሩት ስህተቶች የተለዩ ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው፡፡

Richards (1974)፣ Richards and Sampson (1990) እና Norrish (1992) ተማሪው ለታላሚው ቋንቋ ያለው አመለካከት ቋንቋውን ለመማር ያለው ፍላጎትና የመሳሰሉ ሁኔታዎች ቋንቋውን በመማር ሂደት ተፅዕኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉ ይገልፃሉ፡፡ አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማር ተማሪ የስነልቦና ሁኔታው ቋንቋውን በመናገር ወይም በመፃፍ ሂደት ላይ ስህተት እንዲፈፅም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ የሚኖራቸው አመለካከት ከቤተሰቦቻቸው ሊወርሱ እንደሚችሉ ምሁራን ጨምረው ይጠቁማሉ፡፡ በመሆኑም ወላጆች ለታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች ያላቸው አወንታዊም ሆነ አሉታዊ አመለካከት በልጆቻቸው ላይ ሊንፀባረቅባቸው እንደሚችል እንረዳለን፡፡ ተማሪው ለሚማረው ቋንቋ የሚኖረው አወንታዊ አመለካከት ቋንቋውን በፍላጎት እንዲከታተለው ሊያደርግ ሲችል በተቃራኒ ተማሪው ለቋንቋው የሚኖረው አሉታዊ አመለካከት ደግሞ ተማሪው ቋንቋውን እንዲጠላውና የመማር ፍላጎቱን እንዲያጣ ያደርገዋል፡፡ ይህንን Ellis (1994) እና MC Groarty (1996) የተለያዩ ጥናቶችን ዋቢ አድርገው ሲያብራራ ለሚማሩት ቋንቋ ተነሳሽነትና አወንታዊ አመለካከት የነበራቸው ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ውጤታማ መሆን ሲችሉ በሌላ በኩል ደግሞ ለታላሚው ቋንቋ አሉታዊ አመለካከት የነበራቸው ተማሪዎች ውጤታማ አልነበሩም፡፡ ለቋንቋው አሉታዊ አመለካከት ያለው ተማሪ ተነሳሽነቱ ዝቅተኛ ስለሚሆን ሃሳቡን በፅሁፍ ለመግለፅ በሚሞክርበት ጊዜ ስህተት እንዲፈፅም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

ሌላው የተለያዩ የቋንቋ ምሁራን ስለስህተት ምንጮች በሚጠየቁበት ጊዜ የሚሰጧቸው መልሶች ተቀራራቢነት ያላቸው ቢሆንም አንዳንዶቹ ከተማሪዎቹ ግዴለሽነት የሚመጣ ነው ማለታቸውንም Norrish ገልፀውታል፡፡ ሆኖም እንደ Norrish አባባል ግዴለሽነት ብቻውን ለስህተት መፈጠር ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ ይሁን እንጂ መምህራን ተማሪዎቻቸው ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች ምክንያት እንደሆነ አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ ግዴለሽነት ለመማር ካለፍላጎት መቀስቀስ ጋር በቀጥታ ይገናኛል፡፡ ይህም የፍላጎት ማጣት ምናልባትም የትምህርቱ አቀራረብ ወይም ደግሞ ለትምህርቱ የቀረበው ነገር ከተማሪው ጋር ባለመስማማቱ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ

በግዴለሽነት የሚፈፀመውን ስህተት ለመቀነስ ከሚያስችለውም መንገድ አንዱ የእርስ በርስ እርማት ማካሄድ እንደሆነና የዚህ አይነቱ የአስተራረም መንገድም ስህተቶችን የመመርመር ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንደሚሆን Norrish ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ የቋንቋው ተማሪ ከበርካታ ውጫዊና ውስጣዊ ተፅዕኖ የተነሳ ስህተት ሊፈፅም እንደሚችል ልንገነዘብ እንችላለን፡፡ ይኸውም ከአፍ መፍቻ የቃላትና የመዋቅር ተፅዕኖ የተነሳ ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ ታላሚውን ቋንቋ ለተግባቦታዊ ተግባር ለመጠቀም ሙከራ በሚያደርግበት ጊዜ የቋንቋውን ስርዓት በተሳሳተ ሁኔታ ከመጠቀም ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ የተማሪው ስነልቦናዊ ሁኔታዎች ለስህተቶች መፈጠር አይነተኛ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

## 2.4. የስህተት ትንተና ዘዴዎች

የስህተት ትንተና ለማካሄድ እስከ አሁን ድረስ ወጥነት ያለው ዘዴ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በትንተናው ዙሪያ በጣም ብዙ የስህተት አይነቶች በመፈጠራቸው የተነሳ የስልቶቹን አይነት በመመደቡ ላይ ልዩነቶች እየሰፉ መጥተዋል፤ በዚህም የስህተት ትንተናን ትልቅ እንቅፋት አጋጥሞታል (Lott 1983:256)፡፡ ይሁን እንጂ በብዙዎች ዘንድ በሰፊው የሚሰራባቸው የስህተት ትንተና ዘዴዎች እንዳሉ Dulay et.al. (1982:146-197) ያስረዳሉ፡፡ እነሱም የስነ-ልሳናዊ ክፍሎችን መሰረት ያደረገ፣ የዓረፍተ ነገር ላዕላይ መዋቅርን መሰረት ያደረገ፣ ንፅፅራዊ ክፍልን መሰረት ያደረገና ተግባቦትን መሰረት ያደረገ ሲሆን እንደሚከለተው በዝርዝር ይቀርባሉ፡፡

### 2.4.1. የስነ ልሳን ክፍሎችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል

በርካታ የስህተት ትንተና ዘዴዎች በስነልሳናዊ የመዋቅር ክፍሎች ላይ ተመስርተው የተጠኑ ናቸው፡፡ ጥናታቸውም በአንዱ ስነልሳናዊ ክፍል ወይም በተወሰኑት አሊያም በሁሉም ላይ ሊያተኩር ይችላል፡፡ የስህተት ትንተናው በስነ ድምፅ፣ በስነ መዋቅር፣ በቃላት፣ በስነ-አገባብ ፍቺ እና የዲስኩር ጠቋሚዎች ላይ ሊያተኩር ይችላል፡፡ በዚህ ዘዴ ስህተቶችን ለመተንተን የሚፈልግ አጥኚ ስህተቶችን ከለቀመና ከሰበሰበ በኋላ እንደ ስህተቱ አይነት በተለያየ ስነ ልሳናዊ ምድብ ውስጥ እያስቀመጠ ይተነትናል፡፡ በርካታ አጥኚዎችም ስህተቶችን በስነልሳናዊ መዋቅሮች በመከፋፈልና በመተንተን

ውጤታቸውን ይፋ ለማድረግ ተጠቅመውበታል። አንዳንዶቹም አጥኚዎች ይህን ዘዴ እንደ ብቸኛ የስህተት መተንተኛ ስልት ይቆጥሩታል። በዚህ ዘዴ አጥኚው አስቀድሞ ለማጥናት ካቀዳቸው የስህተት አይነቶች ውጭ ለሆኑ ስህተቶች ትኩረት አይሰጥም (Dulay et.a. 1982:146-150)።

## 2.4.2. የዓረፍተ ነገር ቅርፆችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል

በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት ውስጥ ተማሪዎች የሚፅፏቸውን ዓረፍተ ነገሮች ውጫዊ ቅርፅ ስንመለከት የተለያዩ አይነት ስህተቶች ያሉባቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ተማሪዎች አስፈላጊ የሆነ ዓረፍተ ነገር አካልን ሊገድፉ ወይም የማያስፈልጉትን ሊጨምሩ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ የቋንቋውን ቅርፅ አላግባብ ሊያስፍሩ፣ አንዱን የዓረፍተ ነገር አካል ከሌላው በማስቀደም ቅደም ተከተል ሊያዛቡ፣ ለአንድ አገልግሎት ለምሳሌ ለእምርነት ሁለት ምልክቶች ሊጠቀሙ ወዘተ… ይችላሉ። በመሆኑም ይህ አይነቱ የስህተት አከፋፈል ዘዴ በዓረፍተ ነገር ውጫዊ መዋቅር ላይ የሚታዩ ስህተቶችን ይመለከታል። ይህ ዘዴ አንድን አዲስ ቋንቋ ወይም ሁለተኛ ቋንቋ ለመማር ተማሪው በምን አይነት አእምሮአዊ ሂደት ውስጥ እንደሚያልፍና ቋንቋው ምን አይነት መንገድ ተጠቅሞ እየለመደው (እየተማረው) እንዳለ የሚጠቁም መረጃ ለመስጠት ከማገልገሉም በላይ ተማሪው በሚማረው ቋንቋ ላይ የሚፈፅማቸው ስህተቶች ይብዛም ይነስም የተወሰነ ተጠይቃዊ አካሄድ ላይ የሚመሰረት እንደሆነ እንድንገነዘብ ያስችለናል።

በዓረፍተ ነገር ላዕላይ ቅርፅ ላይ የሚመሰረት የስህተት ትንተና ዘዴ መነሻው ተማሪዎች በሚፅፏቸው ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ናቸው ይህንን ዘዴ በስነልሳናዊ መዋቅር ላይ ተመስርቶ ከሚተነተነው የስህተት አከፋፈል ዘዴ የሚለየው አጥኚው ተማሪዎቹ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች ከማየቱ በፊት ስህተቶችን ለመመደብ የሚያስችለው የስህተት ምድቦች ባለመኖራቸው የተነሳ ነው። በመሆኑም በዚህ የስህተት አከፋፈልና አተናተን ዘዴ አጥኚው ስህተቶቹን የሚመድበው ተማሪዎቹ የፈፀሟቸውን ስህተቶች መሰረት በማድረግ ነው (Dulay et.al. 1982:150-162)።

### 2.4.3. ንፅፅራዊ ክፍፍል

ንፅፅራዊ ትንተና መሰረት የሚያደርገው የስህተት ትንተና ዘዴ የሚያተኩረው በታላሚው ቋንቋ አፈፊትና በታላሚው ቋንቋ ኢ-አፈፊት የሆኑ ተማሪዎች በቋንቋ ለመዳ እና መማር ሂደት የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች በማነፃፀር ላይ ነው፡፡ ይህንንም Dulay etal (1982) በምሳሌ ሲያብራራ አፉን በኮሪያ ቋንቋ የፈታ ሰው እንግሊዘኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ሲማር የሚፈፅመው ስህተትና እንግሊዘኛን በአፍ መፍቻ ቋንቋነት እየለመደ ያለ ህፃን ልጅ የሚፈፅማቸውን ስህተቶች በማነፃፀር ለመተንተን ሙከራ ሲደረግ በንፅፅራዊ ትንተና ላይ የተመሰረተ የስህተት አከፋፈል ዘዴ መተግበር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህ የስህተት አከፋፈል ዘዴ አማካኝነትም በታላሚው ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ህፃናት የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ታላሚውን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ከሚፈፅሟቸው ጋር በምን እንደሚመሳሰሉና በምንስ እንደሚለያዩ ጥናት ያደርጋል፡፡ በጥናቱ ሂደትም ኢ-አፈፊቱ ታላሚውን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት በመማር ሂደት ላይ የሚፈፅማቸውን ስህተቶች በመተንተን ኢ-አፈፊቱ ተማሪ ያጋጠመው ችግር የአፍ መፍቻ ቋንቋው ጣልቃገብነት አልያም ደግሞ በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት ውጤት መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል (Dulay etal 1982:163-172)፡፡

### 2.4.4. ተግባቦታዊ ተፅዕኖ መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል

በዚህ ዘዴ ስህተቶች የሚከፋፈሉት ተግባቦትን ከማወካቸው አንፃር ነው፡፡ በንፅፅራዊ ትንተና እና በዓረፍተ ነገር ላዕላይ መዋቅር ላይ የተመሰረቱ የስህተት ክፍፍሎች በራሳቸው በስህተቶች ገፅታ ላይ የሚያተኩሩ ሲሆኑ ተግባቦትን መሰረት በማድረግ የሚከፈሉት ስህተቶች ግን የሚያተኩሩት ከተግባቦት አኳያ አንባቢው ወይም አድማጩ መልዕክቱን በትክክል ከመረዳት ወይም ካለመረዳት አንፃር ነው፡፡ ይኸውም ተማሪው የሚናገራቸውን ሃሳቦች አድማጩ የማይረዳቸው ከሆነና ግልፅነት ከጎደላቸው የተግባቦቱ ሂደት ሊደናቀፍ ይችላል፡፡ በመሆኑም ይህ የስህተት አከፋፈል ዘዴ የሚያተኩረው ተግባቦትን የሚያደናቅፉትንና የማያደናቅፉትን ስህተቶች ለይቶ በመተንተን ላይ ነው፡፡ በዚህ የስህተት አከፋፈል ዘዴ የትኞቹ ስህተቶች ናቸው አድማጩ መልዕክቱን እንዳይረዳ እንቅፋት የሆኑበት? የሚለው ጥያቄ አብይና

መሰረታዊ ጥያቄ ነው። በመሆኑም Norrish (1992፡80) እንደሚገልፁት የስህተት ትንተና ለማድረግ ሁለት አበይት ዘዴዎች አሉ። የመጀመሪያው እና በጣም የተለመደው ተማሪዎች ይሰሯቸዋል ተብለው የሚገመቱትን የስህተት አይነቶች አስቀድሞ በመመደብ ስህተቶችን በየምድባቸው የማስራጨት ዘዴ ሲሆን ሁለተኛው በተማሪዎች የተሰሯቸውን ስህተቶች መሰረት አድርጎ የስህተት አይነቶችን መበየን ነው።

በመጀመሪያ ዘዴ የስህተት አይነቶች አስቀድመው የተመደቡ በመሆናቸው ተማሪዎቹ የሰሯቸውን ስህተቶች በየምድቡ በመክተት ለመተንተን ስለሚሞከር ለአሰራር ቀላል ነው። ይሁን እንጂ ይህ ዘዴ ስህተቶቹ በሚያሳዩት በራሳቸው ባህርይ ለመከፋፈል አለመቻሉ ደካማ ጎኑ ነው። በሁለተኛው ዘዴ የስህተት አይነቶቹ በስህተቶቹ መሰረትነት የሚመሰረቱ ስለሆነ ከመጀመሪያው ዘዴ የተሻለ ነው፤ ሆኖም ረጅም ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ ለአሰራር አስቸጋሪ ነው (Norrish 1992፡81-92)።

ከፍ ሲል የቀረቡትን አራቱን የስህተት አተናተን ዘዴዎችን በውስጡ ባጠቃለለ መልኩ (Norrish 1992፡81-91) የስህተት አከፋፈልን ከሁለት አብይት ክፍሎች ከፍለው እናገኛቸዋለን ይኸውም ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴና የተፈፀሙ ስህተቶችን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ ናቸው።

### ሀ. ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ

ይህ የስህተት አከፋፈል ዘዴ ተማሪው በአብዛኛው ሊፈፅማቸው ይችላል ተብለው በሚታሰቡት ስህተቶች ላይ በመመስረት የስህተት ትንተናው የሚካሄድበት ስልት ነው። በዘዴው የስህተቶቹ አይነት አስቀድሞ የተወሰነ በመሆኑ በተማሪው ድርሰት ውስጥ የታዩት ስህተቶች በተወሰነላቸው ምድብ ውስጥ ይካተታሉ አስቀድሞ በተወሰነላቸው ምድቦች ውስጥ ስህተቶቹን መፈረጅ ቀላልና ጊዜ ቆጣቢ በመሆኑ ዘዴውን ቀልጣፋ እንዲሆን አድርጎታል።

### ለ. ስህተቶችን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ

የዚህ ዘዴ ዋነኛ መሰረቶቹ በተማሪዎቹ የሚፈፀሙ የተለያዩ ስህተቶች ናቸው። ይህ ዘዴ ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ካደረጉ የስህተት አከፋፈል ዘዴ በተነፃፃሪ ስህተቶቹ

እራሳቸው የስህተት ምድባቸውን እንዲወስኑ የሚደረግበት አሰራር ነው። ዘዴው Hudson (1971) በተባለ ምሁር ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተገበረ የሚነገር ሲሆን ስህተቶችን በአይነታቸው ለመለየት ካርድን እንደ ጥሩ መሳሪያ ይጠቀምበታል። በመጀመሪያ እያንዳንዱ ስህተት በካርዱ ላይ ይመዘገባል። በማስከተልም ካርዶቹ እንደያዙት የስህተት አይነት በየክፍሎቻቸው ይመደባሉ። ክፍሎቹ ባላቸው ተመሳሳይነት አንዱ በሌላው ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል። እንደዚህ እየተደረገ በተቻለ መጠን ስህተቶቹን በአነስተኛ ምድብ ውስጥ ለማጠቃለል ይሞከራል። ከዚያም እንደሚያሳዩት ባህሪይ ትንታኔው ይካሄዳል። ይህ አቀራረብ ይበልጥ ለፅሁፍ ቋንቋ ተስማሚ ነው Norrish (1992፡83-86)።

## 2.5. የስህተት ትንተና ጠቀሜታ

ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት መሳካትም ሆነ አለመሳካት የስህተት ትንተና የሚሰጠው ጠቀሜታ በጣም ከፍተኛ ነው። እንዲሁም በተማሪዎች ድርሰት ላይ የስህተት ትንተና ማካሄድ በርካታ ስነትምህርታዊ ፋይዳዎች እንዳሉት ምሁራን ይገልፃሉ። የስህተት ትንተና ማካሄድ ታላሚውን ቋንቋ በመማር ማስተማሩ ሂደት እንደ አቅጣጫ ጠቋሚ መሳሪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

ይህንን ሀሳብ Lott (1983፡256) የስህተት ትንተና ለመምህራን የተማሪዎቻቸውን ስህተቶች እንዴት መተንተን እንደሚችሉ ቴክኒኮችን በማቅረብ በኩል ጠቀሜታ ያለው ስራ እንደሆነ ይገልፃሉ ሌላው የስህተት ትንተና ከዚህ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች እንደሚያስገኝ Lott (1983: 256)፣ Jackson (1987:102)፣ Richards (1974:25)፣ Dulay et.al. (1982: 138-139) እና Sharma (1986:76-77) ገልፀዋል። ጠቀሜታዎቹም ተማሪዎቹ በታላሚው ቋንቋ ያላቸው እውቀት ምን ያህል እንደሆነና ጠንክረው ቢሰሩ የትኞቹን ስህተቶች በቀላሉ እንደሚያስወግዱ እንደዚሁም የትኛው የታላሚው ቋንቋ ክፍል ላይ ትኩረት ሰጥተው መለማመድ እንዳለባቸው ሊጠቁም ይችላል። በአንድ ክፍል ውስጥ በተለያዩ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ቢኖሩ የጋራ ስህተታቸው የትኛው እንደሆነ በአንዱ ቋንቋ አፉን የፈታ ተማሪ ከሌሎቹ የተለየ የሚፈፅመው ስህተት ካለ የትኛው አይነት ስህተት እንደሚፈፅም እና የስህተቱ ምንጭ ምን እንደሆነ ለመረዳት ይጠቅማል።

በመምህራንና በስርዓተ ትምህርት ቀራጮች እንዲሁም በትምህርት መሳሪያ አዘጋጆች በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው ይፈፀማል ተብለው ያልተገመቱ ስህተቶች ቢፈፀሙ የተፈፀሙበትን ምክንያት አግኝቶ መፍትሔ ለማፈላለግ ይረዳል፡፡ የስህተት ትንተና ተማሪዎች በሚማሩበት ቋንቋ የደረሱበትን ደረጃ ፍንትው አድርጎ ከማሳየቱም በላይ በየደረጃው የትኞቹን ስህተቶች መቅረፍ እንደሚቻል በቶሎ መወገድ ያለባቸውና እያደር የሚፈጠሩትን ስህተቶች ለመለየት ያስችላል፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በእድሜና በክፍል ደረጃቸው መጠን የሚሰሩት ስህተትም ይለያያል፡፡ የስድስት ዓመት ልጅ የሚሰራው ስህተት ከሰላሳ ዓመቱ ይለያል፡፡ ይህንንም ለመረዳት የስህተት ትንተና ያስፈልጋል፡፡

በስህተት ትንተና ተማሪዎች የትኞቹን የታላሚ ቋንቋ ክፍሎች እንደሚሳሳቱ ለማወቅ ይቻላል፡፡ ሁሉም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በጋራ የሚሳሳቷቸው የትኞቹን የታላሚው ቋንቋ ክፍሎች እንደሆኑ ለማወቅ ያስችላል፡፡ በተወሰነ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ከሌሎች ተለይተው ስህተት የሚፈፀሙባቸው የቋንቋ ክፍሎች አሉ፡፡ ስህተቶቹ ስነድምፃዊ፣ ስነምላዳዊ፣ ስነአገባባዊ ናቸው ወይስ ሌላ? የሚሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

የስህተት ትንተና የቋንቋ ትምህርቱ ከቀረበ በኋላ ብቻ የሚከናወን ጉዳይ አይደለም፡፡ በማንኛውም ጊዜ ሊካሄድ ይችላል፡፡ ይህንንም ሀሳብ Sharma (1979:77) ሲያብራሩ የቋንቋ መምህሩ ትምህርቱን ከመጀመሩ በፊት ትምህርቱን እያስተማረ ማለት የመማር ማስተማሩ ሂደት እየተካሄደ አሊያም ከቋንቋ ትምህርቱ በኋላ የስህተት ትንተና በማካሄድ የትምህርቱን አቀራረብ ሊገመግም ማሻሻያ ሊያደርግና የመፍትሄ ሀሳብ ሊያፈላልግ ይችላል፡፡

የስህተት ትንተና ለመምህሩ የሚሰጠው ጥቅም ቀላል እንዳልሆነ Corder (1973:25) ሲገልፁ ለመምህሩ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ችግሩ ጎልቶ የሚታይባቸውን የቋንቋ ይዘቶችን አውቆ ለመለየትና ከስህተቶቹ በመነሳት ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችለውን ዘዴ በመቀየስ የመፍትሄ ሀሳቦችን ለማፈላለግና እንዲሁም ለማስተማሪያ የሚጠቀምባቸውን የማስተማሪያ መሳሪያዎች ውጤታማነት እና ብቃት ለማረጋገጥ ስለሚረዳ መምህሩ ከስህተት ትንተና የሚያገኘው ጥቅም በትንሹ የሚገመት አይደለም፡፡ የስህተት ትንተና ለመምህሩ ከሚኖረው ፋይዳ በተጨማሪ ለቋንቋ

ተመራማሪዎችና መርሃ ትምህርት አዘጋጆች ከፍተኛ ጥቅም እንደሚሰጥ Corder (1973:257)፣ Norrish (1992:80) እና Lengo (1995:20-21) እንደሚከተለው ይገልፃሉ። ለቋንቋ ተመራማሪዎች አንድን ቋንቋ እንዴት መማር እንደሚቻልና ተማሪው ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት የሚጠቀምባቸውን ብልሃቶችንና ቅደም ተከተሎችን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት ይጠቅማል። በመርሃ ትምህርት ቀረፃ ላይ ለተሰማሩ ባለሙያዎች እና ለማስተማሪያ መሳሪያ አዘጋጆች መረጃ በመስጠት በመርሃ ትምህርት እና ማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ ለየትኞቹ ይዘቶች ቅድሚያ ተሰጥቶአቸው መደራጀት እንዳለባቸው መረጃ ይሰጣል።

የስህተት ትንተና ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት በመሆኑ በተማሪዎች የተለያዩ ቋንቋ የመማር ሂደት ላይ ትንተና ማካሄድ በእጅጉ ይጠቅማል።

ከላይ ከተገለፁት ነጥቦች በተጨማሪም በአንድ የትምህርት መርሀ ግብር መነሻ መካከልና መጨረሻ የስህተት ትንተና ማድረግ ጠቃሚነቱ የጐላ ነው በትምህርት መነሻ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ያላቸውን ዳራዊ እውቀት ለመረዳት በትመህርት መካከል የትምህርቱ ሂደት ምን ያህል በተገቢ ሁኔታ እየሄደ እንደሆነ በመገምገም በትምህርቱ መጨረሻ ተማሪዎቹ የትምህርቱ ሂደት ያገኙትን እውቀት እና የቀረፏቸውን ስህተቶች ለመገንዘብ ይጠቅማል። መምህራን በትምህርት መርሃ ግብሩ ሂደት የማስተማሪያ ዘዴያቸው ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነ እና የትኞቹን ተማሪዎች በምን አይነት መንገድ መርዳት እንደሚችሉ የስህተት ትንተናው ሊጠቁማቸው ይችላል። ከዚህም በተጨማሪ ምርምር ሊደረግባቸው የሚገቡ ነጥቦችንም ይጠቁማል።

### 2.6. በስህተት ትንተና ዙሪያ የተሠሩ ስራዎች

ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸውን ስህተት አስመልክቶ በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል። እነዚህ ለመጀመሪያና ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ጥናታዊ ፅሁፎች ሲሆኑ ከዚህ እንደሚከተለው ተቃኝተዋል።

ይልማ ከበደ (1956) ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን በፈቱ የ1ኛ ደረጃ ተማሪዎች ፅህፈት ላይ በሚታዩ ስህተቶች ጥናት

ባደረጉበት ጊዜ ተማሪዎቹ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች የሳልስና የሳድስ፣ የግዕዝና የሀምስን፣ ቦታ ማለዋወጥ፣ የመስተዋድዶችንና የተሳቢ ምልክቶችን አገባባቸውን አለማወቅ፣ የባለቤትና ግሶች አለመስማማት ስህተቶች እንደሆኑና የስህተቶቹ ምንጭም የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንደሆነ ጠቅሰው ከነዚያ ውጭ የሚፈፀሙ ሌሎች የስህተት አይነቶች ግን በራሡ በቋንቋ ውስጣዊ ባህሪይ ምክንያት ሊመጡ እንደሚችሉ ገልፀዋል፡፡

ደብሬ ተሰማ (1990) በኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረቡ ሲሆን ጥናቱ ያተኮረው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸውን ዋና ዋና የስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ውጤቱም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የማስተማር ብቃት ማነስና በቂ የፅሁፍ ልምምድ አለመኖር የስህተት ምንጮች እንደሆኑ ተመልክቷል፡፡

ተክሌ አስፋው (1989) አፋቸውን በመስቃንኛ የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሠት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች ያጠኑ ሲሆን ትኩረት ያደረጉት ሰዋሰዋዊ ስህተቶች ላይ ነው፡፡ የስህተት አይነቶቹ በሶስት የተከፈሉ ሲሆን እነርሱም ፅንሰ ሀሣባዊ ስህተቶችን፣ ጅምላ ጥቅልላዊ ስህተቶች እና እድገታዊ ስህተቶች ናቸው፡፡ ለስህተቶቹ ምንጭ የሚሆኑት መስቃንኛ ቋንቋ አማርኛ ቋንቋ እና ተማሪዎቹ የሚከተሏቸው ሞዴሎች እንደሆኑም ገልፀዋል፡፡

አማረ ሰውነት (1996) በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ ክፌል ተማሪዎች የሚፈፅሟቸው ስነ-ልሳናዊ ስህተቶች በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፍ አቅርበዋል፡፡ በጥናታዊ ፅሁፋቸው በትግርኛ አፈ-ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የተስተዋሉ ሰዋሰዋዊ ስህተቶች ከስነ ድምፅ፣ ከስነ ምዕላድ፣ ከስነ አገባብ፣ ከስነ ፍቺ አንፃር ተንትነዋል፡፡ በጥናቱ ውስጥ ለስህተት ምንጭ ይሆናሉ ተብለው የተጠቆሙት የስህተት ምንጮች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ተፅዕኖዎች፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎችና ስነ ዘዴዎች ድክመት ናቸው፡፡

ከአማረ ስራ ጋር በጣም ተቀራራቢነት ያለው ጥናት የዘውዱ ምልክት (1996) ነው፡፡ የዘውዱ ጥናት የሚያተኩረው በአዊኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ ክፈል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸውን ሰዋሰዋዊ ስህተቶች ላይ ነው፡፡ እነዚህ ሰዋሰዋዊ ስህተቶች የሰነ ድምፅ፣ የስነ ምዕላድ፣ የሀረጋት እና የዐ.ነገር አወቃቀር እንዲሁም የቃላት አጠቃቀምና ፍቺ ተብለው ተከፍለዋል፡፡ በጥናቱ ውስጥ ለስህተት ምንጭ ይሆናሉ ተብለው የታመነባቸውም አራት ናቸው፡፡ እነርሱም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የመማር ማስተማር ሂደት እና ስነልቦናዊ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

መሰሉ መንግስቱ (1991) የቸሀኛ አፈፈት ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ የሚያንፀባርቋቸውን ስነልሳናዊ ባህሪያት ያጠኑ ሲሆን የስህተት አይነተቶቹም በሁለት አበይት ክፍሎች ተከፍለዋል፡፡ ይኸውም ሰዋሰዋዊና ማህበራዊ የቋንቋ አጠቃቀም የሚሉ ናቸው፡፡ በሰዋስዋዊ ስህተቶችም ስነ-ድምፃዊ፣ ስነቃላዊ፣ ስነመዋቅራዊና፣ ስነትርጉማዊ ስህተቶች እንደሚገኙ ተመልክተዋል የስህተቱ ምንጮችም የአፍመፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ እና የታላሚ ቋንቋ ተፅዕኖ መሆናቸው ተገልፀዋል፡፡

አለማየሁ ፀጋዬ (1986) በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች መካከል በተወሰኑ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሠቶች ውስጥ የተፈፀሙ ስህተቶች ያጠኑ ሲሆን ውጤቱ እንደሚያሣየው በድርሰቶቹ ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም፣ በአይነት ለመፈረጅ የሚያስቸግሩ የፅንሠ ሃሳብ ግንዛቤ ስህተቶች ተከስተዋል ለነዚህ ስህተቶች ምንጭ ይሆናሉ ተብለው የተገመቱት የፅሁፍ ቋንቋ አጠቃቀምንና አወቃቀርን ደንብ አለማወቅ፣ ፅሀፈትን አለመለማመድ፣ አሉታዊ የመማር ማስተማር ዘዴ፣ እንዲሁም የፅንሠ ሃሳብ ግንዛቤ እንደሆኑ ተገልጿል፡፡

አብይ አሠፋ (1997) በአዲስ ከተማ ክፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በደብረ ሃይለ ቅዱስ ራጉኤል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸው በተማሪዎቹ ድርሠቶች ውስጥ የታዩ ስህተቶችን የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች፣ የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች፣ የስርአተ ነጥብ ስህተቶች፣ የዲስኩር

ስህተቶች እና የእውነታ ስህተቶች በሚል ፈርጀዋቸዋል፡፡ በተደረገው ትንታኔ ላይ ተማሪዎች ሲፈፅሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጮች ናቸው ተብለው የተገመቱት የመማር ማስተማሩ ሂደትና የስነ-ልቦና ችግሮች መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

ልዑልሰገድ አሠፋ (1997) በወላይትኛና ሲዳምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ በፃፏቸው ድርሰት ውስጥ የታዩ ስህተቶች ያጠኑ ሲሆን ትኩረት ያደረጉትም የስነ-ልሳናዊ ስህተቶች ላይ ሲሆን ይህንንም በአራት ክፍሎች በመክፈል ለማየት ሞክረዋል፡፡ ይኸውም በድምፅ ደረጃ፣ በቃላት ደረጃ፣ በሀረግ ደረጃ በዓረፍተ ነገር መዋቅር ደረጃ የተፈፀሙ ስህተቶች የሚሉ ናቸው፡፡ ለስህተቶቹ መፈጠር በምክንያትነት የቀረቡት የስህተት ምንጮችም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የማስተማሪያ ዘዴ ድክመትንና ስነልቦናዊ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

ተገኝ አህመድ (2000) አፋቸውን በከፋኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሠት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ትንተና በሚል ርዕስ በሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናታቸው በተማሪዎች ድርሠቶች ውስጥ የታዩ ስህተቶችን የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የፅንሠ ሃሳብ ግንዛቤ እና መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች በሚል ፈርጀዋቸዋል፡፡ በተደረገው ትንታኔ መሠረት ለስህተቶች መፈጠር ምክንያትነት የተዘረዘሩት የስህተት ምንጮችም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት፣ ውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የማስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት እና ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ተፅዕኖ ናቸው፡፡

እነዚህ ከላይ በዝርዝር የተቃኙት ሥራዎች ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ ለምን እንደሚሳሳቱ የስህተቶቻቸው አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ ጠቃሚ የመነሻ ሀሣብ ይሰጣሉ፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት የሀረማያ እና የአዴሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ በሚፈፅሟቸው ስህተቶች ላይ ማተኮሩ ከላይ ከተጠቀሱት ቀደምት ጥናቶች ጋር ይመሳሰላል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የሚለየው ተማሪዎቹ የአማርኛን ቋንቋ ትምህርትን ከአምስተኛ

ክፍል በሚጀምሩ ተማሪዎች ላይ በማተኮሩ ነው፡፡ አማርኛን ‹‹ሀ›› ብለው ከአምስተኛ ክፍል መጀመራቸው ደግሞ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ ተገቢ ያልሆነ የፊደላት አፃፃፍ፣ የቃላትና የሃሳብ ድግግሞሽ፣ የፆታ አለመስማማት፣ የባለቤትና የግስ አለመስማማት፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ችግር፣ የአረፍተ ነገርን ትክክለኛ አሰካክ ጠብቆ አለመፃፍና የሃሳብን ፍሰት አለመጠበቅ ወዘተ… ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በኦሮሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች በመዘርዘር የስህተት ምንጮችን በመመርመር የመፍትሄ ሃሳቦችን በመጠቆም ላይ ነው፡፡ ይህ ምዕራፍ ለጥናቱ አላማ መሳካትም አስፈላጊ የሆኑትን የትምህርት ቤቶቹን፣ የተማሪዎችንና የመምህራንን አመራረጥ ዘዴ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችንና የጥናቱን አተናተን ዘዴ ያቀርባል፡፡

### 3.1. የትምህርት ቤቶች አመራረጥ

ጥናቱ በምስራቅ ኦሮሚያ ከሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በሁለት ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኮረ ነው፤ እነዚህም ት/ቤቶች ሀሮማያና አደሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ናቸው፡፡ ትምህርት ቤቶቹ የተመረጡት በምቾት ናሙና /Convineine sampling/ ስልት ነው፡፡ የተመረጡበት ምክንያት ካለው የገንዘብ መጠን የጊዜ ጉዳይና የቦታ ርቀት ጋር በማጣጣም እና በዞኑ ከሚገኙ የተለያዩ የወረዳ ቀበሌዎች የሚመጡ ተማሪዎችን ከአንድ አካባቢ በቀላሉ ማግኘት ስለሚቻል ነው፡፡

### 3.2: የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የሚያተኩረው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ላይ በመሆኑ በቅድሚያ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ከሚማሩት ተማሪዎች መካከል በኦሮሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በነሲብ ናሙና ስልት ተለዩ፡፡ በዚህም መሰረት በሁለቱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ተጠኚ ተማሪዎች ትክክለኛ ቁጥር ታወቀ፤ ጥናቱ ባተኮረባቸው ትምህርት ቤቶች ከተገኙት 550 የኦሮሞኛ ቋንቋ አፍ ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል ድርሰቱን ለመፃፍም ሆነ የፅሁፍ መጠይቁን ለመሙላት 275 ተማሪዎች በነሲብ ናሙና ስልት ለጥናቱ ተመርጠዋል፡፡

### 3.3. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በጥናቱ ተሰታፊ የሚሆኑ መምህራንን ለመምረጥ ናሙና መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ስላልተገኘ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል ገብተው የሚያስተምሩ ሁሉም መምህራን (ብቁጥር አራት ናቸው) ተሳትፈዋል፡፡ እነኚህ መምህራን በሁለቱም ፈረቃ የሚሰሩ በመሆናቸው ሌላውንም ክፍል ማለትም 10፣11፣12ኛን እንደሚያስተምሩ ታውቋል፡፡

### 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን አለማ ያሳከሉ ተብለው የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የፅሁፍ መጠይቅና ድርስቶች ናቸው፡፡

#### 3.4.1. መጠይቅ

##### 3.4.1.1. የተማሪዎች መጠይቅ

በዚህ ጥናት ውስጥ መጠይቆች እንደ አንድ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተደርገው ተወስደዋል ምክንያቱም የድርስት መልመጃ ለሚገኘው ውጤት የድጋፍ ሀሳብ ስለሚሰጥ ነው፡፡ መጠይቆቹ ተዘጋጅተው በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ከተገመገሙ በኋላ የተሰጡትን አስተያየት በመቀበልና በማስተካከል ተጠኚ ተማሪዎች እንዲሞሉት ተደርጓል፡፡ ተማሪዎቹም መጠይቁን ከመሙላታቸው በፊት ስለአሞላሉ በዚህ ጥናት አቅራቢና በሚያስተምሯቸው መምህራኖች ገለፃ ተደርጎላቸዋል፡፡ ያልተረዱት ነገር ካለም እንደዲጠይቁ እድል ተሰጥቷቸዋል፡፡

መጠይቁ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጠይቁ የመጀመሪያው ገፅ የመጠይቁ አላማ የተገለፀበት ሲሆን የመጠይቁ የመጀመሪያው ክፍል ደግም የተጠኚ ተማሪዎችን. አጠቃላይ መረጃ የያዘ ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በምርጫ የሚመለሱ ጥያቄዎችን እንዲይዝ የተደረገ ነው፡፡ በዚህ ክፍል በምርጫ መልሶች የቀረቡትን ሀሳቦች በድጋሜ ለማረጋገጥ በማሰብ በአምስት የእስኬል ክፍሎች አማካይነት ማለትም በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ፣ በጣም ዝቅትኛ በማለት የሚመለሱ ጥያቄዎችን ይዟል፡፡

በክፍል ሶስት በፅህፈት ልምምዱ ወቅት ለተማሪው ችግር የሚፈጥሩትን ነገሮች የሚያጋጥሙትን የስህተት አይነቶችና ምንጮች እንዲሁም ስለትምህርቱ አጠቃላይ ሀሳብ እንዲሰጥበት በማሰብ በፅሁፍ የሚመለሱ ክፍት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

### 3.4.1.2. የመምህራን መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ አላማው መምህራን ፅህፈትን በተመለከተ ስለተማሪዎቹ ዳራ፣ መርሃ ትምህርቱና የመማሪያ መፅሀፉ የፅህፈት ክሂልን ለማዳበር ስላላቸው ጠቀሜታ፣ ስለመማር ማስተማሩ ሂደት፣ ተማሪዎቹ ለቋንቋው ስለሚኖራቸው አወንታዊም ሆነ አሉታዊ አመለካከት፣ በአጠቃላይ ስለስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጮችን መምህራን ያላቸውን አስተያየት ለማግኘት ነው፡፡ የመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ እንደተማሪዎቹ መጠይቅ በባለሙያ ከተገመገመ በኋላ አስተያየት ተሰጥቶበት ለጥናቱ እንዲያመች ተደርጎ ተሻሽሎ ቀርቧል፡፡

መጠይቁ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጠይቁ የመጀመሪያ ገፅ ላይ የመጠይቁ አላማ የተብራራበት ነው፡፡ በክፍል አንድ የመምህራኑን አጠቃላይ ማንነት በተመለከተ መረጃ ለማግኘት የተዘጋጀ ነው፡፡ በክፍል ሁለት ስለመማር ማስተማሩ ሂደት የተመለከቱ ጥያቄዎች እና የተማሪዎቹን የስህተት ምንጮች አስመልክቶ የምርጫ መልሶችን የያዙ ጥያቄዎች ሲኖሩ እነዚህንም በሌላ መንገድ ለማረጋገጥ አምስት የስኬል ደረጃዎች በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ፣ በጣም ዝቅተኛ ያሏቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በክፍል ሶስት ነፃ አስተያየት የሚሰጥት ክፍት ጥያቄ ቀርቦላቸዋል፡፡

### 3.4.2. ድርሰቶች

ለጥናቱ ይጠቅማል ተብለው ከታሰቡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አንዱ ድርሰት ነው፡፡ ድርሰቱ እንዲፃፍ ከመቅረቡ በፊት የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ፣ እድሜና ልምድ ባገናዘበ መልኩ ርዕስ ተዘጋጅቶ በትምህርት መስኩ ባለሙያዎች ተገምግሞ አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ መሻሻል የሚገባው ተሻሽሎ ቀርቧል፡፡

ድርሰቶቹ ነፃ የድርሰት አፃፃፍ (Free writng) ስልትን በመከተል የተፃፉ ሲሆኑ የመጀመሪያ ዙር የድርሰት መልመጃ ያለምንም ቅድመ ዝግጅት ክፍል ውስጥ

እንዲፅፉ ከተደረገ በኋላ የሁለተኛውን ዙር ድርሰት ደግሞ ከሳምንት በኋላ በአማራጭ ከቀረቡላቸው ርዕሶች መካከል በመረጡት ርዕስ ላይ ብቻ ተዘጋጅተው በመማሪያ ክፍል ውስጥ እንዲፅፉ ተደረገ። ድርሰቶቹ በቤት ስራ መልክ እንዳይሰሩ የተደረገው ተማሪዎቹ ሌሎች ሰዎችን አፅፈው ይመጣሉ ከሚል ስጋት ነው።

በመጀመሪያ ዙር 275 ድርሰቶች በሁለተኛ ዙር 200 ድርሰቶች 'በድምሩ 475 ድርሰቶች በክፍል ውስጥ እንዲፃፍ ተደርጓል። ድርሰቶቹን የማፃፍ ሂደት የተካሄደው በትምህርት ቤቱ የአማርኛ መምህራንና በአጥኚዋ የቅርብ ክትትል ነው። ይህ ሲሆን ግን መጀመሪያ ለተማሪዎቹ ግልፅ ያልሆነላቸውን ነገር እንዲጠይቁ ዕድል ተሰጥቷቸዋል። ግልፅ ላልሆነውም ጥያቄ ምላሽ ተሰጥቷል።

በተጠኚዎቹ የተፃፉት ድርሰቶች ለአራሚዎቹ ሲሰጡ በሶስት ቅጅ ተባዝተው ነው፤ አራሚዎቹ አማርኛን በማስተማር የረጅም ጊዜ ልምድ ያላቸው በሙያው የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸውና የሌላ ቋንቋ ተፅዕኖ የሌለባቸው ናቸው። ለእያንዳንዱ ድርሰት ውጤት የተሰጠው በአራሚዎቹ በግል የተሰጡት ነጥቦች ተደምረው ለሶስት እንዲካፈሉ በማድረግ ነው።

### 3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በፅሁፍ መጠይቅ እና በድርሰት አማካኝነት መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ቀሪው ስለመረጃዎቹ መተንተን በመሆኑ ትንታኔው ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

#### 3.5.1. የድርሰት መልመጃዎች አተናተን

ሁለት አበይት የስህተት መክፈያ ዘዴዎች እንዳሉ ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳን ውስጥ ለመግለጽ ተሞክሯል። እነሱም ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴና ስህተቶችን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ ናቸው Norrish (1992:81-91)። ከነዚህም ውስጥ አጥኚዋ ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴን ተጠቅማለች። በነዚህም መሰረት ስህተቶቹ እንደሚከተለው በቅደም ተከተል ቀርበዋል።

- በየገፁ ቃላቱን መቁጠርና ሁሉም ድርሰቶች የተፃፉባቸውን ቃላት በመደመር ጠቅላላ ድርሰቶቹ የተፃፉባቸውን ቃላት ብዛት ማወቅ
- የተገኙትን የቃላት ብዛት ተጠኚ ተማሪዎቹ ለፃፏቸው ድርሰቶች ቁጥር ማካፈልና እያንዳንዱ ድርሰት የተፃፈበትን አማካይ የቃላት መጠን ማግኘት
- በየድርሰቱ ውስጥ የተፈፀሙ ስህተቶችን መቁጠርና አጠቃላይ ስህተቶችን ብዛት ማወቅ
- በአጠቃላይ የተገኙ ስህተቶችን በአጠቃላይ ለተፃፈው የድርሰት ብዛት በማካፈል አማካይ ስህተቱን ማግኘት
- የስህተቶቹን መጠን በመቶ በማባዛት እና የተገኘውን ውጤት ድርሰቶቹ በተፃፉባቸው ቃላት መጠን በማካፈል በመቶ ቃላት ውስጥ ምን ያህል የስህተት ድግግሞሽ እንዳለ ማወቅ (Norrish 1992: 103-104)
- በመጨረሻም የስህተት ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ የተባሉትን ነገሮች ለመገመት የተከሰቱትን ስህተቶች በመመርመር አጥኚዋ ከላይ የተቀረበውን የ(Norrish 1992: 103-104) ስህተት አተናተን ስልት ተጠቅማለች፡፡

### 3.5.2. የመጠይቆች አተናተን

በክለሳ ድርሳን ውስጥ ከተቃኙ የውጭም ሆነ የሀገር ውስጥ ስራዎች እንዲሁም በተጠኚ ተማሪዎቹና በአማርኛ መምህራኑ የመጠይቅ ምላሾች ከተገኙት ሀሳቦች በመነሳት በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ ለፈጸሟቸው ስህተቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የስህተት ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ ሁሉ ተተንትነዋል፡፡ በነዚህ በተጠቀሱት መረጃዎች መሰረትም ዋና የስህተት ምንጭ ናቸው የተባሉት የሚከተሉት ናቸው፡-

- የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ
- የውስጥ ቋንቋ ተጽዕኖ
- የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶችና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት
- ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተናና ውጤት

### 4.1. መግቢያ

የዚህ ጥናት አላማ ተጠኚ ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚፈፀሙ ስህተቶችን መተንተን ሲሆን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የታቀደ መሆኑም በምዕራፍ አንድ ተገልጿል፡፡

- ተማሪዎቹ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸው የስህተት አይነቶች የትኞቹ ናቸው? የስህተቶቹስ መጠን ምን ያህል ነው? ድግግሞሻቸውስ ምን ያህል ነው? እና
- የስህተት ምንጮቹ ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

ለሚሉት የጥናት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ለጥናቱ የተመረጡ ተማሪዎች የፃፏቸው ድርሰቶች ተተንትነዋል፡፡

ተጠኚ ተማሪዎች ድርሰቱን በሁለት ዙር እንዲጽፉ የተደረገ ሲሆን በመጀመሪያው ዙር 275 በሁለተኛው ዙር ደግሞ 200 በአጠቃላይ 475 ድርሰቶችን ጽፈዋል፡፡ ተማሪዎቹ ድርሰቶቹን በሁለት ዙር እንዲጽፉ የተደረገበት ምክንያት በአንድ ጊዜ ብቻ በተፃፈ ድርሰት ስህተትን በስህተትነት ማስቀመጥ ትንሽ ከበድ ስለሚል ነው፡፡ ስህተቶችን በተመለከተ የቀረበው መረጃ በአጠቃላይ ድርሰቶችና ስህተቶች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ የተቆጠሩት የቃላት ብዛት የስህተት ብዛት ወዘተ በሚከተለው ሰንጠረዥ ለማመልከት ተሞክሯል፡፡

ሠንጠረዥ 1 ድርሰቶቹ የተፃፉባቸው የቃላት ብዛት የስህተት ብዛት መቶኛ፣ አማካይ ስህተትና የስህተት ድግግሞሽ

| የድርሰቱ አይነት | የድርሰቱ ብዛት | ድርሰቶቹ የተፃፉበት የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | መቶኛ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ድርሰት አንድ | 275 | 16275 | 59.18 | 9740 | 53.85 | 35.42 | 59.85 |
| ድርሰት ሁለት | 200 | 15092 | 75.46 | 8347 | 46.15 | 41.74 | 55.31 |
| ድርሰት አንድ እ ሁለት | 475 | 31367 | 66.03 | 18087 | 100 | 38.08 | 57.67 |

ከላይ በሰንጠረገዡ ለመግለፅ እንደተሞከረው ስህተቶቹ የተቆጠሩት ተጠኚ ተማሪዎች በሁለት ጊዜ በጻፏቸው 475 ድርሰቶች ውስጥ ነው፡፡ ድርሰቶቹ የተፃፉት 31,367 ቃላት ሲሆን አንድ ተማሪ ድርሰቶቹን ለመፃፍ በአማካይ 66.03% ቃላትን እንደተጠቀመ ከቀረበው መረጃ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ተማሪዎቹ በፃፉቸው 475 ድርሰቶች ውስጥ የተቆጠረው የስህተት ብዛት 18,087 ሲሆን በአንድ ድርሰት ውስጥ የተገኘው አማካይ ስህተትም 38.08% ነው፡፡ ስለሆነም ከ66.03% አማካይ ቃላት ውስጥ የተገኘው የስህተት ድግግሞሽ 57.6% መሆኑን ከመረጃው ለማወቅ ተችሏል፡፡

ድርሰቶቹ በሁለት ጊዜ የተፃፉ ቢሆንም እንኳን ሁለቱን ድርሰቶች ለማነፃፀር የታለመ ባለመሆኑ ልዩነቶቹን በተመለከተ ዝርዝር ጉዳዮችን ለማንሳትም ሆነ ለማየት አልተሞከረም ጥናቱ የሚያተኩረው ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በአጠቃላይ ድርሰቶችና ስህተቶች ላይ በመንተራስ ነው፡፡

እንዲሁም ለጥናቱ በተመረጡ መምህራን ተማሪዎች ከተሞሉ የፅሁፍ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተተንትነዋል፡፡

የተቀረው የምዕራፉ ክፍል በሁለት ንዑሳን ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን በመጀመሪያው ክፍል ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የፈፀሟቸው ስህተቶች በአይነታቸው

የተመደቡ ሲሆን የስህተት ብዛት በመቶኛ፣ አማካይ የስህተት መጠን እና ድግግሞሻቸውን የተመለከተበት ትንታኔ ነው፡፡ የምዕራፍ ሁለተኛው ክፍል ተጠኚ ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ለተፈፀሙት ስህተቶች በዋናነት የታሰቡ የስህተት ምንጮች የተገለፀበት ነው፡፡

## 4.2. በድርሰቶቹ ውስጥ የታዩ ዋና ዋና የስህተት አይነቶች

ተጠኚ ተማሪዎቹ ድርሰቶቹን ሲፅፏቸው በዋናነት የተተኮረባቸው የስህተት አይነቶች የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀምና የፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ስህተቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም በነዚህ ዋና ዋና የስህተት አይነት ምድቦች ውስጥ የተቆጠረ የስህተት ብዛት፣ መቶኛ፣ አማካይ የስህተት መጠን፣ እንዲሁም በመቶ ቃላት ውስጥ የተፈፀመው አማካይ ድግግሞሽ ቀጥሎ በሚቀርበው ሠንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ 2 በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ በዋና የስህተት አይነት ምድቦች ውስጥ የተፈፀሙት ስህተቶች ብዛት መቶኛ አማካይ ስህተት እና አማካይ የስህተት ድግግሞሽ

| የስህተት ዓይነት | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት ብዛት | በመቶኛ | አማካይ ስህተት% | የስህተት ድግግሞሽ% | የስህተት ብዛት | በመቶኛ | አማካይ ስህተት% | የስህተት ድግግሞሽ% | የስህተት ብዛት | በመቶኛ | አማካይ ስህተት% | የስህተት ድግግሞሽ% |
| የቋንቋ አጠቃቀም | 4055 | 41.63 | 14.74 | 24.91 | 3697 | 44.29 | 18.48 | 24.49 | 7752 | 42.86 | 16.32 | 24.72 |
| የቋንቋ አወቃቀር | 2115 | 21.71 | 7.69 | 12.99 | 1670 | 20.01 | 8.35 | 11.06 | 3785 | 20.93 | 7.97 | 12.07 |
| የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም | 2010 | 20.64 | 7.31 | 12.35 | 1750 | 20.96 | 8.75 | 11.59 | 3760 | 20.78 | 7.91 | 11.98 |
| የጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ | 1560 | 16.02 | 5.67 | 9.58 | 1230 | 14.73 | 6.15 | 8.15 | 2790 | 15.42 | 5.87 | 8.89 |
| ድምር | 9740 | 100 | 35.42 | 59.85 | 8347 | 100 | 41.73 | 55.30 | 18087 | 100 | 38.08 | 57.67 |

ከሰንጠረዡ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በሁለቱም ድርሰቶች ከፍተኛ ስህተት የተቆጠረው በቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ውስጥ ነው። ባጠቃላይ ከተፃፉት የስህተት አይነቶች መካከል 7752 ያህሉ ስህተቶች በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ የተቆጠሩ ናቸው። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 42.86% ነው። የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት አማካይ የስህተት መጠን 16.32% ሲሆን አማካይ የስህተት ድግግሞሹም 24.72% ሆኗል። ይህም በመቶ ቃላት ውስጥ የተገኘውን የስህተት ድግግሞሽ ያመለክታል።

ከቋንቋ አጠቃቀም ቀጥሎ ከፍተኛ የስህተት መጠን የተቆጠረው በዐረፍተ ነገር አወቃቀር የስህተት ምድብ ውስጥ ነው። በሁለቱም ዙር ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የተቆጠሩት አጠቃላይ ስህተቶች መካከል 3785 ያህል ስህተቶች የተቆጠሩ ሲሆን ይህም በመቶኛ ሲሰላ 20.93% ነው። አማካይ የስህተት መጠኑም 7.97 ነው አማካይ ድግግሞሹ ደግሞ 12.07% ሊሆን ችሏል።

ከዐረፍተ ነገር አወቃቀር ቀጥሎ ያለው ደግሞ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ነው። ከስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ጉድለት የተነሳ በርካታ ስህተቶች እንደተፈፀሙ በሰንጠረዡ ከቀረበው መረጃ ማየት ይቻላል። ባጠቃላይ በስህተትነት ከተቆጠሩት 3760 ያህሉ ስህተቶች የተቆጠሩት በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ ነው። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 20.78% ሲሆን አማካይ የስህተት መጠኑም 7.91% ነው። አማካይ የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 11.98% እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

የመጨረሻውን ደረጃ የያዘው የስህተት ምድብ በፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ላይ የታየው ሲሆን በጠቅላላው ከተቆጠሩት የስህተት መጠን 2790 ያህሉ ሊሸፍን ችሏል። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 15.42% ሲሆን አማካይ የስህተት መጠኑም 5.87% የስህተት ድግግሞሹ 8.89% ሆኗል።

ከላይ በሠንጠረዡ ውስጥ ከተቀመጡት መረጃዎች መካከል ማለትም ከአራቱ ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ቀዳሚውን ስፍራ ይዞ እናገኘዋለን ዝርዝሮቹን በቀጣዩ ክፍል ለማየት እንሞክራለን።

### 4.2.1. የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች

አለማየሁ (1986፡60) Cooper (1977)ን በመጥቀስ ሲያብራሩ ከመደበኛ የፅህፈት ስርአት ውጭ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ሃሳብን ከማስተላለፍ የሚገታ ብቻ ሳይሆን የመግባባት ሂደትን እንደሚያሰናክል ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ የቋንቋውን አጠቃቀም ስርአት አውቆ ሀሳብን ማስተላፍ የፅሁፍ ቋንቋ መሰረታዊ ባህሪይ መሆኑን አክለው ይናገራሉ፡፡

በዚህ የስህተት አይነት ውስጥ የተመደቡ ስህተቶች አይነትና ብዛት በሚከተለው ሰንጠረዥ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

## ሠንጠረዥ 3 የቋንቋ አጠቃቀም ንዑስ የስህተት አይነቶች

| የስህተት ዓይነት | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት ብዛት | መቶኛ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት ብዛት | መቶኛ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት ብዛት | መቶኛ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ |
| የቃላት አመራረጥ | 1207 | 12.39 | 4.38 | 7.40 | 1084 | 12.98 | 5.42 | 7.18 | 2291 | 12.66 | 4.82 | 7.29 |
| ድግግሞሽ | 781 | 8.02 | 2.84 | 4.79 | 751 | 8.99 | 2.75 | 3.64 | 1532 | 8.47 | 3.22 | 4.87 |
| ግድፈት | 721 | 7.40 | 2.62 | 4.43 | 601 | 7.20 | 3.00 | 3.97 | 1322 | 7.31 | 2.78 | 4.21 |
| ጭመራ | 680 | 6.98 | 2.47 | 4.17 | 689 | 8.25 | 3.44 | 4.56 | 1369 | 7.57 | 2.88 | 4.36 |
| ኢመደበኛ ቃላትና ሀረጋት | 666 | 6.84 | 2.42 | 4.09 | 572 | 6.85 | 2.86 | 3.79 | 1238 | 6.84 | 2.61 | 3.95 |
| ድምር | 4055 | 41.63 | 14.74 | 24.91 | 3697 | 44.29 | 18.48 | 24.49 | 7752 | 42.86 | 16.32 | 24.72 |

ከላይ ከሠንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው በቋንቋ አጠቃቀም ንዑሳን የስህተት አይነቶች ውስጥ የቃላት አመራረጥ ስህተት ከፍተኛውን ቁጥር ያስመዘገበ ሲሆን ድግግሞሽና ግድፈት ደግሞ ቀጣዩን ክፍል ሲይዙ ጭመራና ኢመደበኛ ቃላትና ሀረጋት የመጨረሻውን ደረጃ ይዘው ይገኛሉ፡፡

### 4.2.1.1. የቃላት አመራረጥ ስህተቶች

አንድ ሃሳብ ሊተላለፍ የሚችለው በቃላት አማካይነት በመሆኑ አንድ ፀሀፊ ለማስተላለፍ የሚፈልገውን ጉዳይ ለመግለፅ የሚያስችሉ ቃላት በመምረጥ በተገቢው አውደ ንባብ በመጠቀም አላስፈላጊ ተደጋጋሚነትንና በሌላ ቋንቋ ተፅዕኖ ምክንያት የሚገቡ ቃላትን በማስቀረት የቃላት አደራደር ቅደም ተከተልን በመጠበቅ ሃሳቡን በማያሻማና ግልፅ በሆነ መንገድ ሲያቀርብ ከታለመው የመግባባት ግብ ሊደርስ ይችላል፡፡ ነገር ግን ቃላትን በአግባቡ ካልተጠቀመ ለማስተላለፍ የተፈለገው ሃሳብ ተድበስብሶ ሊቀር ይችላል ምክንያቱም፣ አንባቢው ግልፅ ያልሆነለትን ነገር ከፀሀፊው ጠይቆ መልስ ማግኘት አይችልም (Raimes 1991፡7)፡፡

ከላይ በሠንጠረዡ ለመግለፅ እንደተሞከረው ተጠኚ ተማሪዎቹ ትክክለኛና ተገቢ ቃላትን ባለመጠቀማቸው ስህተት እንደሚፈፅሙ ነው፡፡ ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በአጠቃላይ ከተፈፀሙት 18087 ስህተቶች መካከል 2291 ያህሉ የተቆጠረው በዚሁ የስህተት ምድብ ውስጥ ነው፡፡ የስህተት መቶኛውም 12.66% ሲሆን አማካይ የስህተት መጠኑ ከአጠቃላዩ የስህተት አማካይ 38.08% ውስጥ 4.82% ሊሆን ችሏል፡፡ በአጠቃላይ ድርሰቱ ከተቆጠሩት 57.67% ድግግሞሽ ውስጥ 7.29% ያህሉ በዚህ ውስጥ የተቆጠረ በመሆኑ ከንዑሳን የስህተት አይነቶች ውስጥ የመጀመሪያውን ቦታ ይዞ ይገኛል፡፡

በቃላት አጠቃቀም ሂደት የተፈፀሙት ስህተቶች አብዛኞቹ ሃሳብን በቀጥታና ግልፅ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ የሚያስችሉ ተገቢ ቃላትን ካለመጠቀም ተቀራራቢ ፍቺ ያላቸውን ቃላት ለመጠቀም ሲሞክሩ የተፈፀሙና ቃላትን በተሳሳተ መንገድ ሲገለገሉባቸው የተፈፀሙ ናቸው፡፡

1. ተገቢ ቃላትን ካለመጠቀም የተነሳ የተፈፀሙ ስህተቶች

ተጠኚዎቹ ሀሳባቸውን በግልፅ ለማስተላለፍ የሚያስችላቸውን ተገቢና ትክክለኛ ቃላትን በአግባቡ ካለመጠቀም የተነሳ በርካታ ስህተቶችን ፈፅመዋል፣ ስለሆነም ከአረፍተ ነገሩ አውድ ጋር የሚዛመዱ ተገቢ ያልሆኑ ቃላትን በመጠቀም ሀሳባቸውን በሌላ ቃል ወይም ሀረግ

ለመግለፅ ሲሞክሩ የተፈፀሙ ስህተቶች ተስተውለዋል። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች እንመልከት፤

- ቲሚርት የሚጠቅመው ጥሩ ኑሮ <u>በመጀመሪያ ለራስ ይጠቅማል</u>
- ያልተማሬ ሰው ላቦራቶሪ ውሲጥ ቢገባ የትኛው <u>ጎጀ</u> ነው የትኛው <u>ጥቅም</u> ነው።
- <u>አንዳንዱ</u> አባቶች <u>የትማረ የትድረስ</u> .......
- ትምህርት ለብዙ ነገር <u>ጥቅም አለው።</u>
- የኢትዮጵያ ሰው በሙሉ ከምግብ <u>ቀርቶ</u> ለጫት ያሌው አመለካከት <u>ሶፋ ስፍራ</u> የሚወስዱበት ነው።

ከላይ ከተሰጡት ምሳሌዎች መገንዘብ የተቻለው ተማሪዎቹ በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈልጉትን ሀሳብ ለማስተላለፍ የሚያስችሉ ቃላትን ለመጠቀም ካለመቻላቸው የተነሳ የተፈጠሩ ስህተቶች ይመስላሉ። በመጀመሪያ የቀረበው ምሳሌ ‹‹ትምህርት የሚጠቅመው በመጀመሪያ ራስን ጥሩ ኑሮ ለማኖር ነው›› ለማለት ተፈልጎ ‹‹ትምህርት የሚጠቅመው ጥሩ ኑሮ በመጀመሪያ ለራስ ይጠቅማል›› በማለት ገልፆታል። ሌላው ‹‹ያልተማረ ሰው ላቦራቶሪ ውስጥ ቢገባ የትኛው <u>ጎጀ</u> ነው የትኛው ጥቅም ነው። ‹‹ያልተማረ ሰው ላብራቶሪ ውስጥ ቢገባ የትኛው ጎጂ የትኛው ጠቃሚ እንደሆነ ስማያውቅ ዝም ብሎ ቢነካካ ብዙ ጉዳት ሊደርስበት ይችላል ለማለት ተፈልጎ የቀረበ ይመስላል። ‹‹አንዳንድ አባቶች የትማረ የት ድረሰ ....›› የሚለው ደግሞ አንዳንድ አባቶች ሲተርቱ የተማረ የት ደረሰ ለማለት ተፈልጎ የቀረበ ነው። ‹‹ትምህርት ለብዙ ነገር ጥቅም አለው። ‹‹ትምህርት ለብዙ ነገር ይጠቅማል›› ለማለት ነው።
‹‹የኢትዮጵያ ሰው በሙሉ ከምግብ ቀርቶ በጫት ያለው አመለካከት ሶፋ ስፍራ የሚወስዱበት ነው›› የሚለው በኢትዮጵያ የሚኖሩ ሰዎች በሙሉ ለጫት ያላቸው አመለካከት ከምግብ ይበልጣል ለማለት የተፈለገ ይመስላል። እንደዚህ ከሆነ ደግሞ ‹‹ኢትዮጵያኖች በሙሉ ከምግብ ይልቅ ለጫት ያላቸው አመለካከት ሰፋ ያለ ነው›› ቢባል ይሻል ይሆናል።

በአጠቃለይ ከላይ በምሳሌ ያየናቸው የተሰመረባቸው ቃላት ተገቢ ካለመሆናቸው የተነሳ ስህተት ተፈፅሟል።

2. ሌላው በዚህ ክፍል የታየው ስህተት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ አማካኝነት ቃላትን በተሳሳተ መንገድ የመጠቀም ጉዳይ ነው። ለምሳሌ የሚከተሉትን አገላለፆች እንመልከት፤
   - በድህነት <u>ላሉ</u> ሰዎች መርዳት ቤተሰብ <u>አልቦ</u> ለሆኑ <u>ሊጀች መሪዳት</u>
   - አንድ አንድ ሰዎች ግን <u>ጥቂሙን ሲላል አውቆ</u> <u>ቲምህርት</u> ምን ያደርጋል ቢሎ <u>ከየተማሩ ያቋርጧሉ</u> <u>ኢና</u> ሌላ <u>ሲራ ትጀሚራሉች</u>

- የትምህርት ጥቅም ያወቀ ሀገራ ተጠቂሞበት በተግባር ሲራ ላይ አውሳ በልጽጎዋል፡፡
- ጫት ባትራምዶ ሀይል ሰጪኔት እፅዋት ይመዴባል ይህ ዕፅዋት ለ.ኪ. እንዴ ቡና ሁሉ አካል በማንቆቅ ተጨማሪ ሀይል በሰውነት እንዲከብት ይደረጋል፡፡
- ኢኔ መሆን የሚፈልገው ሳይንቲስትን ነው
- የትምህርት ጥቅምን ትንአግርም አልጨርስም ግን የትምህርት ጥቅም በጥም በዘ ነው፡፡ ትምህርት በጥም አስፍልግ ጥቅም ነው፡፡
- ‹‹… ቲሚርት ተሚሬ በሚገባ አጢኒቼ ዩኒቨርሲቲን ግቦቼ ከዚያም በፈለኩት ሙያ ተመርቂ ኢናት ሀገሬን አኮርቼ .....
- .... ባለፈው አሜታት ማሌትም በደርግ ግዘ እንዲዚያውም በሃይለስላሴ ዘመን ኢትዮፓያ በጣም ቺጊር ውስጥ ነበረ
- .... ሴቶች እንደዜ ያለው ቺጊር ውስጥ ገብቶ ከሚሴቃይ በቲሚርታቸው ጥሩ ውጤት አሚጥተው የባል እጅ ከመጠበቅ ኢነሡም ሴርተው እንዴገቡ ምኞቴ ነው፡፡

ከላይ በምሳሌው የቀረቡት ስህተቶች በሚታዩበት ጊዜ የኦሮሞኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ተጠኚ ተማሪዎች ሳልስና ሳድስን፣ ግዕዝና ራብእን ሀምስና ግዕዝን ‹‹እ›› ና ‹‹ይ››ን ወዘተ እያለዋወጡ በመጠቀማቸው የተነሳ የተከሰቱ ናቸው፡፡ በኦሮሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ያሏቸው አናባቢዎች 5 በመሆናቸው በእነሱም ቋንቋ ውስጥ የሌሉትን አናባቢዎች በሚገለገሉበት ጊዜ በራሳቸው ካሉት ጋር የማጋጨትና በዚህም ምክንያት ስህተት የመፍጠር ሁኔታ ይከሰታል፡፡ ሌላው ደግሞ ከኦሮሞኛ ቋንቋ ‹‹ዝ›. እና ‹‹ዥ›› የሌሉ በመሆናቸው በ‹‹ዘ›› ፋንታ ‹‹ስ›› በ‹‹ዥ›› ፋንታ ‹‹ጅ››ን ይጠቀማሉ ሌላው የአማርኛ ቋንቋ ግሶች በሶስተኛው መደብ ነጠላ ቁጥር ተባእታይ ፆታ ሲነገሩ መድረሻቸው ‹‹እ›› ይሆናል የኦሮሞኛው ግስ ደግሞ በ‹‹ኤ›› ድምጽ የመድረስ ፀባይ አለው፡፡ በዚህም የተነሳ ወደ ሃምስ ይለውጡታል፡፡ ለምሳሌ ‹‹የተማረ›› ለማለት ‹‹የተማሬ›› ሲሉት ይስተዋላል፡፡ ስለሆነም በነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች ስህተቶች ሊፈፀሙ ችለዋል፡፡

ከላይ በምሳሌው የቀረቡትም ስህተቶች ከላይ በተገለፀው መንገድ በመጠቀም የተከሰቱ ስህተቶች ሲሆኑ እንደሚከተለው ተስተካክለው ቢፃፉ የተፈለገውን ሀሳብ ሊያስተላልፉ ይችላሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

- ‹‹.... በድህነት ላሉ ሰዎች መርዳት፣ ቤተሰብ አልባ ለሆኑ ልጆች መርዳት…
- ‹‹.... አንዳንድ ሰዎች ግን ጥቅሙን ስላላወቁ ትምህርት ምን ያደርጋል ብለው ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ…

- ‹‹…. የትምህርትን ጥቅም ያወቁ ሀገሮች ተጠቅመውበትና በተግባር ስራ ላይ አውለውት በልጽገዋል፡፡
- ‹‹ጫት በተለምዶ ሀይል ሰጪ ከሚባሉ እፅዋት መካከል ይመደባል ይህ እፅዋት ልክ እንደ ቡና ሁሉ አካልን በማነቃቃት ተጨማሪ ሀይል በሰውነት ውስጥ እንዲካብት ያደርጋል፡፡
- ‹‹… እኔ መሆን የምፈልገው ሳይንቲስት ነው፡፡
- ‹‹…. የትምህርትን ጥቅም ተናግሬም አልጨርሰው የትምህርት ጥቅም በጣም ብዙ ነው በጣምም አስፈላጊ ነው፡፡
- ‹‹…. ትምህርቴን በሚገባ ተምሬና አጥንቼ ዩኒቨርስቲ እገባና በፈለኩት ሙያ ተመርቄ እናት ሀገሬን አኮራታለሁ፡፡
- ‹‹ … ባለፉት አመታት ማለትም በደርግ ጊዜ እንዲሁም በሃይለስላሴ ዘመን ኢትዮጵያ በጣም ችግር ውስጥ ነበረች
- …. ሴቶች እንደዚህ ያለው ችግር ውስጥ ገብተው ከሚሰቃዩ በትምህርታቸው ጥሩ ውጤት አምጥተው የባል እጅ ከመጠበቅ እንዲድኑ እመኛለሁ፡፡

ተጠኚ ተማሪዎቹ ድርሰቶቹን ሲፅፉ በአንድ አርፍተ ነገር ውስጥ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ከአንድ በላይ በመሆኑ አረፍተ ነገሩ ሲስተካከል እነዚህን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ለአንድ የስህተት አይነት ምድብ የተቆጠረው ለሌላው የስህተት አይነት የሚቆጠር ሲሆን በምሳሌ አቀራረቡም በኩል አንድ አረፍተ ነገር በተለያየ አጋጣሚ ሊነሳ ይችላል፡፡

3. ተቀራራቢ ፍቺ ያላቸውን ቃላት ለመጠቀም ሲሞክሩ የተፈፀሙ ስህተቶች

ተጠኚ ተማሪዎቹ ትክክለኛውን ቃል ካለማወቃቸው የተነሳ ተቀራራቢ ትርጉም ያላቸውን ቃላት ለመጠቀም ሲሞክሩ ስህተቶች ሲፈፀሙ ተስተውሏል፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን ማየት ይቻላል፡፡

- ‹‹ትምህርት ማለት ከስሙ ላይ እንደምናየው የመማርና የማስተማር ሂደትን ያመለክታል፡፡
- ‹‹ቤተሰቦቼን ረድቼ ወይም አግዤ ወደሚገባው እሄዳለሁ፡፡
- ‹‹እናት ሀገሬን ሰው የደረሰበትን ደረጃ ማስደረስ፡፡
- ‹‹… የኔ ምኞት በዚህ ጠባብ አስተሳሰብ ባለበት ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ማስተዋል ለመቀየር እና ቤተሰቤም እውቀት እዲኖረው ማድረግ እፈልጋሁ፡፡

- ‹‹በአሁኑ ሠዓት መንግስታችን በትምህርቱ በኩል አዲስ ፓሊስ ቅርሳ በማስራት ላይ ይገኛል
- ‹‹የወባ በሽታ የሰውን ህይወት በአደጋ ላይ የሚያደርስ ነው
- ‹‹… ቀዝቃዛማ ቦታዎች ላይ ልትያዝ ትችላለች ….››
- ‹‹ የፈጣሪ ህግ በህብረተሰቡ ውስጥ እንዳይሰበር በትክክል መከበሩን ይቆጣጠራል
- ‹‹አላማውን ያወቀ ሰው ምኞቱን ለማሳካት የሚቀጥለው እርምጃ ለዛ ምኞት መካበት መንገድ ያመቻቻሉ፡፡

ለምሳሌነት በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ከስራቸው ከተሰመረባቸው ቃላት መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎቹ ቃላቱን በትክክል ካለማወቃቸው የተነሳ ተቀራራቢ ፍቺ ያለውን ቃል በመምረጥ ሲጠቀሙ ስህተት መፈፀማቸው ነው፡፡ በመጀመሪያ የቀረበው ምሳሌ ‹‹የትምህርትን ትርጉም ለመግለጽ ተፈልጎ የቀረበ ይመስላል ይህ ከሆነ ደግሞ ‹‹ትምህርት ማለት ከስሙ እንደምንረዳው የመማር ማስተማር ሂደት ነው›› ቢል የተሻለ ነው፡፡ ቤተሰቦቼን ረድቼ ወይም አግዤ ወደሚገባው እሄዳለሁ የሚለው ‹‹ቤተሰቦቼን ረድቼ ወይም አግዤ ስጨርስ የራሴን ኑሮ እመሰርታለሁ ተብሎ ቢፃፍ መልካም ነው፡፡ ‹‹እናት ሀገሬ ሰው የደረሰበትን ደረጃ ማስደረስ የሚለው ሀገሬን ከበለፀጉት ሀገሮች ጎን ማሰለፍ እፈልጋለሁ ለማለት የፈለገ ይመስል፡፡ ይህ ከሆነ ‹‹እና ሀገሬን ካደጉት ሀገሮች እኩል ማድረግ እፈልጋለሁ›› ተብሎ ቢስተካከል የተሻለ ይሆናል፡፡ ‹‹…የኔ ምኞት በዚህ ጠባብ አስተሳሰብ ባለበት ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ማስተዋል ለመቀየር እና ቤተሰቤም እውቀት እንዲኖረው ማድረግ እፈልጋሁ››፡፡ የሚለው ‹‹የኔ ምኞት የተሳሳተ አመለካከት ባለበት ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን አስተሳሰብ በመቀየር እና ቤተሰቤም በዚህ ላይ ሰፋ ያለ እውቀት እንዲኖረው ማድረግ›› እፈልጋሁ ተብሎ ቢፃፍ የተሻለ ነው፡፡

አምስተኛው ምሳሌ ላይ የምናየው ደግሞ ፖሊስ ቅርሳ የሚል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪው ለማለት የፈለገው ፖሊሲ ቀርፆ ነው፡፡ ሌላው ‹‹የወባ በሽታ የሰውን ህይወት በአደጋ ላይ የሚያደርስ ነው›› የሚለው በአደጋ የሚለው ቃል አደጋ በሚለው ተስተካክሎ የሚያደርሰው ነው የሚለው ደግሞ የሚጥል ነው በሚል እርማት ቢሰጠው የተስተካከለ አረፍተ ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ‹‹የወባ በሽታ የሰውን ህይወት አደጋ ላይ የሚጥል ነው›› ቢባል ይሻላል ማለት ነው፡፡ ‹‹… ቀዝቃዛማ ቦታዎች ላይ ልትያዝ ትችላች…›› የሚለው የወባ በሽታ መራቢያ ቦታ ለመግለፅ የተፈለገ ይመስላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ‹‹…ረግራጋማ ቦታዎች ላይ ልትራባ ትችላለች›› ቢባል ‹‹…የፈጣሪ ህግ በህብረተሰቡ ውስጥ እንዳይሰበርና በትክክል

መከበሩን ይቆጣጠራል…›› የሚለው ‹‹…የፈጣሪ ህግ በህብረተሰቡ እንዳይጣስና በአግባቡ እንዲከበር ያደርጋል …›› ተብሎ ቢፃፍ የተሻለ ነው፡፡ ሌላውና የመጨረሻው ምሳሌ ‹‹… አላማውን ያወቀ ሰው ምኞትን ለማሳካት የሚቀጥለው እርምጃ ለዛ ምኞት መሳካት መንገድ ያመቻቻሉ …›› የሚለው አረፍተ ነገር እንዲህ ቢባል የተሻለ ይሆናል፡፡ ‹‹… አላማ ያለው ሰው ምኞቱን ለማሳካት ቀጣይ እርምጃው ወደ ውጤት የሚመሩትን መንገዶች ማመቻቸት ነው ቢባል ደህና ነው፡፡

### 4.2.1.2. ተደጋጋሚነት (ድግግሞሽ)

ከቃላት አመራረጥ ስህተት ቀጥሎ የሚገኘው ስህተት አላስፈላጊ ድግግሞሽ ነው፤ በተጠኚ ተማሪዎቹ ከተፈፀሙት 7752 የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች መካከል 1532 ስህተቶች የተፈፀሙት በዚሁ ሲሆን ይህም 8.47% በመቶ ሊሆን ችሏል፡፡ አማካይ ስህተቱ 3.22% ሲሆን በ100 ቃላት ውስጥ የተፈፀመው አማካይ የስህተት ድግግሞሽም 4.87% ነው፡፡

በአረፍተ ነገር ውስጥ አላስፈላጊ በሆነ መልኩ አንድ አይነት ቃላትና ሀረጋት ከአንድ ጊዜ በላይ ከመጠቀም የተነሳ የተፈፀሙ ስህተቶች በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ ተስተውለዋል፡፡ በአረፍተ ነገር ውስጥ ቃላትን ያለምክንያት መደረት እንዲተላለፍ የተፈለገውን መልእክት እንዲደበዝዝ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለነገሩ አፅንኦት ለመስጠት ሲባል የተደጋጋሚነት መኖር የሚፈቀድ ቢሆንም አስፈላጊ ባልሆነ ሁኔታ መደጋገሙ ግን ከማሰልቸቱም በላይ በአረፍተ ነገሩ አማካይነት እንዲተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ ግልፅነት ያሳጠዋል፡፡ በአላስፈላጊ ድግግሞሽ ምክንያት ከተፈፀሙ ስህተቶች መካከል የሚከተሉን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

- ያልተማረ ሰው ቦታ የለውም የሚባል አባባል አለ ያልተማረ ሰው በብዙ ነገሮች ሊጠቃ ይችላል፡፡
- ትምህርት የሚማረው ሰው በጣም ያስባል አርቆ ያስባል
- ትምህርት መማር ደግሞ ለብዙ ነገር ይጠቅማል
- በድህነት ላሉ ሰዎች መርዳት ቤተሰብ አልባ ለሆኑ ልጆች መርዳት
- ሀገሬን በሚያኮራ መልክ ስራዬን ይገፃ ሀገሬን እና ቤተሰቦን አኩራለሁ
- ‹‹ … ትዳሬን መስርቼ ወይም በሚገባ ትዳሬን መርቼ …››
- ‹‹የወደፊት ምኞቼ ተምሬ ትምህርቴን በተፈለገ ቦታ አድርሼ ትምህርቴን እየተማርኩም ቤተሶቼን እያገስኩም መቀጠል እፈልጋለሁ

- ‹‹አንድ ጫት ካልቃመ ስራ መስራት ያቅተዋል ጫት ጉዳት የለውም. ጫት ጥቅም ግን አለው፡፡

ከፍ ሲል ከቀረቡት ምሳሌዎች መረዳት እንደሚቻለው የተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት በተደጋጋሚነት የታዩ ናቸው፡፡ በአረፍተ ነገር ውስጥ የተፈፀሙትን የድግግሞሽ ስህተት የተደረተውን ቃል እንደሚከተለው በማስወገድ ማስተካከል ይቻላል፡፡

- ‹‹ያልተማረ ሰው ቦታ የለውም ከዛም ባሻገር በብዙ ነገሮች ሊጠቃ ይችላል፡፡
- ‹‹የተማረ ሰው አርቆ ያስባል፡፡
- ‹‹ትምህርት ለብዙ ነገር ይጠቅማል፡፡
- ‹‹በድህነት ውስጥ ላሉ ሰዎች እና ቤተሰብ አልባ ለሆኑ ልጆች መርዳት …
- ‹‹ስራ ይዤ ሀገሬን እና ቤተሰቦቼን አኮራለሁ፡፡
- ‹‹… ትዳር መስርቼ በሚገባ አስተዳድራለሁ …››
- ‹‹የወደፊት ምኞቴ ተምሬ እተፈለገው ቦታ ደርሼ ቤተሰቦቼን መርዳት ነው የምፈልገው፡፡
- ‹‹ጫት ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም፡፡ ያልቃመ ሰው ደግሞ ስራ መስራት አይችልም፡፡

### 4.2.1.3. ግድፈት

በጥናቱ የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው ተጠኚ ተማሪዎቹ ድርሰቱን በሚፅፉበት ጊዜ መግባት ያለባቸውን ነገሮች የሚገድፉ በመሆናቸው በፅህፈት የመግባባቱን ሂደት ሊያደናቅፈው እንደቻለ ነው፡፡ ጥቂት የማይባሉ ስህተቶች ከግድፈት የተነሳ እንደተፈፀሙም ለማየት ተችሏል፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ የሚካተቱ ከተቆጠሩት አጠቃላይ ስህተቶች መካከል 1322 ያህሉ በዚሁ የስህተት ምድብ ውስጥ ሲሆን ይህም በመቶኛ ሲሰላ 7.31% ነው፡፡ አማካይ ስህተቱም 2.78% ሲሆን የስህተት ድግግሞሽ 4.21% ሆኗል፡፡

ለምሳሌ ያህልም የሚከተሉት አስረጂዎች ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡

- አንድ ቅን እ( )ደ አጋጣሚ ወንድሞቿን ቁስር አብልታ እ( ) ደሸኘች
- እኔ በበኩሌ ያለ( )ኝ( ) ድርሻ በአግ( )ቡ እወጣለ( )…
- ጫት ጉዳት የለውም ጫት ጥቅም ግን አ( )ው
- ትምህርት ለድሃ ሀብቱ አይን ( )ሌለው ብሌ( ) ነው
- ይህ( ) ቢ( )ደርግ ምን ይሆናል ብሎ ስለማያውቅ ብዙ ጉዳት ይደርስበታል፡፡
- ይህም የ( )መጣ( ) ካለማወቅ የተነሳ ነው፡፡

- ብዙ ልጆች መውለድ ደግሞ በአገር ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለ( )፡፡
- ስለዚህ የአካባ( ) ንፅህና መጠበቅ ቆሻሻን ማቃጠል፡፡

ከቀረቡት ምሳሌዎች ማየት እንደተቻለው ከአረፍተ ነገሮች ውስጥ የተለያዩ ምዕላዶችና ቃላት ስለተገደፉ አረፍተ ነገሮቹ የተሟላ ሀሳብ ሳይሰጡ ቀርተዋል፡፡ እነዚህ የተገደፉት ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ እንደሚከተለው ይስተካከላሉ፡፡

- አንድ ቀን አንደ አጋጣሚ ወንድሞቿን ቁርስ አብልታ እንደሸኘች
- እኔ በበኩሌ ያለብኝን ድርሻ በአግባቡ እወጣለሁ፡፡
- ጫት ጉዳት የለውም ግን ጥቅም አለው፡፡
- ትምህርት ለድሃ ሃብቱ አይን ለሌለው ብሌኑ ነው፡፡
- ይህን ቢያደርግ ምን ይሆናል ብሎ ስለማያውቅ ብዙ ጉዳት ይደርስበታል፡፡
- ይህም የሚመጣው ካለማወቅ የተነሳ ነው
- ብዙ ልጆች መውለድ ደግሞ በአገር ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለው፡፡
- ስለዚህ የአካባቢን ንፅህና መጠበቅ ቆሻሻን ማቃጠል…

#### 4.2.1.4. ጭመራ

ተጠኚ ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ጥቂት የማይባሉ ስህተቶች ከጭመራ የተነሳ እንደተፈፀሙ ለማየት ተችሏል፡፡ በጭመራ ምክንያት በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ ከተቆጠሩት አጠቃላይ ስህተቶች መካከል 1369 ያህሉ ስህተቶች የተፈፀሙት በዚሁ የስህተት ንዑስ ምድብ ውስጥ ሲሆን ይህም በመቶኛ 7.57% አማካይ ስህተቱ 2.88% ሲሆን አማካይ የስህት ድግግሞሽ 4.36% ሊሆን ችሏል፡፡ ለምሳሌ በጭመራ የተፈፀሙ ስህተቶችን የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ማየት ይቻላል፡፡

- የትምህርት <u>ለአንድ</u> ሰው ልጅ የህይወት ስልት ሲሆን…
- ትምህርት<u>ን</u> ጥቅም በብዙ መንገድ ሊገለፅ ይችላል
- የተማረ<u>ን</u> ሰው ቦታ አያጣም
- በኢትዮፓያ ትምህርት የሚሰጠው<u>ን</u> ጥቅም ብዙ አልተለመደም
- <u>እና ስለዚህ</u> የወባ በሽታ በጣም አስቸጋሪ <u>የሆነ የበሽታ አይነት</u> ሲሆን <u>ያለውም</u> …
- ‹‹… ከዚያም በትርፍ ግዜዬ ቤተሰቤን አግዛለሁ በተረፉም <u>በ</u>ሚገባኝን አድርጌ በጥሩ ሁኔታ <u>ማለት</u> <u>እወዳለሁ</u>

በምሳሌዎቹ ላይ የተሰመረባቸው ምዕላዶች ቃላት ሀረጋት ቃላቱ ላይ በመጨመራቸው የተነሳ ስህተት ሊፈጠር ችሏል፡፡ ስለሆነም በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ጭማሪ ሆነው የገቡት አካላት

ሲወጡ አረፍተ ነገሮቹ እደሚከተለው ተስተካክለው ትክክለኛውን መልእክት ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡

- ትምህርት የሰው ልጅ የህይወት ስልት ሲሆን...
- የትምህርት ጥቅም በብዙ መንገድ ሊገለፅ ይችላል
- የተማረ ሰው ቦታ አያጣም
- በኢትዮጵያ ትምህርት የሚሰጠው ጥቅም ብዙ አልተለመደም
- ‹‹...ስለዚህ የወባ በሽታ በጣም አስቸጋሪ ሲሆን ...
- ‹‹... ከዚያም በትርፍ ጊዜዬ ቤተሰቤን አግዛለሁ በተረፈም በጥሩ ሁኔታ የሚገባኝን አድርጌ ማረፍ እፈልጋለሁ፡፡

### 4.2.1.5. ኢ-መደበኛ ቃላትና ሀረጋት

በHeaton (1988፡135) አገላለፅ ሃሳብን በፅሁፍ ማስተላለፍ የሚቻለው መደበኛ ቃላትንና ሀረጋት በአግባቡ መጠቀም ሲቻል ነው፡፡ ኢ-መደበኛ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ግን እንዲተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ ግልፅነት ያሳጣዋል ተጠኚ ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ኢ-መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀምና በንግግር ውስጥ የሚዘወተሩ ቃላት አጠቃቀም በድርሰቶች ውስጥ ለማየት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ከተፈፀሙት ስህተቶች መካከል 1238 ያህሉ የተቆጠረው በዚህ ንዑስ ክፍል ሲሆን ይህም በተጠኝ ተማሪዎቹ ከተፈፀሙት ስህተቶች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 6.84% ሆኗል፡፡ አማካይ ስህተቱም 2.61% ሲሆን አማካይ የስህተት ድግግሞሹም 3.95% ሊሆን ችሏል፡፡ በቋንቋ አጠቃቀም ከተፈፀሙ ስህተቶች መካከል ከኢ-መደበኛ ቋንቋ አጠቃቀም የተፈፀሙ ስህተቶች አነስተኛውን መጠን እንደሸፈኑ በሰንጠረዥ 3 ከቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ያህል የሚከተሉት ቀርበዋል፡፡

- ያልተማረ ሰው ጀዝባ እየተባለ የሚጠራበት አጋጣሚ አለ፡፡
- ‹‹የሐረር ሰው ቀማቴ ነው
- ያልተማረ ሰው ብዙ ልጅ መፈልፈል ይፈልጋል
- በህዝቡ ላይ ከፍተኛ ችግር ያጋጥማል ለምሳሌ በትምህርት፣ በመሰረተ ልማት፣ በመሰረተ ጤና በመሳሰሉት ችግር ህዝቡ ገደል ሊገባ ይችላል
- ለወባ በሽታ ማጥፊያ /መከላከያ/ እንደገና ያልጋ ከሰበና መጠቀም

ከቀረቡት ምሳሌዎች ውስጥ የመጀመሪያው አረፍተ ነገር ያልተማረ ሰው መሀይም እየተባለ የሚጠራበት አጋጣሚ አለ ተብሎ ቢስተካከል የተሻለ ነው፡፡ ሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ ቀማቴ የሚለው ኢ-መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም ስለሆነ "የሐረር ሰው ጫት የሚቅም ነው ቢባል የተሻለ ይሆናል››፡፡ በቀጣዩ ምሳሌ ውስጥ ያለው መፈልፈል "ደግሞ ለሰው ልጅ ልንጠቀምበት አይገባም ስለዚህ ሊሆን የሚችለው "ያልተማረ ሰው ብዙ ልጅ መውለድ ይፈልጋል"፡፡ በአራተኛው ምሳሌ ውስጥ ያለው ደግሞ "ገደል ሊገባ" የሚል ሲሆን ይህ ሲስተካከል "በህዝብ ላይ ከፍተኛ ችግር ይደርሳል ለምሳሌ በትምህርት፣ በመሰረተ ልማት፣ በመሰረተ ጤና በመሳሰሉት ችግር ህዝቡ ሊጎዳ ይችላል"፡፡ ሌላውና የመጨረሻው ምሳሌ ለወባ በሽታ ማጥፊያ (መከላከያ) እንደገና ያልጋ ከሰበና መጠቀም የሚለው የቋንቋ አወቃቀር ስህተትና ኢ-መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም የሚታይበት ሲሆን የቋንቋ አወቃቀር ስህተቱ በስፍራው ሲደርሰበት ይገለፃል፡፡ በዐረፍተ ነገሩ አማካይነት ለመግለፅ የተፈለገው ጉዳይ ግን የወባ በሽታን በአጎበር መከላከል ይቻላል ለማለት ተፈልጎ ይመስላል፡፡

### 4.2.2. የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች

ማንኛውም ድርሰት የሚገነባው ከዐረፍተ ነገር ጀምሮ ነው፤ እያንደንዱ አረፍተ ነገር የቋንቋው ትክክለኛ ሰዋሰዋዊ ስርዓት ጠብቆ መገንባት ይኖርበታል፡፡ ከንግግር ቋንቋ ይልቅ በፅሁፍ የሚተላለፍ መልዕክት የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ስርዓት መጠበቅ እንዳለበት በርካታ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ (Widdowson, 1979፡118 Norrish, 1990፡65፡6) ተጠኚ ተማሪዎች የቋንቋውን የአወቃቀር ስርአት /ሰዋሰው/ በደንብ ካለመረዳት የተነሳ በርካታ ስህተቶችን እንደፈፀሙ ለማየት ተችሏል፡፡

በሰንጠረዥ 2 በቀረበው የጥናቱ መረጃ መሰረት በአብይ የስህተት አይነትነት ከተመደቡት አራት ስህተቶች መካከል በሁለተኛ ደረጃ የሚገኘው የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ሲሆን በአጠቃላይ በድርሰቶቹ ውስጥ ከተፈፀሙት ስህተቶች መካከል 3785 የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች የተቆጠሩ ሲሆን ይህም በመቶ ሲሰላ 20.93% ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የስህተቱ መጠን 7.97% ሲሆን አማካይ የስህተት ድግግሞሽ 12.07% ሆኗል፡፡

ከቋንቋ አወቃቀር ጋር በተያያዘ በድርሰቶቹ ውስጥ በዋነኝነት የተፈፀሙት የስህተት አይነቶች የአረፍተ ነገር ስምምነት፣ የአጣማሪዎች አገባብ ስህተት እንዲሁም የመስተአምር የመስተዋድድና የተሳቢ አመልካች አገባብ ንዑሳን የስህተት አይነቶች ናቸው፡፡ እነዚህንም በዝርዝር ለማመልከት ይቻል ዘንድ በሚከተለው ሠንጠረዥ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

## ሠንጠረዥ 4 ከቋንቋ አወቃቀር ጋር በተያያዘ በድርሰቶቹ ውስጥ በዋነኝነት የተፈፀሙ የስህተት አይነቶች

| ድርሰት አንድ | የስህተት | | አማካይ ስህተት % | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት | | አማካይ ስህተት% | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት | | አማካይ ስህተት% | የስህተት ድግግሞሽ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | መቶኛ | | | ብዛት | መቶኛ | | | ብዛት | መቶኛ | | |
| የአረፍተ ነገር ስሙሙነት | 857 | 8.79 | 3.12 | 5.27 | 607 | 7.27 | 3.03 | 4.01 | 1464 | 8.09 | 3.08 | 4.66 |
| የመስተአምር እና የተሳቢ አገባብ | 563 | 5.78 | 2.05 | 3.46 | 416 | 4.98 | 2.08 | 2.76 | 979 | 5.41 | 2.06 | 3.12 |
| የአጣማሪዎች አገባብ | 413 | 4.24 | 1.50 | 2.53 | 439 | 5.26 | 2.19 | 2.90 | 852 | 4.71 | 1.79 | 2.71 |
| የመስተዋድድ አገባብ | 282 | 2.89 | 1.02 | 1.72 | 208 | 2.49 | 1.04 | 1.38 | 490 | 2.71 | 1.03 | 1.56 |
| ጠቅላ ድምር | 2115 | 21.71 | 7.69 | 12.99 | 1670 | 20.01 | 8.35 | 11.06 | 3785 | 20.93 | 7.97 | 12.07 |

#### 4.2.2.1. የዐረፍተ ነገር ስምምነት

ከፍ ሲል በቀረበው ሠንጠረዥ እንደተገለፀው በቋንቋ አወቃቀር ስህተትነት ከተነሱት ንዑሳን ክፍሎች መካከል የቀዳሚነቱን ስፍራ የያዘው የአረፍተ ነገር ስምምነት ነው፤ በድርሰቶቹ ውስጥ በአጠቃላይ ከተፈፀሙት 18087 ስህተቶች መካከል 1464 ያህሉ የተቆጠረው በዚሁ የስህተት አይነት ውስጥ ነው። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 8.09% አማካይ የስህተት መጠኑ 3.08% ሲሆን የስህተት ድግግሞሹ 466% ያህል ነው። በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ የሚነሱት ጉዳዮች የቁጥር፣ የፆታ፣ የጊዜና የመደብ ስምምነት ስህተቶች ናቸው።

ሀ. **የቁጥር ስምምነት ስህተቶች፡-** ይህ በተማሪዎቹ የድርሰት መልመጃዎች ውስጥ የታዩትን የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ የገላጭና ተገላጭ የቁጥር አለመጣጣም ስህተቶችን ያጠቃልላል። ለምሳሌ ያክል የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች እንመልከት፤

- በዓለማችን አሉ የሚባሉት ነገር ሁሉ የትምህርት ውጤት ነው
- ጫት የሚኒቅመው ኢንቅልፋችን ኢንዳይመጣ ናቸው
- የሰው ልጅ ሀሳብና አላማ የተለያየ ናቸው
- እርሷ ግን የወደፋት አላማ ስላላት ተግታ ይሰራሉ
- በዶክተርነት ወደ አውሮፓ ሄደው እየሰራች ነው
- ትምህርት በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ

ከፍ ሲል ለቁጥር ስምምነት ስህተት የተመለከቱትን አስረጂዎች በሚከተለው አይነት ቢስተካከሉ የተሻሉ ይሆናሉ።

‹‹.... በዓለማችን አሉ የሚባሉት ነገሮች ሁሉ የትምህርት ውጤቶች ናቸው።

‹‹.... ጫት የምንቅመው እንቅልፋችን እንዳይመጣ ነው።

‹‹.... የሰው ልጅ ሀሳብና አላማ የተለያየ ነው።

‹‹.... እርሷ ግን የወደፊት አላማ ስላላት ተግታ ትሰራለች።

‹‹.... በዶክተርነት ወደ አውሮፓ ሄዳ እየሰራች ነው።

‹‹.... ትምህርት በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታል።

## ለ. የፆታ ስምምነት

- እሱ ቤተሰቦቼን በደንብ ከረዳች
- የወደፊት ምኞቴ ትምህርት ተምሬ በሚገባ አጥንች ዩኒቨርስቲ ግብቼ ከዚያም በፈለኩት ሙያ ተመርቄ እናት ሀገሬን አኮራቻት ከድህነት አወጣቻት …
- አንድ ገበሬ ጫት ተክሎ ከበቀለ በኃላ ጫቱን ቆርጦ ትሸጣለች
- አንድ ሰው ትምህርት ከተማረ ብዙ አይነት ነገሮች የማከናወን ብቃት ሊኖራት ይችላል፡፡
- …. ሁልጊዜ በለሊት ተነስታ ያጠናል የቤት ስራዋን ማታ ትሰራለች፣ በጣም ትጉና ታታሪ ተማሪ ነው፡፡ የምታስበው እንደ አዋቂ ነው፡፡

ከላይ በፆታ ስምምነት ስህተት በተነሱት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ተጠኚ ተማሪዎቹ የተባዕታይ ፆታ አመልካች ምዕላድን ባለመጠቀማቸው የድርጊት ባለቤት የሆኑትን ወንዶች በአነስታይ ፆታ ሊጠሩዋቸው ችለዋል፡፡ እነዚህም አረፍተ ነገሮች እንደሚከተለው ቢስተካከሉ የተሻለ ነው፡፡

- እሷም ቤተሰቦቼን በደንብ ከረዳች
- ወደፊት ትምህርቴን ስጨርስ ቤተሰቦቼን መርዳት እፈልጋለሁ
- የወደፊት ምኞቴ ትምህርት ተምሬ በሚገባ አጥንቼ ዩኒቨርስቲ ገብቼ ከዚያም በፈለኩት ሙያ ተመርቄ እናት ሀገሬን አኩርቼ ከድህነት አውጥቼ …..
- አንድ ገበሬ ጫት ተክሎ ከበቀለ በኃላ ጫቱን ቆርጦ ይሸጣል
- አንድ ሰው ከተማረ ብዙ አይነት ነገሮችን የማከናወን ብቃት ሊኖረው ይችላል
- …. ሁልጊዜ በለሊት ተነስታ ታጠናለች፣ የቤት ስራዋን ማታ ትሰራለች በጣም ትጉና ታታሪ ተማሪ ናት፡፡ የምታስበውም እንደ አዋቂ ነው፡፡

## ሐ. የመደብ ስምምነት ስህተቶች

በተጠኚ ተማሪዎች ድርሰቶች ውስጥ የመደብ ስምምነት ስህተቶች ይስተዋላሉ ለምሳሌ፡-

- እኛ ሴቶች ብዙ እንቅፋት ይደርስበታል
- እኔ ጫት ከጀመርኩኝ ሁለት አመታትን አስመዝግባለች
- ትምህርትን መርጠን ወደ ትምህርት ቤት የምንሄደው እውቀት እንድታገኝ ነው

እነዚህ ከላይ የተገለፁት አረፍተ ነገሮች በሚታዩበት ጊዜ በመጀመሪያው አረፍተ ነገር የአንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር እና የሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር በሁለተኛው አረፍተ ነገር

አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር እና ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አነስታይ በሶስተኛው አረፍተ ነገርም በአንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር እና በሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አነስታይ ስለሆነም አረፍተ ነገሮቹ በሚከተለው መንገድ ቢስተካከሉ የተሻለ ይሆናል፡፡

‹‹ እኛ ሴቶች ብዙ እንቅፋት ይደርስብናል

‹‹ እሷም ቤተሰቦቿን በደንብ ከረዳች

‹‹ እኔ ጫት ከጀመርኩኝ ሁለት አመታትን አስመዝግቢያለሁ (እሷ ጫት መቃም ከጀመረች ሁለት አመታትን አስመዝግባለች

‹‹ ትምህርትን መርጠን ወደ ትምህርት ቤት የምንሄደው እውቀት እንድናገኝ ነው ወይም ትምህርትን መርጣ ወደ ትምህርት ቤት የምትሄደው እውቀት እንድታገኝ ነው

‹‹… በጣም ትጉና ታታሪ ተማሪ ስለሆነች ሁል ጊዜ በሌሊት ተነስታ ታጠናለች፣ የቤት ስራዎን ማታ ትስራለች፡፡

## መ. የጊዜ ስምምነት ስህተቶች

- የወደፊት ምኞቴ በሀገራት ያሉትን ባህሎች አወኩ እፈልጋለሁ ለምን ቢባል ልዩነታችን አንድነታችን ጌጣችን ይሆናል
- በአሁኑ ሰአት መንግስታችን በትምህርቱ በኩል አዲስ ፖሊሲ ቅርሳ በማሰራት ላይ አግኝቷል
- የወባ በሽታ የሚተላለፈው መንገድ ብዙ ናቸው ከነዚሁም ውስጥ የወባ በሽታ የተያዘው የሰውየውን ልብስ መልበስ ከሰውየው ጋር አብረን አድረን … በወባ ትንኝ ሊይዝ ይችላል

ከእነዚህ መረጃዎች መገንዘብ እንደተቻለው ተጠኚ ተማሪዎቹ ድርሰቶቹን በሚፅፉበት ጊዜ ስህተት ሊፈፅሙ የቻሉት ድርጊቱ የተፈፀመበትን ወይም የሚፈፀምበትን ጊዜ በአግባቡ ሊገልፁ ባለመቻላቸው ነው፤ ለምሳሌ የመጀመሪያው አረፍተ ነገር ሲታይ ፀሐፊው የሀገሩን ባህል ለማወቅ የወደፊት ምኞቱ እንደሆነ ለመግለፅ የሚፈልግ ይመስላል፡፡ ነገር ግን በግሱ ላይ የትንቢት ጊዜ ቅርፅን በመጠቀም ሲገባው የአሁን ጊዜን ቅርፅን በመጠቀም ስህተት ሊፈጠር ችሏል፡፡ በዚህም ምክንያት የአረፍተ ነገሩ የጊዜ ስምምነት ስርአት ተጥሶ እንመለከታለን፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ ውስጥም ፀሐፊው መንግስት በአሁን ሰዓት አዲስ የትምህርት ፖሊሲ ቀርፆ በማሰራት ላይ መገኘቱን ለመግለፅ ፈልጎ ይመስላል ግን በግሱ ላይ የአሁን ጊዜ ቅርፅ ያለውን ቃል መጠቀም ሲችል የሃላፊ ጊዜ ቅርፅ በመጠቀሙ ስምምነቱ

ሊጣስና ስህተት ሊፈጠር ችሏል፡፡ በሶስተኛ ዐረፍተ ነገር ውስጥም የሚስተዋለው ከአንደኛውና ከሁለተኛው አረፍተ ነገር የተለየ አይደለም፡፡ ስለዚህ ከስራቸው የተሰመረባቸው ቃላት በሚከተለው መንገድ ተስተካክለው ቢፃፉ ዐረፍተ ነገሩ ሊቃና ይችላል፡፡

- በሀገራችን ያሉትን ባህሎች ማወቅ እፈልጋለሁ ለምን ቢባል ልዩነታችን አንድነታችን ጌጣችን ነውና
- በአሁን ሰአት መንግስት በትምህርቱ በኩል አዲስ ፓሊሲ ቀርፆ በማሰራት ላይ ይገኛል፡፡
- የወባ በሽታ የሚተላለፍባቸው መንገዶች ብዙ ናቸው ከነዚህም ውስጥ የወባ በሽታ የሚዛመተው የሰውየውን ልብስ በመልበስ፣ ከሰውዬው ጋር አብሮ በማደር … በወባ ትንኝ ሊያዝ ይችላል፡፡

### 4.2.2.2. የመስተአምር እና የተሳቢ አገባብ

በቋንቋ አወቃቀር አብይ የስህተት አይነት ምድብ ውስጥ ካሉት ንዑሳን የስህተት አይነት ምድቦች መካከል የመስተአምር እና የተሳቢ አመልካች ቅጥያ(ን) አጠቃቀም ስህተቶች ተስተውለዋል፡፡ በቋንቋ አወቃቀር የስህተት ምድብ ውስጥ የመስተአምር የተሳቢ አመልካች ስህተቶች የሁለተኛ ደረጃ የያዙ ሲሆን በአጠቃላይ ከተፃፉት ድርሰቶች ከተፈፀሙት ስህተቶች መካከል 979 ያህል ስህተቶች የተቆጠሩት በዚህ የስህተት ንዑስ ምድብ ውስጥ ነው፡፡ ይህም በመቶኛ 5.41%፣ አማካይ የስህተት መጠን 2.06% እና የስህት ድግግሞሽ 3.12% ሆኗል፡፡

### ሀ. የመስተአምር አገባብ ስህተት

ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ መስተአምር በሚጠቀሙበት ጊዜ ስህተት ፈፅመዋል፡፡ ስህተቶቹ በአብዛኛው የተፈፀሙት ያለቦታው በመጠቀም ወይም ተገቢ በሆነ ቦታ ደግሞ በተሳሳተ ሁኔታ በማስገባት ነው፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፡-

- ‹‹… <u>አንድ</u> ሰዎች ግን ጥቂሙን ስላልአውቆ ትምህርት ምን ያደርጋል ብሎ የሚማሩት ትምህርት ያቋርጡና ሌላ ስራ የጀሚራሉ፡፡
- <u>ሴት</u> እንደዚ ያለው ችግር ውስጥ ገብተው ከሚቸገሩ በትምህርታቸው ቢበረቱ <u>የባሉን</u> እጅ ከመጠበቅ ይዲናሉ

ከፍ ሲል የቀረቡት ምሳሌዎች ከተሰመረባቸው መረጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው በመጀመሪያው አረፍተ ነገር የማብዛት ምልክት የሆነው ቁጥር አንዳንድ መሆን ሲገባው

‹‹አንድ›› በሚል ተገልጿል። በሁለተኛ አረፍተ ነገር ደግሞ አላስፈላጊ የመስተአምር ቅጥያ ተጨምሮበት ‹ሴቶች› መሆን የሚገባው ‹‹ሴት›› ሲሆን የባል መሆን የሚገባውም የባሉን በማለት ተገልፆል። አረፍተ ነገሮቹ እንደሚከተለው ቢስተካከሉ ሙሉ ስሜት ሊሰጡ የሚችሉ ይሆናሉ።

‹‹… አንዳንድ ሰዎች ግን ጥቅሙን ስላላወቁ ትምህርት ምን ያደርጋል ብለው የሚማሩትን ትምህርት ያቋርጡ እና ሌላ ስራ ይጀምራሉ።

‹‹… ሴቶች እንደዚህ ያለው ችግር ውስጥ ገብተው ከሚቸገሩ በትምህርታቸው በርትተው እራሳቸውን ችለው የባልን እጅ ከመጠበቅ ይድናሉ።

## ለ. የተሳቢ አገባብ ስህተት

ቀጥሎ ባሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሳቢ አመልካች አጠቃቀም ስህተቶች የተፈፀሙ ሲሆን ስህተቱ ያለበት ስፍራ ለመጠቆም በቅንፍ ( ) ተመልክቷል።

- እናት ሀገሬ( ) ሰው የደረሰበት ደረጃ ማድረስ እፈልጋሁ
- በትርፍ ጊዜ ቤተሰቤ( ) አግዛለሁ በተረፈም….
- የትምህርት( ) ትርጉም የዚን ያህል ካወራን የትምህርት ጥቅምን ደግሞ በይበልጥ እናነሳዋለን
- ሀገራች ( ) ኢትዮጵያ ልታድግ የምትችለው በወንድ ብቻ ሳይሆን በሴቶችም ጥረት መሆን አለበት
- ያልተማረ ሰው ልጆቹ ( ) እንዴት እንደሚያስተምር …
- እኔ መሆን የምፈልገው ሳይንቲስት (ን) ነው
- ሀገሬን በሚያኮራ መልክ ስራ (ን) ይገኘ ሀገሬን እና ቤተሰቦቼን አኮራለሁ።

ከመረጃዎቹ መረዳት እንደሚቻለው ተጠኚ ተማሪዎቹ ተሳቢዎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ መግባት ባለባቸው ቦታዎች ላይ የመግደፍ አላስፈላጊ በሆነው ቦታ ደግሞ የመጨመር ሁኔታ ታይቷል። ስለዚህ ከላይ የቀረቡት አረፍተ ነገሮች እንደሚከተለው ቢስተካከሉ የተሻለ ይሆናል።

- ‹‹እናት ሀገሬን ሰው የደረሰበት ደረጃ ማድረስ እፈልጋለሁ
- ‹‹በትርፍ ጊዜ ቤተሰቤን አግዛለሁ በተረፈም..
- ‹‹የትምህርትን ትርጉም የዚን ያህል ካወራን የትምህርት ጥቅምን ደግሞ በይልጥ እናነሳለን

- ‹‹ሀገራችን ኢትዮጵያ ልታድግ የምትችለው በወንድ ብቻ ሳይሆን በሴቶችም ጥረት መሆን አለበት
- ‹‹ያልተማረ ሰው ልጆቹን እንዴት እንደሚያስተምር …
- ‹‹… እኔ መሆን የምፈልገው ሳይንቲስት ነው
- ‹‹… ሀገሬን በሚያኮራ መልክ ስራ ይገኘ ሀገሬንና ቤተሰቦቼን እረዳለሁ

### 4.2.2.3. የአጣማሪዎች አገባብ ስህተቶች

ተጠኚ ተማሪዎች የአጣማሪዎችን አገባብ በትክክል ካለመረዳታቸው የተነሳ ስህቶችን እንደሚፈፅሙ ለማየት ተችሏል፡፡ በአጣማሪዎች አጠቃቀም ጉድለት የተፈፀመው ስህተት ብዛት 852 ያህል ሲሆን ይህም በመቶኛ ሲሰላ 4.71% ያህል ነው፡፡ አማካይ ስህተቱ 1.79% ሲሆን የስህተቱ ድግግሞሽ 2.71% ሊሆን ችሏል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉትን ምሳሌዎች ለአብነት ማቅረብ ይቻላል፡፡

- ‹‹… ትምህርት ግን ሊጠፋ የማይችል፣ ሊከስር የማይችል ዘላለማዊ ንብረት ነው፡፡ በርግጥ ካልተጠቀሙበት ሊከስር ይችላል ነገር ግን የትምህርት ጥቅም በብዙ መንገድ ሊገለፅ ይችላል፡፡
- ‹‹… የቤተሰብ ሃላፊነትን ለመሸከም በብዙ ስራ ላይ ለመሰማራትና አእምሮን ለማዳበር ወዘተ እና ስለዚህ የትምህርት ጥቅም ብዙ ከሆነ መማር የሰው ልጅ መጠየፍ የለበትም
- ትምህርት ማህበራዊ ኑሮን ለመኖር ጠቃሚ ነው፡፡ እንዲሁም ይሁን እንጂ የዚህን ዘመን ኑሮ ያለእውቀት፣ ያለትምህርት፣ ያለመግባባት መኖር አይችልም፡፡

እነዚህ ከስራቸው የተሰመረባቸው አጣማሪዎች በሚታዩበት ጊዜ በመጀመሪያው አረፍተ ነገር ውስጥ ‹‹ነገር ግን›› የሚለው አጣማሪ በስህተት የገባ ሲሆን በሁለተኛው እና በሶስተኛው አረፍተ ነገር ውስጥ ‹‹እና›› ‹‹ስለዚህ›› እንዲሁም ‹‹ይሁን እንጂ›› የተባሉት በአንድ ላይ በመግባታቸው ስህተት ፈጥረዋል፡፡ ስለዚህ እንደሚከተለው ቢስተካከሉ ሳይሻል አይቀርም፡፡
‹‹… ትምህርት ግን ሊጠፋና ሊከስር የማይችል ዘላለማዊ ንብረት ነው፡፡ በርግጥ ካልተጠቀሙበት ሊከስር ይችላል ስለዚህ የትምህርት ጥቅም በብዙ መንገድ ሊገለፅ ይችላል፡፡

‹‹… የቤተሰብ ሀላፊነትን ለመሸከም በብዙ ስራ ላይ ለመሰማራትና አእምሮን ለማዳበር ወዘተ ይጠቅማል ስለዚህ የትምህርት ጥቅም ብዙ ስለሆነ መማርን የሰው ልጅ መጠየፍ የለበትም፡፡

‹‹ ትምህርት ማህበራዊ ኑሮን ለመኖር ጠቃሚ ነው፡፡ ስለዚህም የዚህን ዘመን ኑሮ ያለእውቀት …. መኖር አይችልም፡፡

### 4.2.2.4. የመስተዋድድ አገባብ ስህተቶች

በቋንቋ አወቃቀር አቢይ የስህተት አይነት ምድብ ውስጥ ከተነሱት አንዱ የመስተዋድድ አገባብ ስህተት ነው፡፡ ከድርሰቶቹ ውስጥ በአጠቃላይ ከተፈፀሙት 18087 ስህተቶች መካከል 490 ያህሉ የተቆጠረው በዚህ የስህተት አይነት ውስጥ ነው፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 2.71%፣ አማካይ የስህተት መጠኑ 1.03% ሲሆን የስህተት ድግግሞሽ 1.56% ያህል ነው፡፡

የድርሰት መልመጃዎቹ እንደሚያመለክቱት የመስተዋድድ አገባብ ስህተቶች የተፈፀሙት በተለያዩ ቦታዎች ነው ይህም ተጠኚ ተማሪዎቹ ምንም አይነት መስተዋድድ በማያስፈልግበት ቦታ መስተዋድዶቹን ሲጠቀሙ ለማየት ተሞክሯል፡፡ በተጨማሪም ትክክለኛ እና ተገቢ ያልሆኑ መስተዋድዶችን በመጠቀምና መስተዋድዶችን በመግደፍ ነው፤ ከእነዚህ ውስጥ ለአብነት የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡-

- በወደፊት ትምህርቴን ስጨርስ ቤተሰቦቼን መርዳት እፈልጋለሁ
- ከኢትዮጵያውያን እንደነሱ ብንማር ጥሩ ነበር
- ….ብዙውን ጊዜ በተለያዩ በሴቶች ላይ በትምህርት ምክንያት ላይ የሚደርሰው ጭቆና በጣም ያሳዝናል

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች መስተዋድድ በማያስፈልግበት ቦታ በመጨመር የተፈፀሙ ስህተቶች ናቸው፡፡ በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ የገቡትን መስተዋድዶች በማውጣት አረፍተ ነገሮቹን እንደሚከተለው ማስተካከል ይቻላል፡፡

- ‹‹ወደፊት ትምህርቴን ስጨርስ ቤተሰቦቼን መርዳት እፈልጋሁ
- ‹‹ኢትዮጵያውያንም እንደነሱ ብንማር ጥሩ ነበር
- ‹‹…ብዙውን ጊዜ በተለያዩ ሴቶች ላይ በትምህርት ምክንያት የሚደርሰው ጭቆና በጣም ያሳዝናል፡፡

ሌላው ተገቢ ያልሆኑ መስተዋድዶችን በመጠቀም የተፈፀሙ ስህተቶች በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ በስፋት ተስተውሏል የሚከተሉትን ምሳሌዎች ለማየት እንሞክር

- ‹‹…. እንግዲህ የትምህርት ብዙ ጥቅም አለው፡፡

- በወባ በሽታ የሚገኝበት ቦታ
- ‹‹… እንደየ ሚራቡበትን ቦታዎች መድፈን

መስተዋድዶቹ ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ በአረፍተ ነገር ውስጥ በመግባታቸው የተነሳ ስህተት ሊፈጠር ችሏል፡፡ ስለዚህ የተሰመረባቸውን መስተዋድዶች በተገቢው መስተዋድድ ተስተካክለው ቢፃፉ የሚከተለውን ይመስላሉ

‹‹…እንግዲህ ትምህርት ብዙ ጥቅም አለው፡፡

‹‹ የወባ በሽታ የሚገኝበት ቦታ .....

‹‹.... የሚራቡበት ቦታዎችን መድፈን ወዘተ

መስተዋድዶችን በመግደፋቸው የተነሳ የተፈፀሙ ስህተቶችን በተጠኚ ተማሪዎቹ የድርስት መልመጃዎች ውስጥ ታይተዋል ለምሳሌ የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች እንመልከት

- …እድሜያቸው ( )ትምህርት የደርሱ ህፃናትን ወደ ትምህርት ቤት በመውሰድ ተገቢው ትምህርት እንዲያገኙ መንግስታችን ብዙ እያጠረ ይገኛል
- ሰው ምኞቱን ( )ማሳካት አላማ ሊኖረው ይገባል
- … ጠዋት ተነስታ ( )ወንድሞቿ ቁርስ ታዘጋጀለች፡፡ ወደ ትምህርት ቤት እንድሄዱ ታደርጋለች ይህ የሁልጊዜ ስራዋ ነው

እነዚህ ከዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የተገደፋት መስተዋድዶች በሚከተለው መንገድ ሲገቡ ዐረፍተ ነገሩ የተሟላ ይሆናል፡፡

- "…እድሚያቸው ለትምህርት የድረሱ ህፃናትን ወደ ትምህርት ቤት በመውሰድ ተገቢውን ትምህርት እንደያገኙ መንግስታችን ብዙ አየጣረ ይገኛል
- "ሰው ምኞቱን ለማስካት አለማ ሊኖረው ይገባል
- "…ጠዋት ተንስታ ለወንደሞቿ ቁርስ ታዘጋጃለች ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ ታደርጋለች ይህ የሁል ጊዜ ስራዋ ነው፡፡

### 4.2.3. የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች

ስርአተ ነጥብ የምንጠቀመው በፅሁፍ የሚቀርብን ሀሳብ በዐረፍተ ነገሮች ከፋፍሎ ለማቅረብ፣ የዐረፍተ ነገሩ ሀሳብ መቋጨቱን ለማመልከት፣ ዝርዝር ሀሳቦችን ለመለየት ወዘት ነው፡፡ ነገር ግን ተገቢውን ስርአተ ነጥብ በተገቢው ቦታ አለመጠቀም ወይም ደግሞ ስርአተ ነጥብ ፈፅሞ አለመጠቀም የሚተላለፈው ሀሳብ እንዳይሳካ ምክንያት ይሆናል፡፡ ስለዚህ ፀሐፊው የፃፈውን ነገር አንባቢያን እንዲረዱለት ለማድረግ በተገቢው ቦታ ስርአተ

ነጥቦችን መጠቀም ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ ግን የአንባቢያን የማንበብ ስሜት ሊቀንስ እንደሚችል Day (1984:137) ይገልፃሉ።

በጥናቱ ውስጥ በስህተትነተ ከታዩት የስህተት ምድቦች መካከል በርካታ ቁጥር ያለው ስህተት የታየበት የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ነው። በድርሰቶች ውስጥ የታዩትና በተደጋጋሚ የተሰተዋሉት የአራት ነጥብና ነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ስህተቶች ናቸው።

ተጠኚ ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ከፍ ሲል በተዘረዘሩት የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ጉድለት የተነሳ የተፈፀሙ ስህተቶች ብዛት በጥናቱ ከተቆጠረው ከአጠቃላይ የስህተት መጠን ውስጥ 3760 ያህሉን ይዟል። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 20.78% ይሸፍናል። አማካይ ስህተት 7.91% ሲሆን የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ 11.98% ሊሆን ይችላል። ዝርዝርን ከሚቀጥለው ሰንጠርዥ መመልከት ይቻላል።

### ሠንጠረዥ 5 ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ጉድለት የተነሳ የተፈፀሙ ስህተቶች

| | ድርስት አንድ | | | | ድርስት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የስህተት አይነት | የስህተት ብዛት | በመቶኛ | አማካይ ስህተት % | የስህተት ድግግሞሽ % | የስህተት ብዛት | በመቶኛ | አማካይ ስህተት% | የስህተት ድግግምሽ % | የስህተት ብዛት | በመቶኛ | አማካይ ስህተት % | የስህተት ድግግሞሽ % |
| አራት ነጥብ | 1318 | 13.53 | 4.79 | 8.09 | 1028 | 12.31 | 5.14 | 6.81 | 2346 | 12.97 | 7.48 | 7.48 |
| ነጠላ ሰረዝ | 692 | 7.10 | 2.52 | 4.26 | 722 | 8.65 | 3.61 | 4.78 | 1414 | 7.82 | 2.97 | 4.49 |
| ድምር | 2010 | 20.64 | 7.31 | 12.35 | 1750 | 20.96 | 8.75 | 11.59 | 3760 | 20.79 | 7.91 | 11.98 |

### 4.2.3.1. የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች

በአራት ነጥብ ንዑስ የስህተት አይነት ምድብ ውስጥ 2346 ስህተቶች የተቆጠሩ ሲሆን ይህም በአጠቃላይ ድርሰቶች ውስጥ ከተፈፀሙት ስህተቶች መካከል 12.97% ሊሸፍን ችሏል። አማካይ የስህተት መጠን 4.94% ሲሆን የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ 7.48% ነው። በአራት ነጥብ አጠቃቀም ንዑስ የስህተት ምድብ ውስጥ የተመለከቱት ስህተቶች፣ በአራት ነጥብ ፋንታ ሁለት ነጥብ በመጠቀም የተፈፀሙ ስህተቶች፣ በተገቢው ቦታ አራት ነጥብ ባለመጠቀም የተፈፀሙ ስህተቶች ወዘተ ናቸው።

### ሀ. በአራት ነጥብ ፈንታ ሁለት ነጥብ በመጠቀም የተፈፀሙ ስህተቶች

‹‹ብትምህርት አለም ላይ እያለሁ ምኞቴን የሚያሰናክሉብኝን ነገሮች ሁሉ በትዕግስት ማሳለፍ እንዳለብኝ አውቃለሁ (፡) እኛ ሴቶች ብዙ እንቅፋት ይደርስብናል (፡) ለምሳሌ ያደግንበት ማህበረሰብ ተፅኖ ያደርግብናል (፡) በምንኖርበት አካባቢ ለሴቶች ያላቸው አሜሌካኬት ጥሩ አይዴለም (፡) ሴቶችም ይህ ተፅዕኖ ስለሚያድርባቸው ከመማር ይልቅ ትዳር መስርቶ ቤት ውስጥ ለመዋል ይገደዳሉ(፡)

‹‹...የትምህርት ጥቅም ብዙ ናቸው (፡) ነገር ግን በሀገራችን በኢትዮጵያ ትምህርት የሚሰጠውን ጥቅም ብዙ አልተለመደም (፡) ይሁን እንጂ የትምህርት ጥቅም ያወቀ ሀገር ተጠቅሞበት በተግባር ሲራ ላይ አውለ በልፅጎዋል(፡)

### ለ. በተገቢው ቦታ አራት ነጥብ ባለመጠቀም የሚፈፀም ስህተት

‹‹...የትምህርት ጥቅም ያወቀች ሀገር አሁን አድጋ ዜጎቿም በበቂ እውቀት እየኖሩ ናቸው( ) ለምሳሌ አሜሪካ ብንወስዳት ድሮ ልክ እንደኛ ነበረች( ) ነገር ግን የትምህርት ጥቅም ስላአወቁ አደጉ( )

‹‹... የገዳ ስርአት ምንጩ የህዝባዊ ህግ ነው ይባላል /ተብሎ/ ይታመናል ( ) ይህ ደግሞ የአንድ ገዳ ስርአት /ህግ/ ተሰበረ ማለት አንድ ሰው በህብረተሰቡ ውስጥ የእግዚአብሔርን ህግ ሰበረ ማለት ነው( )

‹‹...እያንዳንዱ ሰው የራሱን ምኞት ለማሳካት ይሞክራል( ) ከሚሞክራቸው ሙከራዎች ውስጥ የሚሳኩና የማይሳኩ ይኖራሉ። ለምሳሌ ራሴን ብወስድ

‹‹ኤሌክትሪካል ኢንጅነር ለመሆን ምኞት አለኝ ( ) ይህን ምኞቴን ለማሳካት ብዙ ጥረት አደርጋለሁ()

‹‹…. የሰው ልጅ ሀሳብና አላማ የተለያየ ነው( ) ስለዚህ ለዛ አላማ ዋናው ምክንያት ሊሆን የሚችለው ትምህርት ስንማር ብቻ ነው( ) ትምህርት በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ( ) …››

‹‹ የወባ ትንኝ ወባ ያለውን ነክሳ የሌለውን ሰው ትነክሳለች( )

ከላይ በ‹‹ሀ›› የተመለከቱት ስህተቶች በሚታዩበት ጊዜ በአራት ነጥብ ፈንታ ሁለት ነጥብን በመጠቀም ስህተት ሲፈፅሙ በ‹‹ለ›› የተመለከተው ስህተት ደግሞ የአራት ነጥብ ጠቀሜታና አገባብ ካለመገንዘብ የተነሳ ነጥቡ ሊገባበት የሚችለው ቦታ በቅንፍ እንደተመለከተው ምንም ባለማስገባት ስህተት ሊፈፅሙ ችለዋል፡፡ ስለሆነም በእነዚህ ስህተቶች በተፈፀሙባቸው ቦታዎች ላይ አራት ነጥብ ቢገባ ይስተካከላል፡፡

### 4.2.3.2. የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ስህተቶች

ነጠላ ሰረዝ የምንለው በዝርዝር የሚቀርቡ ጉዳዮችን ስሞችን ጥገኛ ሃረጎችንና የመሳሰሉትን አንዱን ከአንዱ ለመለየት አገልግሎት ላይ የሚውል የስርአተ ነጥብ አይነት ነው፡፡ ተተኳሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ከነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ጉድለት የተነሳ በርካታ ስህተቶች ፈፅመዋል፡፡

በጥናቱ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በድርሰቶቹ ውስጥ በአጠቃላይ ከተፈፀሙት ስህተቶች መካከል 1414 የሚያህሉ ስህተቶች የተፈፀሙት በዚህ ንዑስ የነጠላ ሰረዝ የስህተት ምድብ ውስጥ ነው፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 7.82% ነው፡፡ አማካይ የስህተት መጠኑ 2.97% ሲሆን የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ 4.49% ሊሆን ችሏል፡፡

በዚህ ንዑስ የስህተት ምድብ ውስጥ በስህተትነት የተቆጠሩትን በሙሉ በአስረጅነት ማቅረብ አስቸጋሪ በመሆኑ ስለስህተቱ አይነት ባህሪ ለመገንዘብ እንዲቻል የሚከተሉት በምሳሌነት ቀርበዋል፡-

- ትምህርት ቤት ማለት የአዋቂዎች ማሰብሰብያ (:) የአዋቂዎች መፍለቂያ (:) የፕሮፎሰሮች መንደር (:) መሆኑ ማንንም አያጠራጥርም
- ‹‹...ትምህርትን ጥቅም በብዙ መንገድ ሊገለፅ ይችላል ለምሳሌ ያህል ለአእምሮ ብቃት ከሰው ጋር ለመለማመድ (:) ጭንቅላትን ለማዳበር (:) የህይወት ገፅታን ለማወቅ (:) ለሀገር ደህንት ለመላቀቅ (:) ለኑሮ ፕላን ለማውጣት ወዘተ .... ተገልፆ አያልቅም፡፡
- ‹‹... ለሰው ልጅ የወደፊ ምኞት መንገድ ከሚሆኑ መካከል ዋነኛው አላማ መያዝ (-›) ለአላማ መትጋት (-›) አላማውን ማግኘት ነው፡፡
- ‹‹ ትምህርት መማር ደግሞ ለብዙ ነገር ይጠቅማል አላማን ግብ ለመምታት (:) የቤተሰብን ሀላፊነት ለመሸከም (:) በብዙ ስራ ላይ ለመሰማራት (:) አእምሮን ለማዳበር (:) ወዘተ...

ከላይ በምሳሌነት ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት የተቻለው በነጠላ ሰረዝ ፈንታ ሁለት ነጥብ በመጠቀም በተገቢው ቦታ መግባት ያለበትን በመተው እና የቀስት ምልክት በማስገባት ስህተቱ ሊፈፀም እንደቻለ ነው፡፡ ስለዚህ በነዚህ ከላይ በቀረቡት አጠቃቀሞች ሳቢያ የተፈፀመውን ስህተት ለማስተካከል ሁለት ነጥቡንና ቀስቱን አስወግዶ ነጠላ ሰረዝ በመጠቀም እደሚከተለው ማስተካከል ይቻላል፡፡

- ‹‹ትምህርት ቤት ማለት የአዋቂዎች መስበሰቢያ፣ የአዋቂዎች መፍለቂያ፣ የፕሮፌሰሮች መንደር ወዘተ መሆኑ ማንንም አያጠራጥርም፡፡
- ‹‹... የትምህርት ጥቅም በብዙ መንገድ ሊገለፅ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ያህል ለአእምሮ ብቃት ከሰው ጋር ለመላመድ፣ ጭንቅላትን ለማዳበር፣ የህይወት ገፅታን ለማወቅ፣ ለሀገር ደህንነት፣ ለኑሮ ፕላን ለማውጣት ወዘተ ... ተገልፆ አያልቅም፡፡
- ‹‹ ለሰው ልጅ የወደፊት ምኞት መንገድ ከሚሆኑ መካከል ዋነኞቹ አላማ መያዝ፣ ለአላማ መትጋት፣ አላማውን ማግኘት ወዘተ ነው፡፡
- ‹...ትምህርት መማር ደግሞ ለብዙ ነገር ይጠቅማል አላማን ግብ ለመምታት፣ የቤተሰብን ሃላፊነት ለመሸከም፣ በብዙ ስራ ላይ ለመሰማራት፣ አእምሮን ለማዳበር ወዘተ....››

### 4.2.4. የፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ስህተቶች

በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ስህተቶች ሲባል የቃላት ትክክለኛ ፍቺ ካለማወቅ ወይም ለቃላቱ የተሳሳተ ትርጉም መስጠትና ቃሉ የያዘውን ጽንሰ ሀሳብ ካለመረዳት የተነሳ በተሳሳተ መንገድ በመጠቀም የሚመጣ ስህተት ማለት ነው፡፡

በሠንጠረዥ 2 የሠፈረው መረጃ እንደሚያመለክተው በአጠቃላይ ተጠኚ ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ከተፈፀሙት 18087 ስህተቶች መካከል በፅንስ ሃሳብ ግንዛቤ የስህተት ምድብ ውስጥ የተቆጠሩ ስህተቶች ብዛት 2790 ነው፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 15.42% ሆኗል፡፡ አማካይ ስህተቱ 5.87% ሲሆን አማካይ የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ 8.89% ሊሆን ችሏል፡፡ ለአብነት ያህልም የሚከተሉት ዐረፍት ነገሮች ቀርበዋል፡፡

- ምኞቲ ሁሉ ይሳኬል ቢሎ ማሜን አደገኛ ነው አዳጊያች ነው ሲባል የተቻለው በዙ ችግሮች ሊያጋጥሙኝ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ለመሞት በበሽታ ዩንቨርሲቲ ውጤት አጥ ጋቢ በማሚጣት ለመስራት በመቻል በመባሬር ነው ፡፡
- የትምህርት ጥቅም ለአንድ ሰው ልጁ የህይወት ሲልት ሲሆን በአንድ የሰው አካል ለይ አእምሮአዊ ትፅንግርት ሲሆን....

ከላይ በምሳሌነት የቀረቡት ስህተቶች እንደሚከተለው ቢስተካከሉ የተሻሉ ይሆናሉ፡፡

- ምኞት ሁሉ ይሳካል ብሎ ማመን አዳጋች ነው፡፡ ምክንያቱም የሰው ልጅ ብዙ ችግር ሊያጋጥሙት ይችላሉና ነው፡፡ ለምሳሌ በህመም ምክንያት ትምህርትን ማቋረጥ በርትቶ ካለመስራት ወይም ካለማጥናት የተነሳ ከዩንቨርስቲው መባረር ስለሚኖር ምኞት ላይሳካ ይችላል፡፡
- የትምህርት ጥቅም ለሰው ልጅ የህይወት ስልት ነው፡፡

### 4.3. የስህተት ምንጭ መላምቶች

በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ ለመግለፅ እደተሞከረው በዚህ ንዑስ ክፍል ትኩረት የሚደረገው ሁለተኛውን መሰረታዊ የጥናት ጥያቄ ለመመለስ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ በተጠኚ ተማሪዎች ከተፃፉት ድርስቶች ውስጥ ከተፈፀሙ ስህተቶች ትንተና ለመምህራንና ተማሪዎቹ ከቀረቡላቸው መጠይቆች የተገኙ ደጋፊ መረጃዎችን

በማገናዘብ በዋናነት የሚታሰቡ የስህተት ምንጮች የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶች እና የስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ተፅዕኖ ናቸው።

### 4.3.1. የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ

የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ለተፈፀሙት ስህተቶች የስህተት ምንጭ ይሆናሉ ተብለው ከተገመቱት መላምቶች መካከል አንዱ ነው። በክለሳ ድርሳኑ ለማየት እንደተሞከረው የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ከታላሚው ቋንቋ (አማርኛ) ውስብስብነት የተነሳ ተማሪዎቹ የቋንቋውን አወቃቀር በሚገባ ካለማወቃቸው የተነሳ ወይም ቢያውቁት እንኳን ለተግባቦት ተግባር ሊያውሉት ሲሞክሩ የሚፈፀሙ የቋንቋ አጠቃቀምና አወቃቀር ስህተቶችን ይመለከታል። ለምሳሌ የሚከተሉትን ዐረፍት ነገሮች ለአብነት ያህል መመልከት ይቻላል፡-

- የስው ልጁ ሃሳብና አላማ የተለያዩ <u>ናቸው</u>
- እርሱ ግን የወደፊት አላማ ስላላት ተግታ <u>ይስራሉ</u>
- ትምህርት በሰው ልጁ ሕይወት ውስጥ ትልቅ ሚና <u>ይጫወታሉ</u>
- እኛ ሰቶች ብዙ እንቅፋት <u>ይደርስበታል</u>
- እኔ ጫት ከጀመርኩኝ ሁለት አመታትን <u>አስመዝግባለች</u>
- አንድ ገበሬ ጫት ተክሎ ከበቀለ በኋላ ጫቱን ቶርጦ <u>ትሸጣለች</u>

እነዚህን ከላይ ያየናቸው ምሳሌዎች በአረፍተ ነገር ስምምነት ከቀረቡት ስህተቶች መካከል ሲሆን ምሳሌዎቹ በሚታዩበት ጊዜ የመጀመሪያዎቹ ሶስት አረፍተ ነገሮች የቁጥር አለመስማማት ችግር ያለባቸው ሲሆን የቀሩት ሶስት አረፍተ ነገሮች ደግሞ የመደብ ስምምነት ችግር አለባቸው። ቀጥሎ ደግሞ ለቃላት አመራረጥ ከቀረቡት ስህተቶች መካከል የሚከተሉት ለአብነት እንመልከት

- የኢትዮጵያ ሰው በሙሉ ከሚጊብ <u>ቀርቶ</u> በጫት ያለው አመለካከት ሶፋ ስፍራ የሚወስዱበት ነው።

ከላይ ለማየት የተሞከረውን ምሳሌ ስንፈትሽ ፀሀፊው ሊገልፅ የፈለገው በኢትዮጵያ የሚኖር ሰው ከምግብ ይልቅ ጫትን እንደሚያስበልጥ እና ለጫት ያለውም አመለካከት ሰፊ እንደሆነ ነው። ይሁን እንጂ ተገቢ ቃላትን ያለመጠቀሙና ተገቢ

መስተዋድዶች ባለመጠቀሙ ምክንያት ስህተት ሊፈጠር ችሏል፡፡ ሌላው ለአጣማሪዎች አጠቃቀም ስህተት ከተጠቀሱት መካከልም

- ‹‹ትምህርት ማህበራዊ ኑሮን ለመኖር ጠቃሚ ነው፡፡ እንዲሁም ይሁን እንጂ የዚን ዘመን ኑሮ ያለ እውቀት ያለ ትምህርት ያለ መግባባት መኖር አይቻልም፡፡

ከላይ ያለው ምሳሌ በሚታይበት ጊዜ ተማሪው ሁለቱን አጣማሪዎች መግባት በማይገባቸው ቦታዎች ላይ በማስገባታቸው ስህተት ሊፈፀም ችሏል፡፡

ሌላው ለመስተዋድድ አገባብ ስህተቶች ከተጠቀሱት መካከል

‹‹…. ብዙውን ጊዜ በተለያዩ በሴቶች ላይ በትምህርት ምክንያት ላይ የሚደርሰው ጭቆና በጣም ያሳዝናል

‹‹በወደፊት ትምህርቴን ስጨርስ ቤተሰቦቼን መርዳት እፈልጋለሁ

‹‹ከኢትዮጵያውያን እንደነሱ ብንማር ጥሩ ነበር

ከላይ በምሳሌ የቀረቡት አረፍተ ነገሮች ሲታዩ የመጀመሪያው አረፍተ ነገር በትምህርት ምክንያት በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጭቆና ለመግለፅ ነው፡፡ ነገር ግን መስተዋድዱ በማያስፈልግበት ቦታ በመግባቱ ስህተት ሊፈጠር ችሏል፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ ‹‹ለወደፊት›› ማለት ሲገባው በወደፊት በማለት ስህተት ሊፈጠር ችሏል፡፡ የሶስተኛ ምሳሌ ደግሞ ከመጀመሪያው ጋር ተመሳሳይ በሆነ ምክንያት ስህተት ተፈፅሟል፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ማለትም በአረፍተ ነገር ስምምነት በአጣማሪዎች አጠቃቀም በመስተዋድድ አገባብ የታዩት ስህተቶችንና ሌሎቹም ሲታዩ የሰዋሰው አገባብ ወይም የቋንቋ አወቃቀር ትምህርት በተሟላ መንገድ ባለመስጠቱ ምክንያት የተከሰቱ ናቸው ሊባል ያስችላል፡፡

መምህራንና ተማሪዎችም ለቀረቡላቸው መጠይቆች የሠጧቸው ምላሾች መካከል አብዛኞቹ እስከአሁን የተገለፁትን ሀሳቦች የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በክፍል ሶስት ከቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ በፅህፈት ልምምድ ጊዜ የምትፈፅሚያቸው/ማቸው/ የስህተት አይነቶች ምን ምን ናቸው ተብለው ተማሪዎቹ ለተጠየቁት ሲመልሱ 103 የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ 50 የፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ፣ 50 ያአረፍተ ነገር

አመሰራረት፣ 45 የአንቀጽ አመሰራረት ስህተቶች፣ 27 የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች እንደሆኑ ገልፀዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ለምትፈፅሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጭ ናቸው ብላችሁ የምታስቧቸውን ግለፁ ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄም ሲመልሱ አንደኛው ለትምህርቱ ያለን አመለካከት በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ሲሆን ከዛ ባሻገር የሁለተኛ ቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ስርአት አለመረዳት፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ በቋንቋ ውስጥ ከአንድ በላይ ፍቺ ያላቸው ቃላት መብዛት፣ የሚጠብቁና የሚላሉ ቃላት መኖር የቋንቋው ከባድ መሆን በክፍለጊዜ ማነስ ምክንያት ለፅህፈትም ሆነ ለሌሎች ክሂሎች ልምምድ እድል ማጣት፣ የፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ማነስ ወዘተ የሚሉት ይገኙበታል። ስለሆነም እንደተጠኚዎቹ አገላለፅ የቋንቋው ከባድ መሆን የሚለው አባባል የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ተማሪዎቹ ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች በምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላሉ። በተመሳሳይ ሁኔታም ተማሪዎቹ ለሚፈፅሟቸው የስህተት አይነቶች መምህራኑ በክፍል ሶስት ተጠይቀው ሲመልሱም የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ የፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ፣ የአረፍተ ነገር አመሰራረት፣ የሳድስ፣ የስርአተ ነጥቦች አጠቃቀም የመስተዋድዶችና የማሰሪያ አንቀጽ አጠቃቀም ወዘተ እንደሚፈፅሙ ገልፀዋል።

ተማሪዎቹ ይፈፅሟቸዋል ተብለው ለቀረቡት ስህተቶች የስህተት ምንጩን እንዲገልፁ በተጠየቁት መሰረት ከመለሷቸው መልሶች መካከል ለተማሪዎቹ ስህተት መፈፀም ምንጭ ከሆኑት አንደኛው ትምህርቱን የሚጀምሩት ከአምስተኛ ክፍል ስለሆነና ምንም ሳያውቁ ዘጠነኛ ክፍል ስለሚደርሱ ነው። በዚህ ጊዜ ድርሰት ሲፅፉም ሆነ አረፍተ ነገር ሲመሰርቱ ብዙ ስህተት ይፈፅማሉ፤ ለነኚህ ስህተቶች ምንጭ የሚሆነው ደግሞ የሁለተኛው ቋንቋ ስርአት አለመልመዳቸው፣ የፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ማነስ ወዘተ የሚሉት ይገኙበታል።

በአጠቃላይ ቀደም ሲል በስህተት ትንተናው ከተገኙት መረጃዎች ከመምህራኑና ከተጠኚ ተማሪዎቹ ከተሰጡት ምላሾችና አስተያየቶች እንዲሁም ከተዛማጅ ጽሁፎች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በዚህ ጥናት ውስጥ ተጠኚ ተማሪዎቹ ድርሰት ሲፅፉ ለፈፀሟቸው ስህተቶቹ መፈጠር ምክንያት ሆነው ከቀረቡት ነገሮች መካከል አንዱ የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ሊሆን እንደሚችል ነው።

### 4.3.2 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ

Norrish (1938:22) መማር የልምድ ክምችት ውጤት በመሆኑ የተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልምድ ታላሚውን ቋንቋ በመማር ሂደት ላይ ጣልቃ በመግባት የስህተት ምንጭ ሊሆን እንደሚችል ይገልፃሉ። በአፍ መፍቻነት የዳበረ የቋንቋ ልምድ አንድን አዲስ ቋንቋ በመልመድ ሂደት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማሳደር ለስህተት መፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል።

በኦሮሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ለታዩት ስህተቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ በዋናነት ይጠቀሳል፤ በመሆኑም ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ የተነሳ ተጠኚ ተማሪዎቹ በድምፆች፣ በቃላት አመራረጥ በአረፍተ ነገር አመሰራረትና በመስተዋድድ አጠቃቀም ላይ ስህተት እንደሚፈፅሙ የተሰበሰበው መረጃ ያስገነዝባል።

በኦሮሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተጠኚ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ/ኧ/ን እና /እ/ በመግደፍ በድርሰቶቻቸው ውስጥ ስህተት እንደፈፀሙ ቀደም ሲል ለመግለፅ ተሞክሯል። የኦሮሞኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ያሏቸው አናባቢዎች አምስት ናቸው። በአማርኛ ቋንቋ የድምፅ ስርአት ውስጥ የሚገኙ /ኧ/ እና /እ/ በኦሮሞኛ ቋንቋ ውስጥ ባለመኖራቸው ተማሪዎቹ ‹‹እ›› የተባለችውን ሳድስ አናባቢ በአማርኛ ቋንቋ በሚጠቀሙበት ጊዜ ከሳልሱ አናባቢ ‹‹ኢ›› ጋር ያተካኩታል። በአጠቃቀማቸው እነኢህን አናባቢዎች እንደሁለት አናባቢ በመቁጠር ሳይሆን እንደ አንድ አድርገው የሚጠቀሙባቸው በመሆኑ ስህተት ይፈፅማሉ /ይልማ 1956፡3/ ለአብነት የሚከተሉትን አስረጅዎች እንመልከት፡-

- ባለፈው አሜት ማሌትም በደርግ ግዘ እንደዚያው በሃይለስላሴ ዘሜን ኢትዮፓያ በጣም ቺግር ውስጥ ነበረች ኢናም የቴማር ሰው ኢራሱ የሌም
- የጫትጢቂም ተገስቶ ተቂሞ ሰውነታችን ያኔቃቃል ጨኒቂላታቺን ይሰቤሲባል

እነዚህ የተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት ሳልሱን ለሳድስ፣ ሳድሱን ለሳልስ በመተካት የተፃፉ ሲሆኑ በቃላቱ ላይ ብቻ ሳይሆን በአረፍተ ነገሩ ሃሳብ ላይም ለውጥ ሊያመጡ ችለዋል ከላይ የጠቀስናቸው ሀሳቦች እንደሚከተለው ቢስተካከሉ የተሻለ ይሆናሉ።

- ባለፉት አመታት ማለትም በደርግ እና በሃይለስላሴ ዘመን ኢትዮጵያ በጣም ችግር ውስጥ ነበረች የተማረም ሰው አልነበራትም፡፡
- የጫት ጥቅም ተገዝቶ ይቃማል ከዚያም ሰውነታችን ይነቃቃል አዕምሮአችንም ይሰበሰባል፡፡

ይልማ (1956፡32) እንደሚሉት በኦሮሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የ‹‹ኧ›› ድምፅ ልሳን የሌላቸው በመሆኑ በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ በ/ኧ/ ቦታ በአብዛኛውን ጊዜ /ኣ/ን አልፎ አልፎ ደግሞ /ኤ/ን በመተካት ስህተት እንደሚፈፅሙ ለመመልከት ተችሏል፡፡ እንዲሁም የአማርኛ ግሶች በሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባዕታይ ፆታ ሲነገሩ መድረሻቸው አናባቢ /ኧ/ ይሆናል፡፡ የኦሮሞኛው ግስ ደግሞ በ/ኤ/ ድምፅ የመድረስ ጠባይ ስላለው ተማሪዎቹ በዚያው በለመዱት ስርአት በመጠቀማቸው ስህተት ይፈፅማሉ፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፡-

- ‹‹…. በእርግጥ እንዲ ይሆናል አሲባ አታውቅም ከኢህቷ አንድ መኪና <u>ይገጩውና ይሞታ</u> <u>እናትየው</u> ይህን ሰሚታ በጣም ሲለደነገጠች <u>በሺቴኛ ሆኔች</u>…
- ‹‹… ሀገራችን ኢትዮጵያ ሊታድግ የምትቺለው በወንድ ብቻ ሳይሆን በሴቶቺም <u>ጥሬት</u> መሆን <u>አሌቤት</u> …

እነዚህ የተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ሲታዩ ተጠኚ ተማሪዎቹ ሐምሱን-ግዕዝ፣ ግዕዙን-ሐምስ፣ራብዕን-ግዕዝ፣ ግዕዙን-ራብዕ በማለዋወጥ የተፃፉ ሲሆኑ በመለዋወጣቸው ምክንያት ስህተት ሊፈፅም ችሏል፡፡

ይልማ (1956፡32) እንደሚሉት በኦሮምኛ ቋንቋ መስተዋድዶች በቃላት መጨረሻ እንጂ መጀመሪያ ላይ ባለመግባታቸው በአማርኛ ቋንቋ ሲጠቀሙባቸው ይዘሏቸዋል፤ ወይም ያለቦታው ያስገቧቸዋል፡፡ ስለዚህም ተጠኚ ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በቃል መነሻ ላይ ለገደፏቸው መስተዋድዶች ምክንያቱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ እንደሆነ ለመገመት አያዳግትም፡፡ ቀደም ባለው ክፍል በአስረጅነት የቀረቡት የቃላት እና የመስተዋድድ አጠቃቀም ስህተቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ምክንያት ሊፈጠሩ ከቻሉት ስህተቶች ውስጥ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ ከፍ ሲል በምሳሌነት የቀረቡትና ሌሎችም አይነት ስህተቶች የሚታዩበት ጊዜ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ለስህተት መፈጠር ምክንያት መሆኑን ሊያረጋግጡ

ይችላሉ፡፡ መምህራንና ተጠኚዎቹ ለቀረበላቸው መጠይቆች የሰነዘሯቸው አስተያየቶችም ይህንኑ ሃሳብ የሚያጠናክሩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ለመምህራን በቀረበው መጠይቅ ክፍል ሁለት መመሪያ ሁለት ተራ ቁጥር ‹8› ላይ በፅህፈት ልምምዱ ላይ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚኖረው ተፅዕኖ ምን ያህል ነው? ተብለው ተጠይቀው ሲመልሱ ካሉት አራት መምህራን መካከል ሁለቱ መምህራን በጣም ከፍተኛ ሲሉ ሁለቱ መምህራን ደግሞ ከፍተኛ ነው ሲሉ መልሰዋል፡፡ እንዲሁም የመምህራንን ነጻ አስተያየት በሚጠይቀው ክፍል ተራ ቁጥር 9 ተማሪዎቹ ፅህፈትን በሚለማመዱበት ጊዜ ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጮች ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱትን ቢጠቅሱልን ተብለው በተጠየቁት መሰረት ከአራቱ ሁለቱ መምህራን ዋነኛው የስህተት ምንጭ የአማርኛ ቋንቋን ለመማርም ሆነ ለማወቅ እንዲሁም ለመጠቀም ያላቸው ተነሳሽነት በጣም ዝቅተኛ መሆን ሲሉ የቀሩት ሁለት መምህራ ደግሞ የአማርኛ ቋንቋን ትምህት የሚጀምሩት ከአምስተኛ ክፍል ስለሆነ በተጨማሪም በሳምንት የሚማሩት ክፍለ ጊዜ አንድ መሆኑ ምንም ሳያውቁ ዘጠነኛ ክፍል ስለሚደርሱ የመማሪያ መፅሐፉ የሚያዘውን መልመጃ እንዲሰሩ ሲታዘዙ የተለያየ ስህተት ይፈፅማሉ፡፡ ለዚህ ስህተት መፈፀም ምንጩ ደግሞ መጀመሪያ ላይ ሁለቱ መምህራ የገለፁት እንዳለ ሆኖ ለቋንቋው ሁለተኛ ሰው መሆናቸውና ከክፍለ ጊዜው ውጭ የሚገለገሉት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ስለሆነ ለስህተቱ ምንጭ ሊሆን ይችላል የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

### 4.3.3. የመማር መማስተማር ሂደት ድክመቶችና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለስህተት ከሚዳረጉባቸው ምክንያቶች መካከል ታላሚውን ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጁት የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የመማር መስተማር ሂደት ድክመቶች እንደሆኑ በክለሳ ድርሳኑ ውስጥ የተዳሰሰ ነገር ነው፡፡ በመሆኑም የመምህሩ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ደካማነትና የተማሪዎቹ የትምህርት ተሳትፎ በጣም ዝቅተኛ መሆን ለስህተት መፈጠር በምክንያትነት ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡

በስህተት ትንተናው ከተገኙት ፍንጮች በተጨማሪ ከመምህራኑና ከተማሪዎቹ የመጠይቅ መልሶች የተገኙት መረጃዎች የመማር ማስተማሩ ሂደት ለፅህፈት ልምምዱ ተግባራዊ አለመሆን አስተዋፅኦ እንዳለው ይጠቁማሉ፡፡ ከእነዚህ መረጃዎች ውስጥ መልመጃውንና የመልመጃውን ተግባራዊነት በሚመለከት ለቀረቡት ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች ይገኛሉ፡፡

ሠንጠርዥ 6 የክፍልና የቤት ስራ ልምምድን በሚመለከት ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | | 5 | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 4 | ተማሪዎችን በሬዶዬ ካዳመጡት በቴሌቭዥን ካዩትና ከሰሙት በጋዜጣ ካነበቡት ሃሳብ እንዲሰበስቡ ያደርጋሉ | | | | | | | 1 | 25 | 3 | 75 |
| 11 | ፅህፈትን ለማዳበር የሚያስችሉ የተጓዳኝ ትምህርት እንቅስቃሴዎች በትምህርት ቤት ይካሄደሉ | | | | | | | | | 4 | 100 |
| 12 | በፅሁፍ የሚመለስ የክፍል ወይም የቤት ስራ ሰጥተው ያውቃሉ | | | 1 | 25 | 1 | 25 | | | 2 | 50 |
| 14 | ተማሪዎች የሚሰጣቸውን የክፍልና የቤት ስራ ስርተው ይመጣሉ | | | 1 | 25 | | | 1 | 25 | 2 | 50 |
| 18 | በክፍልም ሆነ በቤት ስራ የሰጡትን መልመጃ አርመው ያውቃሉ | 2 | 50 | 2 | 50 | | | | | | |
| 5 | ፅህፈትን ለመለማመድ ተማሪዎቹ በግልና በበድን የሚያደርጉት ጥርት ምን ያህል ነው | | | | | | | 1 | 25 | 3 | 75 |
| 6 | እርሰዎ ፅህፈትን ለማለማመድ የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው | | | | | | | 1 | 25 | 3 | 75 |
| 7 | ተማሪዎቹ የፅህፈት ችሎታቸውን ለማሻሻል የተለየዩ ነገሮችን የማንበብ ልምዳቸው ምን ያህል ነው | | | | | | | | | 4 | 100 |

አማራጭ

1. በጣም ከፍተኛ
2. ከፍተኛ
3. መካከለኛ
4. ዝቅተኛ
5. በጣም ዝቅተኛ

የፅሁፈት ልምምዱን በተመለከተ ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው መምህራኑ በፅሁፍ የሚመለስ የክፍል ሆነ የቤት ስራ ስለመስጠታቸው በተጠየቁት መሰረት በአብዛኛው እንደማይሰጡ አሉታዊ የሆነ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ሌላው በመመሪያ ሁለት በተራ ቁጥር 6 እርስዎ ፅሁፈትን ለማለማመድ የሚደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው ተብለው ለተጠየቁት ሲመልሱ አንድ መምህር ዝቅተኛ ነው፡፡ ሲል ሶስቱ መምህራን ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ነው ብለዋል፡፡ ለዚህም ምክንየታቸውን ሲገልፁ ሶስቱ የክፍለ ጊዜው ማነስና የተማሪዎቹ የትምህርት ፍላጎት ማጣት ሲሉ አንዱ መምህር ደግሞ የክፍለ ጊዜው ማነስ በማለት መልሰዋል፡፡ እንደገናም የፅሁፈት ልምምዱን ሊያዳብሩ የሚችሉ የተንዳኝ ትምህርት እንቅስቃሴዎች ድጋፍ ምን ያህል እንደሆነም ተጠይቀው ሲመልሱ የአራቱም በጣም ዝቅተኛ ነው ብለዋል፡፡ ለዚህም እንደምክንያት ያቀረቡት የተንዳኝ ትምህርት እንቅስቃሴዎች ቢኖሩም እንኳን የሚሰጡት በኦሮሞኛ ቋንቋ እንጂ በአማርኛ እንዳልሆነ ገልፀዋል፡፡ በመጠይቅ 4 ላይ መምህራኑ ተማሪዎቻቸው በሬዲዮ ካዳመጡት፣ በቴሌቪዥን ካዩትና ከሰሙት በጋዜጣ ካነበቡት ሃሳብ እንዲሰበሰብ ያደርጋሉ ለሚለው አንድ መምህር የሚያደርገው ዝቅተኛ እንደሆነና ሶስቱ መምህራኑ ደግሞ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በመጨረሻም በክፍል ሶስት በክፍት ጥያቄዎች ውስጥ መምህራኑ የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎችን የፅሁፈት ክሂል ለማዳበር መወሰድ ያለባቸው የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲዘረዝሩ ተጠይቀው ሲመልሱ የፅሁፈት ክሂልን ለማስተማር ሰፋ ያለ ጊዜ ስለሚጠይቅ በቂ ክፍለ ጊዜ መመደብ ትምህርቱን ከአምስተኛ ክፍል ይልቅ ከአንደኛ ክፍል ቢጀምሩና ከታች ክፍሎች አንስቶ ተማሪዎቹ በተደጋጋሚ የሚፅፏቸውን ስህተቶች በመረዳት ስህተታቸውን ሊያስተካክሉ የሚችሉባቸውን መንገዶች የፅሁፍ መልመጃዎችን ማሰራት ወዘተ የሚሉትን መልሶች አስፍረዋል፡፡

የፅሁፈት ልምምድን በተመለከተ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 7 የፅህፈት ልምምድ አስመልክቶ ከተማሪዎቹ የተገኙ የመጠይቅ ምላሾች

| ተ.ቁ | ጥያቂዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | | 5 | |
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 3 | ፅህፈትን ለመለማመድ የመምህሩ ጥረት ምን ያህል ነው | 5 | 1.82 | 20 | 7.27 | 80 | 29.09 | 140 | 50.91 | 30 | 10.91 |
| 6 | መልመጃዎች ታርመው መመለሳቸው ለፅህፈት ክሂሉ መዳበር የሚሰጡት ጠቀሜታ ምን ያህል ነው | 105 | 38.18 | 75 | 27.27 | 45 | 16.36 | 30 | 10.91 | 20 | 7.27 |
| 9 | ፅህፈትን በመለማመድ በኩል የመምህሩ እወቀት ምን ያህል አጥጋቢ ነው | 80 | 29.09 | 80 | 29.09 | 50 | 18.18 | 30 | 10.91 | 35 | 12.73 |
| 10 | በትምህርት ቤት የተቋቋሙት ልዩ ልዩ ክበባት ለፅህፈት ልምምድ ያላቸው አስተዎፅኦ ምን ያህል ነው | 0 | 0 | 0 | 0 | 10 | 3.64 | 108 | 39.27 | 157 | 57.09 |
| 7 | መምህሩ አንቀፅ ወይም ድርሰት መፃፍ የሚያስችሉ የክፍልና የቤት ስራዎችን ሰጥተው ያውቃሉ | 7 | 2.54 | 45 | 16.36 | 50 | 18.18 | 135 | 49.09 | 38 | 13.8 |
| 8 | መምህሩ የሚስጡትን የክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራ አርመው ይመልሳሉ | 61 | 22.18 | 40 | 14.54 | 86 | 31.27 | 42 | 15.27 | 46 | 16.73 |

አማራጭ

1. ዘወትር አወንታዊ
2. አብዛኛውን ጊዜ አወንታዊ
3. በመጠኑ አወንታዊ
4. አብዛኛውን ጊዜ አሉታዊ
5. ፈፅሞ አሉታዊ

በሠንጠረዥ 8 በጽህፈት ልምምዱ ጊዜ የመምህራኑ የትምህርት አቀራረብ በተመለከተ ለመምህራኑ የቀረበ መጠይቅ ምላሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የመምህራኑ | |
|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % |
| 17 | ተማሪዎቹ ድርሰት እንዲፅፉ ሲደረግ ርዕሱ በማንበብ ይመረጣል? | | |
| | 1. በመምህሩ | | |
| | 2. በተማሪዎቹ | 2 | 50 |
| | 3. በመምህሩና በተማሪዎቹ | - | - |
| | 4. በመማሪያ መጽሐፍ የቀረበው ርዕስ ተግባራዊ ይሆናል | 2 | 50 |
| | 5. ከላይ በተዘረዘሩት በሁሉም ይመረጣል | - | - |
| 16 | በክፍልም ሆነ በቤት ስራ ተማሪዎቹን ድርሰት እንድፅፉ የሚያደርጉበት ጊዜ | | |
| | 1. በሳምንት አንድ ጊዜ | - | - |
| | 2. በየሁለት ሳምንቱ | - | - |
| | 3. በወር አንድ ጊዜ | - | - |
| | 4. በየሶስት ወሩ | - | - |
| | 5. ሁኔታው ሲጋብዝ | 4 | 100 |
| 9 | ጽህፈትን ለማለማመድ የሚጠቀሙበት መንገድ የትኛው ነው? | | |
| | 1. ርዕስ ሰጥቶ አንቀጽ እንዲመሰረቱ ማድረግ | 4 | 100 |
| | 2. አንቀጽ ሰጥቶ ተማሪዎቹ አንቀፁን እንዲመረምሩት በማድረግ | - | - |
| | 3. አስተዋጽኦ ነድፌው ድርስት እንዲጽፋ በማድረግ | - | - |
| | 4. ተማሪዎቹ የራሳቸውን ርዕስ መርጠው እንዲፅፋ በማድረግ | - | - |
| | 5. ሁሉንም መንገድ በመጠቀም | - | - |
| 7 | በክፍል ውስጥ ጽህፈት በሚያለማምዱበት ጊዜ ስለቃላት አመሰራረትና የአረፍት ነገር አገነባብ አስተምረው ያውቃሉ? | - | - |
| | 1. ዘወትር አስተምራለሁ | 2 | 50 |
| | 2. አብዛኛውን ጊዜ አስተምራለሁ | 2 | 50 |
| | 3. በመጠኑ አስተምራለሁ | - | - |
| | 4. አንዳንድ ጊዜ አስተምራለሁ | - | - |
| | 5. እንዳመቺነቱ አስተምራለሁ | | |
| 10 | የድርስት ትምህርት ለማስተማር የትኛው ዘዴ የተሻለ ይመስልዎታል? | | |
| | 1. የድርሰት አፃፃፍ ህጎችን አስቀድሞ ማስተማር | 4 | 100 |
| | 2. በመጀመሪያ ተማሪዎቹ እንዲፅፋ በማድረግ | - | - |
| | 3. ራሳቸው ከጻፋት ድርስት በመነሳት የድርስት አፃፃፍ ህጎችን እንዲያወጡ በማድረግ | - | - |
| | 4. በተማሩት ህግ መሰረት አንቀጽ ብሎም ድርስት እንዲፅፍ በማድረግ | - | - |
| | 5. አስተዋጽኦ ነድፌው በነደፋት መሰረት እንዲፅፋ በማድረግ | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 13 | ጽህፈትን ለማለማመድ የሚያስችሉ የክፍልም ሆነ የቤት ስራዎችን አልፎ አልፎ የሚሰጡ ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልዎታል? | - | - |
| | 1. ጽህፈትን ማስተማር አስቸጋሪ በመሆኑ | 2 | 50 |
| | 2. ለአማርኛ የተሰጠው ክ/ጊዜ ጽህፈትን ለማለማመድ ስለማያስችል | - | - |
| | 3. በጽሁፍ የሚመለስ ጥያቄ በመማሪያ መጽሐፉ በስፋት ስለማይዘጋጅ | 2 | 50 |
| | 4. የተማሪዎቹ የመፃፍ ፍላጎት አነስተኛ በመሆኑ | - | - |
| | 5. ጽህፈትን ማስተማር ጠቀሜታው አነስተኛ በመሆኑ | | |
| 15 | ተማሪዎች የሚሰጣቸውን የክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራ በአብዛኛው የማይሰሩ ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልዎታ? | 3 | 75 |
| | 1. ተማሪዎቹ ትምህርቱን ስለሚንቁት | - | - |
| | 2. የጽህፈት ስራ አስቸጋሪ በመሆኑ | 1 | 25 |
| | 3. ተማሪዎቹ የመፃፍ ፍላጎት ስለሌላቸው | - | - |
| | 4. በመማሪያ መጽሐፍ ለጽህፈት የሚመረጡት ርዕሶች የተማሪዎቹን ፍላጎት ባለመያዛቸው | - | - |
| | 5. ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑ ስለሚያስቸግራቸው | | |
| 20 | እንደየክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራ የሰጡትን መልመጃ አንዳንድ ጊዜ የሚያርሙ ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልዎታል? | 1 | 25 |
| | 1. የተማሪዎቹ ቁጥር በርካታ በመሆኑ | - | - |
| | 2. ተማሪዎቹ መልመጃውን ሰርተው ስለማይመጡ | - | - |
| | 3. የማረም ስራ አድካሚና አሰልቺ በመሆኑ | - | - |
| | 4. በታረመው መሰረት ተማሪዎቹ ጽህፈታቸውን ለማሻሻል ስለማይጥሩ | 3 | 75 |
| | 5. በቂ ክፍለ ጊዜ ባለመሰጠቱ | | |

በሠንጠረዥ 8 የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ተማሪዎቹ ድርሰት የሚፅፉበት ርዕስ የተማሪዎቹን ፍላጎት ባለመያዙ መምህራንም ድርሰት የሚያፅፉት በተወሰነ የጊዜ ቅደም ተከተል ሳይሆን ሁኔታው ሲጋብዝ ወይም እንደአመቺነቱ በመሆኑ ድርሰቱን ለማፃፍ በአብዛኛው የሚጠቀሙበት መንገድ ርዕስ ሰጥቶ አንቀጽ እንዲፅፉ የሚያደርግ እንጂ በተለያየ መንገድ እንዲፅፉ የሚያደርግ ባለመሆኑ በክፍል ውስጥ ስለቃላት አመሰራረትና አረፍተ ነገር አገባብ አንዳንድ ጊዜ በማስተማራቸው ድርሰትን ለማፃፍም የተሻለ መንገድ ነው ብለው የሚያስቡትና የሚያስተምሩት አስቀድመው የድርሰት አፃፃፍ ህጎችን በማስተማር እንጂ ተማሪዎቹ ከሚፅፉት ድርሰት በመነሳት ህጉን ራሳቸው እንዲያወጡ ወይም ሌላ የተሻለ መንገድ በመፈለግ እንዲፅፉ የሚያስችሉ ባለመሆናቸው ለአማርኛ ቋንቋ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ አነስተኛ በመሆኑ

ጽህፈትን ማለማመድ ባለመቻሉና ተማሪዎቹ ቋንቋውን የመማር ተነሳሽነታቸው እጅግ በጣም ዝቅተኛ ስለሆነ ስህተቶቹ ሊፈፀሙ ችለዋል፡፡

የተማሪዎቹ ድርሰት በስህተት የተሞላ መሆኑንና የስህተቶቹ መከሰት ምናልባትም ከመምህራን የማስተማር ስልትና መፃህፍት በብዛት ካለመዘጋጀታቸው የተነሳ ሊሆን እንደሚችል ማረው (1987፡1) ኃይለሚካኤል (1993)ን በመጥቀስ ይገልፃሉ፡፡

በሌላ በኩል ደካማ የማስተማር ዘዴ ለስህተት መፈጠር ምክንያት ከመሆን ባያልፍም መርሃ ትምህርቱና የማስተማሪያ መፅሀፉ በሚታዩበት ጊዜ ከመምህራኑ ውጭ በመሆናቸው ስህተት እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናሉ (Broughton፣1993፡133-5)፡፡

ሠንጠረዥ 9 ፅህፈትን ለማለማመድ መምህራኑ የሚጠቀሙባቸውን ማቴሪያሎች በተመለከተ የመምህራን መጠይቅ ምላሾች

| ተ.ቀ | | የመምህራ | |
|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % |
| 1 | በመማሪያ መፅሀፍ የቀረቡት መልመጃዎች በአብዛኛው የሚያዳብሩት የቱን ነው | | |
| | ሀ. ማዳመጥና መናገር | - | - |
| | ለ. ማንበብን | 1 | 25 |
| | ሐ. ፅህፈትን | 2 | 50 |
| | መ. ስነ-ልሳንን | 1 | 25 |
| | ሠ. ስነ-ፅሁፍን | - | - |
| 2 | ለፅህፈት ልምምድ በይበልጥ የሚያግዙ መልመጃዎች የትኞቹ ናቸው? | | |
| | ሀ. መልመጃ አንድ | - | - |
| | ለ. መልመጃ ሁለት | - | - |
| | ሐ. መልመጃ ሦስት | 2 | 50 |
| | መ. መልመጃ አንድና ሁለት | - | - |
| | ሠ. መልመጃ ሁለትና ሶስት | 2 | 50 |
| 3 | የፅህፈት ትምህርትን በምን ላይ ተመርኩዘው ያስተምራሉ | | |
| | ሀ. በመማሪያ መፅሀፍ ብቻ | - | - |
| | ለ. በመርሃ ትምህርቱ | - | - |
| | ሐ. በመርሃ ትምህርቱና በመማሪያ መፅሀፍ | 4 | 100 |
| | መ. ከመርሃ ትምህርቱና ከመፅሀፉ ውጭ | - | - |
| | ሠ. በመርሃ ትምህርቱ በመማሪያ መፅሀፉና ከመፅሁ ውጭ | - | - |
| 5 | መርሃ ትምህርቱና የመማሪያ መፅሀፉ ፅህፈት የሚዳብርበትን መማሪያና ዝርዝር ሃሳቦቹን ይዘዋል | | |
| | ሀ. ሙሉ በሙሉ ይዘዋል | | |
| | ለ. በአብዛኛው ይዘዋል | - | - |
| | ሐ.በመጠኑ ይዘዋል | - | - |
| | መ.አልፎ አልፎ ይዘዋል | 1 | 25 |
| | ሠ.ምንም አልያዙም | 3 | 75 |
| | | - | - |

ከላይ በሠንጠረዥ ከቀረበው የመጠይቅ ምላሽ ለመረዳት እንደተቻለው በመማሪያ መፅሀፉ የቀረቡት መልመጃዎች በብዛት የስነ-ፅሁፍ እውቀትን እንደሚያዳብሩ ነው፡፡

በመማሪያ መፅሀፉ ካሉት መልመጃዎች መካከል ለፅህፈት ልምምዱ እገዛ የሚያደርገው መልመጃ ሶስት ነው፡፡ ነገር ግን ለአማርኛ ቋንቋ የተመደበው ክፍለ ጊዜ በሳምንት አንድ ስለሆነ እንኳን ፅህፈትን ለመለማመድ ሌላውንም መልመጃ መስራት እንደማይቻል ገልፀዋል፡፡ ምክንያቱም የፅህፈት ክሂል እንደሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ሁሉ በአንድ ጀንበር የሚለመድ ባለመሆኑ ነው፡፡ ሌላው መርሃ ትምህርቱና የመማሪያ መፅሀፉን ፅህፈት የሚዳብርበትን መመሪያና ዝርዝር ሃሳቦች ስለመያዙ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ አልፎ አልፎ ይዘዋል የሚል ሲሆን መምህራኑም መርሃ ትምህርቱንና የመማሪያ መፅሀፉን ብቻ ተመርኩዘው ፅህፈትን የሚያስተምሩ ስለሆነ በፅህፈት ልምምዱ ላይ ችግር ሊከሰት እንደቻለ ነው፡፡

በአጠቃላይ በስህተት ትንተናው ከተገኙት መረጃዎች ከመምህራኑና ከተማሪዎቹ የመጠይቅ መልሶች እንዲሁም ከተዛማጅ ፅሁፎች የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ተማሪዎቹ ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች ምክንያቶቹ በመጀመሪያ የተማሪው ለትምህርቱ ወይም ለቋንቋው ተነሳሽነት አለመኖር በመቀጠል መርሃ ትምህርቱና የመማሪያ መፅሀፍ አዘጋጃጀት፣ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጠው ክፍለ ጊዜ ማነስ፣ የመምህራኑ የማስተማር ዘዴና የተማሪዎቹ ቁጥር መብዛትና መልመጃዎቹ በወቅቱ ታርመው አለመመለሳቸው.... ሲሆኑ በጥቅሉም የመማር ማስተማር ሂደት እንደ አንድ የስህተት ምንጭ ይሆናል የሚሉ ናቸው፡፡

## 4.3.4. ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች

ተማሪዎቹ ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው ከታሰቡት የስህተት ምንጮች በተጨማሪ የስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ተፅዕኖ ተማሪዎቹ ለፈፀሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለማወቅ ተሞክሯል፡፡

አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ለቋንቋው አሉታዊ አመለካከት የሚኖራቸው ከሆነ ቋንቋውን የመልመድ ፍላጎት ስለሚቀንስ ስህተት የመፈፀም አዝማሚያ ሊጨምር ይችላል፡፡ ነገር ግን ተማሪዎቹ ለሁለተኛ ቋንቋ አወንታዊ አመለካከት ካላቸው ቋንቋውን የመማርና የማወቅ ፍላጎት ስለሚጨምር ስህተት የመስራት ሁኔታ ሊቀንስ ይችላል ሲሉ Norish /1992:18/ ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎቹ ማህበራዊ መቼት ማለትም በአካባቢው ያለው ማህበረሰብ ለታለሚው

ቋንቋ የሚኖረው አመለካከት በተማሪዎቹ ቋንቋውን በመማር ሂደት ላይ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሣድር እንደሚችል ምሁራን ይጠቁማሉ፡፡

ከስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች አንፃር በኦሮሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን አመለካከት ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋን ለመማርም ሆነ ለማወቅ ተጠኚ ተማሪዎቹ ያላቸውን ፍላጎት ለመረዳት ከመምህራኑና ከተማሪዎቹ የመጠይቅ መልሶች የተገኙት መረጃዎች እንደሚጠቁሙት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ሲገልፁ የተወሰኑ ተማሪዎች ደግሞ ዝቅተኛ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ፅህፈትን ለመለማመድ ያለቸው ፍለጎትም ዝቅተኛ አንደሆነ ከመጠይቁ ከተገኘው ምላሽ መገንዘብ ተችሏል፡፡

ሌለው ያደክበት ወይም ያደግሽበት ማህበራዊ እና ባህላዊ ሁኔታዎች ከአማርኛ ተናጋሪዎች ባህል ጋር ያለው መራራቅ ምን ያህል እንደሆነ ተጠይቀው አብዛኞቹ ተማሪዎች ያደጉበት ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ከአማርኛ ተናጋሪዎች ባህል ጋር ያለው መራራቅ ከፍተኛ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ይህም ተማሪዎቹን ለስህተት ያጋልጣቸዋል ብሎ መገመት አያዳግትም፡፡ ከዚህም ባሻገር የተጠኚ ተማሪዎቹ ወላጆች ታላሚውን ቋንቋ ለሚናገር ማህበረሰብ ዝቅትኛ የሆነ አመለካከት እንዳላቸው ከተማሪዎቹ ምላሾች መረዳት ተችሏል፡፡ በተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት ውስጥ ለማየት እንደተሞከረው ወላጆች ታላሚውን ቋንቋ ለሚናገር ማህበረሰብና ለቋንቋው አሉታዊ አመለካከት የሚኖራቸው ከሆነ ተፅዕኖው ታላሚውን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩት ልጆች ላይም ሊንፀባረቅ እንደሚችል ይገመታል፡፡ ስለዚህ ቋንቋውን በመማር ሂደት በርካታ ስህተቶች ሊፈፀሙ ይችላሉ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ለመምህራኑ ተማሪዎቻቸው ለትምህርቱ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ተማሪዎቹ ከሰጧቸው ምላሾች ጋር በጣም ተመሳሳይነት እንዳለው ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህም ሁለት መምህራን በጣም ዝቅተኛ ሲሉ ሁለቱ ደግሞ ዝቅተኛ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ ለተማሪዎቹና ለመምህራኑ በቀረቡላቸው መጠይቆች የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚያስረዱት ተማሪዎቹ በስነ-ልቦና ተፅዕኖ ምክንያት በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ ስህተት ሊፈፅሙ እንደሚችሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳብ

### 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ ተብሎ የተጠና ነው። ጥናቱ የተካሄደው በምስራቅ ሐረርጌ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች መካከል በሀሮማያና በአዴሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ በኦሮሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። እነዚህ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ዋና ዋና የስህተት አይነቶች የትኞቹ ናቸው? ብዛታቸውና ድግግሞሻቸው ምን ያህል ነው? የሚሉት የጥናቱ የመጀመሪያ መሰረታዊ ጥያቄዎች ሲሆኑ ሁለተኛው መሰረታዊ ጥያቄ ደግሞ ተማሪዎቹ ለፈፀሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉት እነማን ናቸው? የሚል ነው። እዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችሉ መረጃዎች በድርሰት መልመጃዎች እና በመጠይቆች አማካይነት ተሰብስበዋል።

### ሀ. በተማሪዎቹ የተፈፀሙ ዋና ዋና የስህተት አይነቶች

በዚህ ጥናት በተማሪዎቹ ድርሰት ውስጥ አራት ዋና ዋና የስህተት አይነቶች እንደተፈፀሙ ለማወቅ ተችሏል። እነዚህ ስህተቶችም የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች፣ የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶችና ከፅንሰ ሃሳብ ጋር በተያያዙ የሚፈፀሙ ስህተቶች ናቸው። በእያንዳንዱ ዋና ዋና የስህተት አይነቶች ውስጥም በርካታ ንዑሳን የስህተት አይነቶች ተካተዋል።

የቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ከፍተኛው የስህተት መጠን የታየበት ሲሆን በድርሰቶቹ ውስጥ በአጠቃላይ ከተቆጠሩት ስህተቶች መካከል 7752 ያህሉን ይዟል። አማካይ የስህተት ድግግሞሹም 24.72% ነው። ከቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ውስጥ ከፍተኛውን የስህተት መጠን የያዘው ደግሞ የቃላት አመራረጥ ላይ ሲሆን ቀጥሎ አላስፈላጊ ድግግሞሽ፣ ግድፈት፣ ጭመራ፣ ኢመደበኛ ቃላትና ሐረጋትን ከመጠቀም ጋር የተያያዙ ስህተቶች በስፋት ታይተዋል። በቃላት አመራረጥ እና አጠቃቀም ንዑስ የስህተት ምድብ ውስጥ ተገቢ ቃላትን ካለመጠቀም የተነሳ

የተፈፀሙ ስህተቶች፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ አማካይነት ቃላትን በተሳሳተ መንገድ የመጠቀም፣ ተቀራራቢ ፍች ያላቸውን ቃላት ለመጠቀም ሲሞክሩ የተፈፀሙ ስህተቶች ተስተውለዋል፡፡ ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በዚህ አይነት ሁኔታ የተፈጠሩ ስህተቶች 2291 ሊሆኑ ችለዋል፡፡

በአላስፈላጊ ድግግሞሽ ምክንያት የተከሰቱ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች በሚለው ንዑስ የስህተት ምድብ ውስጥ ተጠኚ ተማሪዎች ያለበቂ ምክንያት ቃላትንና ሀረጋትን በመደጋገማቸው የተነሳ የተፈጠሩትን ስህተቶች ለማየት ተችሏል፡፡ በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ በዚህ አይነት ሁኔታ የተፈፀሙ ስህተቶች መጠን 1532 ሆኗል፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 8.47% አማካይ ስህተቱ 3.22% ሲሆን አማካይ የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 4.87% ሊሆን ችሏል፡፡

በተጠኚ ተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ መግባት የነበረበትን ቃል ወይም ሀረግ በመግደፍ ስህተቶችን ፈፅመዋል፡፡ በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ ተፈላጊውን ቃል ወይም ሀረግ በመግደፍ የተፈፀሙ ስህተቶች ብዛት 1322 ሲሆን ይህም በመቶኛ ሲሰላ 7.31% ነው፡፡ አማካይ ስህተቱ 2.78% የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 4.21% ሊሆን ችሏል፡፡ ሌላው ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ጥቂት የማይባሉ ስህተቶች ከጭመራና ኢመደበኛ ቃላትና ሀረጋትን ከመጠቀም የተነሳ እንደተፈጸሙ ለማየት ተችሏል፡፡

የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች በሚለው ስር በጠቅላላው 3785 ያህል ስህተቶች የታዩ ሲሆን ይህም ከጠቅላላ ስህተት ውስጥ 20.93% ነው፡፡ አማካይ የስህተት ድግግሞሹም 12.07% ሆኗል፡፡ ይህ የስህተት አይነት ከቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ቀጥሎ ከፍተኛውን ቁጥር የያዘ የስህተት አይነት ነው፡፡

በስህተት ምድቡ ውስጥ ካሉት ንዑሳን የስህተት አይነቶች መካከል የዐረፍተ ነገር ስምሙነት ከፍተኛውን ቁጥር የያዘ ሲሆን ይህም በመቶኛ ሲሰላ 8.09% አማካይ የስህተት ድግግሞሹም፣ 4.66% ሊሆን ችሏል፡፡ የአረፍተ ነገር ስምሙነት ሲባልም የቁጥር ስምሙነት ስህተቶች፣ የፆታ ስምሙነት ስህተቶች፣ የመደብ ስምሙነት ስህተቶች እና የጊዜ ስምሙነት ስህተቶች ያካትታል፡፡

በሠንጠረዥ 4 እንደተመለከተው ከአጠቃላዩ የስህተት ብዛት ውስጥ 8.09 በመቶ የታላሚውን ቋንቋ የአረፍተ ነገር ስምሙነት ስርአት ባለመጠበቅ የተፈፀሙ ስህተቶች ናቸው፡፡

የመስተአምርና የተሳቢ አገባብ ስህተቶች ከአረፍተ ነገር ስምሙነት ቀጥሎ በሁለተኛነት የሚገኝ ሲሆን የያዘው የስህተት መጠን 5.41% ነው፡፡ ጠቅላላ የስህተት መጠኑም 979 ሲሆን አማካይ ስህተቱ 2.06%፣ የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 3.12% ነው፡፡

የአጣማሪዎችን አገባብ ባለማወቅ የተፈፀሙ ስህተቶች ከአጠቃላዩ የስህተት ብዛት ውስጥ 4.71% ሲሆን አማካይ የድግግሞሽ መጠኑ 2.71% እንደሆነ ከጥናቱ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ስህተቱም በአብዛኛው የአጣማሪዎችን ሰዋሰዋዊ አገልግሎት በሚገባ ካለማወቅ የተነሳ የተፈፀሙ መሆናቸውም ተስተውሏል፡፡

ከቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች መካከል የመስተዋድድ አገባብ ስህተቶች ዝቅተኛውን የስህተት መጠን የያዘ ሲሆን ይህም በመቶኛ 2.71% ነው፡፡ ጠቅላላ የስህተት መጠኑ 490 ሲሆን አማካይ ስህተቱ 1.03%፣ የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 1.56% ሊሆን ችሏል፡፡ የመስተዋድድ አገባብ ስህተት ሲባልም ተገቢን መስተዋድድ በተገቢው ቦታ ያለመጠቀም፡፡ መስተዋድዶችን መግደፍና መስተዋድዶችን እርስ በርስ በማተካካት የተፈጠሩ ስህተቶችን ያካትታል፡፡

የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ በብዛት ታይተዋል፡፡ በአጠቃላይ በድርሰቶቹ ውስጥ ከተቆጠሩት ስህተቶች ውስጥ 3760 ያህሉን ሸፍኗል፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 20.78% ፣ አማካይ ስህተቱ 7.91% ሲሆን አማካይ የስህተት ድግግሞሹ 11.98% ያህል ነው፡፡ ከስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ውስጥ የመጀመሪያውን ስፍራ የያዘው የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ሲሆን ይህም 12.97% ያህሉን ሸፍኗል፡፡ በመቀጠልም የታየው የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ስህተት ሲሆን ይህም 7.82% ሊሸፍን ችሏል፡፡

በአራት ነጥብ አጠቃቀም ላይ የታዩ ስህተቶች በአራት ነጥብ ፋንታ ሁለት ነጥብ በመጠቀም የተፈፀሙ ስህተቶችና በተገቢ ቦታ አራት ነጥብ ባለመጠቀም የተፈፀሙ ስህተቶች ናቸው፡፡ በነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ላይ በነጠላ ሰረዝ ፋንታ ሁለት ነጥብ በመጠቀም እንዲሁም የቀስት ምልክት በማስገባት ስህተት ሊፈፀሙ ችለዋል፡፡

## ለ. የስህተት ምንጮች

በኦሮሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ለፈፀሟቸው ስህተቶች ምንጭ ናቸው ተብለው የሚታመኑት የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የአፍ መፍቻ ተፅዕኖ፣ የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶችና ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ናቸው። ከተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ የተገኙ መረጃዎችና በመምህራኑና በተማሪዎቹ የተሞሉ መጠይቆችም ይህንኑ የሚያጠናክሩ ናቸው።

የተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ በተለይም በታላሚው ቋንቋ ያቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ወዘት ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ የተነሳ የተፈፀሙ ስህተቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይታመናል። ከቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች መካከልም የመስተዋድዶች መገደፍ ከተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ለመገመት ተችሏል። ተጠኚ ተማሪዎች ከታላሚው ቋንቋ ውስብስብ ባህሪይ የተነሳ ስህተቶች ሊፈፅሙ እንደቻሉም ተገምቷል። በቋንቋ አወቃቀር የስህተት ምድብ ውስጥ የአረፍት ነገር ተዋቃሪዎች ስምሙነት ጉድለት፣ የአረፍት ነገር አወቃቀር ቅደም ተከተል ስህተቶች የታላሚውን ቋንቋ ህግጋት በሚገባ ባለመማራቸው ምክንያት የተፈጠሩ ስህተቶች ናቸው ብሎ መገመት ይቻላል።

ሌላው የስህተት ምንጭ ሊሆን ይችላል ተብሎ የተገመተው ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ያላቸው ዝቅተኛ አመለካከትና ለትምህርቱ ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆን ከዛም ባሻገር ተማሪዎቹ ትምህርቱን የሚጀምሩት ከአምስተኛ ክፍል መሆንና የክፍል ጊዜው በጣም ማነስ ለስህተት መፈጠር ምንጮች ሊሆኑ እንደሚቸሉ ነው።

## 5.2. የመፍትሄ ሃሣብ

በድርስት ትንትናው ወቅት ተጠኚ ተማሪዎቹ የተለየዩ አይነት ስህተቶችን እንደፈፀሙ ለማወቅ ተችሏል ። ስህተቶቹ የበርካታ ተፅዕኖዎቹ ድምር ውጤት እንደሆኑ ከመረጃ ትንተናው ለመገንዘብ ተችሏል። እነዚህን ስህተቶች መቅረፍ ይቻል ዘንድ አጥኚዋ የሚከተሉትን የመፍትሄ ሃሳቦች አቅርባለች።

- ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ከታች ክፍል ማለትም ከአንደኛ ክፍል እንዲጀምሩ ቢደረግ

- አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ክሂላቸው በሚገባ ይዳብር ዘንድ ለቋንቋው ትምህርት በቂ ጊዜ ተመድቦ እንዲማሩ ቢደረግ፡፡
- ተማሪዎቹ መጀመሪያ ለትምህርቱ አወንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ማለትም ለቋንቋው ካላቸው የተሳሰተ ግንዛቤ እራሳችውን አፅድተው ትምህርቱን እንደማንኛውም ትምህርት እንዲመለከቱት የተለያዩ የማነሳሻ ዘዴዎች ተግባራዊ ቢደረጉ፡፡
- መምህራን በተማሪዎቻቸው ድርሰት ውስጥ የሚፈፀሙትን የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር እና የመሳሰሉትን ስህተቶች በመለየት ስህተቶች የሚያስከትሏቸውን ችግሮች በማስረዳትና ተደጋጋሚ የፅህፈት ልምምዶችን እንደያድርጉ በማበረታታት ተማሪዎቹ የፅህፈት ክሂልን እንዲያዳብሩ ከፍተኛ ጥረት ቢደረግ፡፡

የፅህፈት ክሂል እንደሌሎች ክሂሎች ሁሉ በአንድ ጀምበር የሚሻሻል ባለመሆኑና ስህተቶቹንም መቅረፍ የሚቻለው ተከታታይነት እና ቀጣይነት ባለው የፅህፈት ልምምድ ሂደት በመሆኑ መምህራኑ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ፅህፈትን ቢያለማምዷቸው የተሻለ ነው፡፡

- በትምህርት መሣሪያዎች ዝግጁት ወቅት የተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ እና ታላሚው ቋንቋ ግንዛቤ ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ ቢመቻች፡፡
- ታላሚውን ቋንቋ ለማስተማር ተብለው የሚዘጋጁ መረሃ ትምህርቶች፣ የመማሪያና የማስተማሪያ መፅሀፎች እንደዚሁም ሌሎች የትምህርት መሣሪያዎች የተማሪዎቹን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከግንዛቤ ባስገባ መልኩ ሊዘጋጁ ይገባል፡፡ ይህም አፍ የፈቱበት ቋንቋ ከታላሚው ቋንቋ በምን እንደሚለይ አፍ መፍቻ ቋንቋው በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ሊያስከትለው የሚችለው ተፅዕኖ ምን ሊሆን እንደሚችል ተፅዕኖውንም ለመቅረፍ ምን ምን ስልቶቹን መቀየስ እንደሚቻል ማስተዋልን ያጠቃልላል፡፡
- ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ በሚሰጣቸው ትምህርት ብቻ ቋንቋውን በሚገባ ላይለምዱት ይችላሉ፡፡ ስለዚህም የተማሪዎቹን ችሎታ፣ ፍላጎት እና ቋንቋን ያገናዘበ አጋዥ መፅሀፍ በማዘጋጀት ተማሪዎቹ እንዲገለገሉበት ቢደረግ ቋንቋውን በመልመድ ሂደት ትልቅ ለውጥ ሊመጣ ይችላል፡፡

# ዋቢ መፃህፍት


ልዑል ሰገድ አሰፋ (1997)፡፡ "በወላይትኛና ሲዳምኛ ተናጋሪዎች የአማርኛ ድርሰት ውስጥ የታዩ ስህተቶችና የስህተቶች ምንጭ ትንተና፡፡" የአርት ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡

መሰሉ መንግስቱ (1991)፡፡ "የቸሀኛ አፈፊት ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ የሚያንፀባርቋቸው ስነ-ልሳናዊ ባህሪያት፡፡" የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ የሁኒቨርስቲ፡፡

ማረው አለሙ (1987)፡፡ "በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍል በ2ኛ አመት ተማሪዎች በግልና በቡድን የሚፃፉ በሳል ድርሰቶች ንፅፅራዊ ግምገማ ጥናት" /የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)" አዲስ አበባ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፡፡ (ያልታተመ)

ምህረት ሳዳም (1998)፡፡ "በዋቻም አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሀድይኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ትንተና፡፡" (ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት) አዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ፡፡

ሰለሞን ተሰማ (1987)፡፡ "የብጤ አርማት ተግባራዊነትና ውጤታማነት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ገላጭ ጥናት፡፡" (የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)፡፡ አዲስ አበባ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፡፡ (ያልታተመ)

ባዬ ይማም (1987)፡፡ **የአማርኛ ሰዋሰው**፡፡ አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

ተክሌ አሰፋው (1989)፡፡ "በቡታጅራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፋቸውን በመስቃንኛ የፈቱ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ጥናት፡፡" የአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡

ተገኝ አህመድ (2000)፡፡ "አፋቸውን በክፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው

ስህተቶች ትንተና።" አርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ትምህርት ሚኒስቴር (1970)። "የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ስርአተ ትምህርት ከ7-12 ክፍል።" ስርአተ ትምህርትና ሱፐርቪዥን መምሪያ የአማርኛ ትምህርት ቡድን የተዘጋጀ፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)።

ነጋሳ እጀታ (1965)። "በ1962 ዓ.ም የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና ላይ በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚታዩ የስህተት አይነቶች።" የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ፅሑፍ፣ አ.አ.ዩ. አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

አለማየሁ ፀጋዬ (1986)። በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚፈፀሙ ስህተትና ዋና ዋና የስህተት ምንጮች ትንተናንና የአርትስ ማስተርስደ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አ.አ.ዩ.

አማረ ስውነት (1996)። "በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በማርኛ ቋንቋ ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስነ-ልሳናዊ ስህተቶች።" የአርትስ ማስተርስ ድግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

አብይ አሰፋ (1997)። "በአዲስ ከተማ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በደብረሃይል ቅዱስ ራጉኤል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ትንተና።" የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ዘውድ ምልከት (1996)። "በአዊ መስተዳድር ዞን በአዊኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ሰዋሰዋዊ ስህተቶች፡" የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ይልማ ከበደ (1956)። "በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቋንቋቸው ኦሮሞኛ የሆኑ ተማሪዎች የሚያደርጉት የአማርኛ ስህተት።" የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ የቀረበ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ደብሬ ተሰማ (1990)። "በኦሮሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸው ዋና ዋና የስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና።" የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

All Wright, Dandk. Baily (1991). *Focus on the language Classroom: An Introduction to Classroom Research to Language Teachers*. Cambridge University Press.

Broughton, G. etal. (1978). *Teaching English as a Foreign Language*. London, Rutledge.

Brown, H.D. (1994). *Principles of Language Learning and Teaching*. New Jersey: Prentice Hall.

Corder, S. (1967) "The Significance of Learner's. Error." *IRAL*. Vol. 12 No.1 P.11-27.

Corder, S. (1973) *Introducing Applied Linguistics*. London: Penguin Groups Ltd.

Corder, S. (1974). "The Significance of Learners Errors." In J.C. Richards (ed.) *Error Analysis: Perspectives on Second Language Acquisitions*. London and New York: Longman Group UK Limited.

Day, S. (1984). *The Writers Work Book*. New York: Macgraw Hill Company.

Dulay, H.etal. (1982). *Language Two*. Oxford: Oxford University Press.

Edge, J. (1989). *Mistakes and Correction*. London: Longman.

Ellis, R. (1989). *Understanding Second Language Acquisitions*. 5th ed. Oxford: Oxford University Press.

Ellis, R. (1994). *The Study of Second Language Acquisitions*. Oxford: Oxford University Press.

Heaton, J.B. (1988). *Writing English Language Tests.* New York: Longman Inc.

Hundson, G. (1976). "Highland East Cushitic". In M.L. Bender (ed) *The Non-Semitic Languages in Ethiopia.* Michigan Michigan State University.

Jakson, H. (1987). "The Value of Error Analysis and Its Implications for Teaching and Therapy with special Reference to Panjabi Learners" In Abdurham (ed.) *Bilingualism and Bilingual.* Oxford: Nter - Nelson Publishing Company Ltd.

James, C. (1991). *Contrastive Analysis*: New York: Longman.

James, C. (1996). *Contrastive Analysis.* 13th ed. New York. Longman Group UK Limited.

Jhonson, C. (1976) 'Mistake Correction". *ELT.* Vol. 33 No. 3 P. 20.

Johansson, S. (1975b). "The use of Error Analysis and Contrastive" INJ. Richards (ed) *Error Analysis.* London: Longman.

Lado, R. (1964). *Linguistic Across Cultures.* Ann Arbor: University of Michigan Press.

Lengo Nsakala (1995). *English Teaching Forum.* Vol. 33. No. 3 P.20.

Lindmann, Beate. (1996). "The Concept of Error in an Analysis of Learner Language." *The International Abstracting Journal for Language. Teachers and Applied Linguists.* Vol. 29/3 No. 112.

Littlewood, W. (1986). *Foreign and Second Language Learning.* Language Acquisition Research and its Implications for the Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Littlewood, W. (1994) *Foreign and Second Language Learning.* Cambridge: Cambridge University Press.

Lott, D. (1983). "Analyzing and Counteracting Interference Errors" *ELT* Vol. 37. No. 3 P. 256-261.

McGroaty, M. (1996). "Language Attitudes, Motivation and Standards" In S. Mukay and N. HornBerger (eds.) *Sociolinguistics and Language Teaching*. New York: Cambridge University Press.

Negara, E.A. (1983). "Non-contrastive Errors in African English: Types and Significance." *IRAL*. Vol. 16 No. 1 P. 1-17.

Norrish, John. (1983). *Language Learners and their Errors*. London Macmillan Publishers Ltd.

Norrish, John. (1990). *Language Learners and their Errors*. London Macmillan Publishers Ltd.

Norrish, John. (1992). *Language Learners and their Errors*. London Macmillan Publishers Ltd.

Raimes, A (1991). "Out of the moods: Tradations in Teaching of Writing" *Tesol Quarterly*. Vol. 25 No. 4 P. 407- 430.

Richards, J.C (1974) *Error Analysis: Perspectives on Second Language Acquisition*. London: Longman Group Ltd.

Richards, J.C and G.P. Samposn (1990). "The Study of Learners English." In J.C.Richards (ed). *Error Analysis.* London: Longman Group Ltd.

Sharma, S.K. (1979). *Error Analysis: why and how*? Washington: Prentice Hall.

Sharma, S.K. (1986). *Error Analysis: why and How*? Washington: English Language Programs Division Bureau of Educational and Cultural Affairs.

Spolisky, B. (1989). *Conditions for Second Language Learning*. Oxford: Oxford University Press.

White, R. (1994). *The English Teacher's Hand Book*. Hongkong: Thomas Nelson and Sons Ltd.

Widdowson, H.G. (1979). *Teaching Language as Communication*. Oxford: Oxford University Press.

# አበሪዎች

## በተማሪዎች የሚሰራ የድርሰት መልመጃ

**መመሪያ፡-** ከዚህ በታች ከቀረቡት ርዕሶች መካከል በይበልጥ አውቀዋለሁ ብዙ ሊያፅፈኝ ይችላል የምትለውን (የምትይውን) አንዱን ርዕስ ብቻ በመምረጥ ከአንድ ገፅ ያላነሰ ድርሰት በክፍል ውስጥ ፃፍ /ፃፊ/ ድርሰቱን ለመፃፍ የተፈቀደው ጊዜ 50 ደቂቃ ነው፡፡

ማሳሰቢያ፡-

ሀ. በድርሰት ወረቀታችሁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም

ለ. አፍ የፈታችሁበትን ቋንቋ መፃፍ አትርሱ

አማራጭ ርዕሶች

1. የትምህርት ጥቅም
2. የወደፊት ምኞቴ
3. የጫት ጥቅም
4. የሐረርጌ ባህላዊ ምግብ
5. ሸዋሊድ
6. የወባ በሽታ
7. ትምህርት ቤቴ
8. የገዳ ሥርአት

## በቋንቋዎች ጥናት ተቋም
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል
## በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

### ለተከበራችሁ ተማሪዎች !

በመጠይቁ የተዘጋጀው አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸውን የስህተት አይነቶችና የስህተቶቹን ምንጮች ለማጥናት ለተጀመረው ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡

ከዚህ ጥናት የሚገኘው ውጤትም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ፅህፈትን በሚለማዱበት ጊዜ እንቅፋት የሚሆኑባቸውን ነገሮች ለመቀነስ ብሎም ለማቃለል ያግዛል ተብሎ ይታመናል፡፡

ለጥናቱ ዓላማ መሳካት የእናንተ ትክክለኛውንና ተገቢውን መረጃ መስጠት እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ በመሆኑም መጠይቁን በጥንቃቄ አንብባችሁ ትክክለኛውን መልስ በመመለስ እንድትተባበሩ በትህትና እንጠይቃለን፡፡

ስለትብብራችሁ አስቀድመን እናመሰግናለን፡፡

## ክፍል አንድ

አጠቃላይ መረጃ

መመሪያ፡- ትክክለኛውን መልስ በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ ፃፍ/ፊ/

1.1. ፆታ ---------

1.2. ዕድሜ --------

1.3. አፍ የፈታህበት /የፈታሽበት/ ቋንቋ -----------

1.4. ከጓደኛ ወይም ከዘመድ ጋር ደብዳቤ የምትለዋወጥበት /ጭበት/ ቋንቋ -----

## ክፍል ሁለት

መመሪያ አንድ፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ሊሆን ይችላሉ ተብለው የታሰቡ አማራጮች ቀርበዋል፡፡ እያንዳንዱን ጥያቄ በጥንቃቄ ካነበብክ (ሽ) በኋላ ለጥያቄው ተገቢ መልስ ይሆናል ያልከውን (ያልሽውን) መርጠህ (ሽ) ከፊት ለፊት ያለውን ፊደል አክብበው (ቢው)

1. በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ክፍል ውስጥ ትገኛለህ /ሽ/?

   ሀ. አዘውትሬ እገኛለሁ

   ለ. አብዛኛውን ጊዜ እገኛለሁ

   ሐ. በመጠኑ እገኛለሁ

   መ. አልፎ አልፎ እገኛለሁ

   ሠ. በወር አንድ ጊዜ እገኛለሁ

2. በተራ ቁጥር 1 ለቀረበው ጥያቄ መልሱ ከሐ- ሠ ያለው ከሆነ ምክንያቱ ምንድነው?

   ሀ. የትምህርቱ አሰጣጥ ስለማይስብ

   ለ. የቤት ስራ በወቅቱ ስለማልሰራ

   ሐ. ባልማርም ስለማውቀው

   መ. በአብዛኛው የማልገለገልበት በመሆኑ

   ሠ. ሁለተኛ ቋንቋዬ በመሆኑ

3. የአማርኛን ቋንቋ ትወደዋለህ/ትወጅዋለሽ/?

ሀ. ሙሉ በሙሉ እወደዋለሁ　　　　መ. በከፊል እወደዋለሁ

ለ. በአብዛኛው እወደዋለሁ　　　　ሠ. አልወደውም

ሐ. በመጠኑ እወደዋለሁ

4. በተራ ቁጥር ‹‹3›› ለቀረበው ጥያቄ መልስህ /ሽ/ ሀ ወይም ለ ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልሃል?

ሀ. ከማህበረሰቡ ጋር በስፋት ስለምግባባበት　　መ. ትምህርቱ በሚገባ ስለሚሰጥ

ለ. የስራ ቋንቋ በመሆኑ　　　　ሠ. ለመማር ቀላል በመሆኑ

ሐ. የራሴን ማንነት ስለምገልፅበት

5. በተራ ቁጥር ‹‹3›› ለቀረበው ጥያቄ መልስህ /ሽ/ ሐ፣መ ወይም ሠ ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልሃል?

ሀ. ሁለተኛ ቋንቋ በመሆኑ　　　　መ. በተፅዕኖ እንድማር ስለተደረገ

ለ. ትምህርቱ ስለማይገባኝ　　　　ሠ. ብማርም ባልማርም ስለማውቀው

ሐ. በኑሮየ ውስጥ ብዙ ስለማልጠቀምበት

6. በኦሮሞኛ ቋንቋ አፉን /አፏን/ የፈታ /የፈታች/ ተማሪ በአማርኛ ቋንቋ ፅህፈትን ለመለማመድ ፍላጎት አለው /አላት /ብለህ/ሽ/ ትስማማለህ/ያለሽ/?

ሀ. እጅግ በጣም እስማማለሁ　　　　መ. አንዳንድ ጊዜ እስማማለሁ

ለ. በጣም እስማማለሁ　　　　ሠ. ምንም አልስማማም

ሐ. በመጠኑ እስማማለሁ

7. መምህሩ አንቀፅ ወይም ድርሰት መፃፍ የሚያስችሉ የክፍልና የቤት ስራዎችን ሰጥተው ያውቃሉ?

ሀ. ዘወትር ይሰጣሉ　ለ. በአብዛኛው ይሰጣሉ　　ሐ. በመጠኑ ይሰጣሉ

መ. አንዳንድ ጊዜ ይሰጣሉ　ሠ. ሰጥተው አያውቁም

8. መምህሩ የሚሰጡትን የክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራ አርመው ይመልሳሉ?

ሀ. ሙሉ በሙሉ ይመልሳሉ　　　　መ. አንዳንድ ጊዜ ይመልሳሉ

ለ. በአብዛኛው ይመልሳሉ　　　　ሠ. መልሰው አያውቁም

ሐ. በመጠኑ ይመልሳሉ

9. በተራ ቁጥር ‹‹10›› ለቀረበው ጥያቄ መልሱ ‹መ› ወይም ‹ሠ› ከሆነ ምክንያቱ ምን ይሆናል ተብሎ ይገመታል?

ሀ. የተማሪዎች ቁጥር በርካታ በመሆኑ

ለ. መምህሩ ለማረም ስለሚሳነፉ

ሐ. የማረም ስራ አድካሚና አሰልቺ በመሆኑ

መ. የተማሪዎች ስራ ስለማይጥማቸው

ሠ. ምክንያቱ አይታወቅም

10. መምህሩ ፅህፈትን በሚያለማምዱበት ጊዜ ይበልጥ ትኩረታቸው ምን ላይ ነው /መልሱ ከአንድ በላይ ሊሆን ይችላል/?

ሀ. በዐ.ነገር ግንባታ ነው

ለ. በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ ነው

ሐ. በቃላት አጠቃቀም ላይ ነው

መ. በፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ላይ ነው

ሠ. በአስተዋፅኦ አነዳደፍ ላይ ነው

11.በትምህርት ቤቱ ውስጥ የድራማና የስነ-ፅሁፍ ክበብ የጋዜጠኞች ክበብ የፀረ ኤድስ ክበብ እንቅስቃሴ የሚካሄድ ከሆነ ለፅህፈት ልምምዱ ጠቀሜታው ምን ያህል ነው?

ሀ. ሙሉ በሙሉ ጠቀሜታ አለው

ለ. በአብዛኛው ጠቀሜታ አለው

ሐ. በመጠኑ ጠቀሜታ አለው

መ. አንዳንድ ጊዜ ጠቀሜታ አለው

ሠ. ጠቀሜታ የለውም

12.አንዳንድ ተማሪዎች የሰሩትን የፅህፈት መልመጃ እንዲያነቡ ሲጠየቁ ፈቃደኛ የማይሆኑበት ምክንያት ምን ይመስልሃል /ሽል/?

ሀ. መሳሳት እንደ ድክመት ስለሚቆጥሩት ደካማ ላለመምሰል

ለ. ስህተት ቢፈፅሙ በተማሪዎች ፊት እንዳይሳቅባቸውና እንዳይፌዝባቸው

ሐ. ከስህተት መማር መቻሉን ባለመገንዘባቸው

መ. በሚያነቡበት ጊዜ ቢሳሳቱ ስለሚያፍሩ

13. የተማሪዎቹ መልመጃዎች ሲታረሙ ስህተት ቢፈጠር መምህሩ ምን ያደርጋሉ?

ሀ. ስህተት መፈፀሙ የማይቀር መሆኑን ያስገነዝባሉ

ለ. ስህተት ተፈጥሮአዊ የቋንቋ መማር ሂደት አንዱ አካል እንደሆነ ይገልፃሉ

ሐ. ተማሪዎቹ ስህተት የማይፈፅሙበትን መንገድ ያመቻቻሉ

መ. ስህተት መፈፀም አስነዋሪና አስቀያሚ እንደሆነ ይገልፃሉ

ሠ. ተማሪ ተሳሳተ ማለት መምህሩ ምንም እንዳልሰራ ተቆጠረ ማለት ነው በማለት ይናደዳሉ

14.ተማሪዎች ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሙትን ስህተት ከተማሪዎቹ ድክመት የመጣ ነው ብለህ/ሽ/ የምትገምት /ቺ/ ከሆነ ለድክመቱ መንስኤው ምን ይሆናል ተብሎ ይታሰባል?

ሀ. ከተማሪው ውስጣዊና ውጫዊ የግል ችግር

ለ. የትምህርቱን አውድ በመሳቱ

ሐ. የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ ለቋንቋው ትምህርት ያልተመቻቸ በመሆኑ

መ. በድካምና በሰውነት መዛል በሚፈጠር ዝንጋታ

ሠ. የትምህርት አሰጣጡ ስለማይስበው

15.በጥቅሉ ተማሪዎች ፅህፈትን በሚለማመዱበት ጊዜ ለሚፈጠሩ ስህተቶች የስህተት ምንጮች ናቸው ተብለው የሚገመቱት ከሚከተሉት ውስጥ የትኞቹ ናቸው?

ሀ. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ሠ. የመምህራን የአሰተራረም ጉድለት

ለ. የሁለተኛ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርአት አስቸጋሪነት

ሐ. የመምህራን የማስተማር ጉድለት

መ. የመማሪያ መፅሀፍ ለፅህፈት ትኩረት ባለመሰጠቱ

16.ፅህፈትን በምትለማመድበት /በምትለማመጅበት/ ጊዜ ችግር የሚያጋጥምህ /ሽ/ ምን ላይ ነው ?

ሀ. የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ መ. የ.ዐ.ነገር አመሰራረት ላይ

ለ. ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ መጠቀም ሠ. የቃላት ፍቺ ላይ

ሐ. የፅንሰ ሃሳብ ቅንብር ላይ. ረ. መደብ አመልካች ምዕላዶችን በትክክል መጠቀም

17.አንተ /አንቺ/ ስህተት በምትፈፅምበት/ሚበት/ ጊዜ ተደጋጋሚ ስህተቶችን የምትፈፅመው /ሚው/ ከላይ በተራ ቁጥር 19 ከተዘረዘሩት ውስጥ የትኞቹ ላይ ነው?

ሀ. ሀ　　　　መ. መ

ለ. ለ　　　　ሠ. ሠ

ሐ. ሐ

18.ዘጠነኛ ክፍል ከመግባትህ/ሽ/ በፊት በተለይም በሰባተኛ እና በስምንተኛ ክፍሎች የአማርኛ መምህር/ሽ/ ፅህፈትን እንድትለማመዱ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስል ነበር?

ሀ. ሁልጊዜ ፅህፈትን እንድንለማመድ ያደርጉ ነበር

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ፅህፈትን እንድንለማመድ ያበረታቱን ነበር

ሐ. ፅህፈትን እንድንለማድ መጠነኛ ጥረት ያደርጉ ነበር

መ. አልፎ አልፎ የፅህፈት (የድርሰት) መልመጃዎችን ይሰጡን ነበር

ሠ. ፅህፈትን እንድንለማመድ አስተምረውን አያውቁም

መመሪያ ሁለት ከዚህ በታች አምስት አማራጭ መመዘኛዎችን የያዙ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄም የሚሰጠው መልስ አንድ ብቻ ሲሆን ከቀረቡት መልሶች መካከል ተገቢ መልስ ነው ብለህ/ሽ/ የምታምንበትን /ኒበትን/ መመዘኛ በመምረጥ መልሱን በተሰጠው ባዶ ሳጥን ውስጥ የ‹√› ምልክት አስቀምጥ /ጪ/

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መመዘኛዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተ ኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| 1 | አንተ/አንቺ በአማርኛ ቋንቋ ፅህፈትን ለመለማመድ ያለህ/ሽ ፍላጎት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 2 | አንተ/አንቺ ከልዩ ልዩ መፃህፍት መፅሄት ጋዜጣዎች ከሬድዮና ቴሌቪዥን ወዘተ... የሰበሰብከውን/ሽውን/ ሃሳብ በራስህ/ሽ/ አባባል ፅሀፊ/ሽ/ ለማቅረብ ያለህ/ሽ/ ፍላጎት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 3 | ፅህፈትን ለመለማመድ የአማርኛ የመምህሩ ጥረት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 4 | የመማሪያ መፅሀፉ መልመጃዎች ፅህፈትን በመለማመድ በኩል ያላቸው አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 5 | የአማርኛ ሳልስና ሳድስ ፊደላትን አጠቃቀም ካለማወቅ የተነሳ ድርሰት ስትፅፍ/ፊ/ የሚያጋጥምህ /ሽ/ ችግር | | | | | |
| 6 | መልመጃዎች ታርመው መመለሳቸው ለፅህፈት ክሂሉ መዳበር የሚሰጠው ጠቀሜታ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 7 | መልጃዎቹ እየታረሙ በሚመለሱበት ጊዜ ተማሪዎቹ የሚፈፅሟቸው የስህተቶች መጠን ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 8 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ አማካኝነት የሚፈፀሙ ስህተቶች መጠን ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 9 | ፅህፈትን በማለማመድ በኩል መምህሩ ያለው ዕውቀት ምን ያህል አጥጋቢ ነው? | | | | | |
| 10 | በትምህርት ቤቱ የተቋቋሙት ልዩ ልዩ ክበባት ለፅህፈት ልምምዱ ያላቸው አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 11 | ያደክበት/ሽበት ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ከአማርኛ ተናጋሪዎች ባህል ጋር ያለው መራራቅ ምን ያህል ነው? | | | | | |

## ክፍል ሶስት

መመሪያ ሶስት ከዚህ በታች የተማሪው ነፃ አስተያየት የሚጠይቁ ጥያቄዎች ቀርበዋል ስለሆነም ጥያቄዎቹን በጥንቃቄ ካነበብክ/ሽ በኋላ ተገቢ መልስ ይሆናል ብለህ/ሽ/ የምትገምቺውን /ገምተውን/ ሃሳብ በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ በሰፊው ፃፍ /ፊ/

1. ፅህፈትን ለመለማመድ ችግር የሚያስከትሉብህ /ሽ/ ነገሮች ካሉ በዝርዝር ግለፃቸው/ጫቸው

   ___________________________________________

2. በፅህፈት ልምምድ ጊዜ የምትፈፅማቸው/ሚያቸው/ የስህተት አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ በዝርዝር ግለፅ /ጪ/

   ___________________________________________

3. በፅህፈት ልምምድ ጊዜ ለሚፈፀሙት ስህተቶች የስህተት ምንጮች ናቸው ተብለው የሚገመቱት ምን ምን ናቸው

   ___________________________________________

4. በጥቅሉ እስከአሁን ድረስ የቀረቡትን መጠይቆች በሚመለከትና የአማርኛን የጽህፈት ትምህርት አስመልክቶ የሚኖርህን /ሽን/ አስተያየት ግለፅ/ጪ/

   ___________________________________________

5. ስለ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚኖርህን/የሚኖርሽን/ አስተያየት በሰፊው ግለፅ/ጪ/

   ___________________________________________

ስለትብብራችሁ በቅድሚያ እናመሰግናለን!

## አ/አ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ት/ቤት

## በቋንቋዎች ጥናት ተቋም

## የኢ/ያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ት/ት ክፍል

## በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን የሚሞላ መጠይቅ

### ለተከበራችሁ መምህራን

ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የሃሮማያና አደሌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸውን የስህተት አይነቶችንና የስህተት ምንጮች ለማጥናት ለተጀመረው ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡

ከጥናቱ የሚገኘው ውጤትም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ፅህፈትን በሚለማመዱበት ጊዜ እንቅፋት የሚሆኑባቸውን ነገሮች ለመቀነስ ብሎም ለማቃለል ያግዛል ተብሎ ይታመናል፡፡

ለጥናቱ አላማ መሳካት ደግሞ የእርስዎ ቅንና ሙያዊ ድጋፍ ተገቢንና ትክክለኛውን መረጃ ለማግኘት የሚኖረው አስተዋፅኦ እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመሆኑም መጠይቁን በጥንቃቄ አንብበው ትክክለኛ ነው ብለው ያሰቡትን መልስ በመስጠት እንዲተባበሩ በትህትና ይጠየቃሉ፡፡

ውድ ጊዜዎን ሰውተው መጠይቁን በመሙላት ላደረጉልን ትብብር አስቀድመን እናመሰግናለን፡፡

### ክፍል አንድ

### አጠቃላይ መረጃ

መመሪያ፡- ትክክለኛውን መልስ በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ ፃፉ

1.1. ፆታ ----------------------------

1.2. አፍ የፈቱበት ቋንቋ ---------------------

1.3. የትምህርት ደረጃ -------------------------

1.4. የሰለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ ----------------

1.4.4. አብይ --------------------------------

1.4.5. ንዑስ --------------------------------

1.5. አሁን በሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ ያለዎት የስራ ልምድ ------------------

1.6. በተመደቡበት የክፍል ደረጃ በሳምንት የሚያስተምሩት ክ/ጊዜ ------------------

## ክፍል ሁለት

*መመሪያ አንድ*

ከዚህ በታች አማራጭ መልሶችን የያዙ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ከነዚህ ጥያቄዎች አንዳንዶቹ ከአንድ በላይ የሆኑ አማራጭ መልሶችን ይዘዋል። ስለሆነም ጥያቄዎቹን በጥሞና ካነበቡ በኋላ ትክክለኛ መልስ የያዘ/ዙ/ የሚመስልዎትን ፊደል ያክብቡ።

1. ለክፍሉ ደረጃ በቀረበው የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረቡት የመልመጃ ይዘቶች በአብዛኛው ተማሪዎቹ የትኞቹን የእውቀትና የክሂል ዘርፎች እንዲለማመዱባቸው ያስችላሉ?

   ሀ. ማዳመጥና መናገርን
   ለ. ማንበብን
   ሐ. ፅህፈትን
   መ. ስነ-ልሳንን
   ሠ. ስነ-ፅህፍን

2. ከላይ በተራ ቁጥር ‹1› ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ ‹ሐ› ከሆነ ተማሪዎችን በይበልጥ በፅህፈት ክሂል ላይ እንዲለማመድ የሚያደርጉት መልመጃዎ የትኞቹ ናቸው ብለው ይገምታሉ?

   ሀ. መልመጃ አንድ
   ለ. መልመጃ ሁለት
   ሐ. መልመጃ ሶስት
   መ. መልመጃ አንድና ሁለት
   ሠ. መልመጃ ሁለትና ሶስት

3. የፅህፈት ትምህርትን የሚስተምሩት በምን ላይ ተመርኩዘው ነው?

   ሀ. በመማሪያ መፅሐፍ ብቻ
   ለ. በመርሃ ትምህርቱ ብቻ
   ሐ. በመርሃ ትምህርቱና በመማሪያ መፅሀፉ
   መ. ከመርሃ ትምህርቱና ከመማሪያ መፅሀፉ ውጭ ከተለያዩ ነገሮች ላይ በተወሰዱ ፅሁፎች

ሠ. በመርሃ ትምህርቱ በመማር መፅሀፉና ከመፀሀፉ ውጭ

4. ከላይ በተራ ቁጥር 3 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎች ‹መ› ወይም ‹ሠ› ከሆነ ተማሪዎችዎች በራዲዮ ካዳመጡት፣ በቴሌቪዥን ካዩትና ከሰሙት፣ በጋዜጣ መፅሔት መፃህፍት ካነበቡት ሃሳብ ሰብስበው ፅፈው እንዲመጡ ያደርጋሉ?

   ሀ. ዘወትር አደርጋለሁ
   ለ. በአብዛኛው ጊዜ አደርጋለሁ
   ሐ. አንዳንድ ጊዜ አደርጋለሁ
   መ. በወር አንድ ጊዜ አደርጋለሁ
   ሠ. ፈፅሞ አላደርግም

5. በተራ ቁጥር 3 ለቀረበው ጥያቄ ‹ሐ› ወይም ‹ሠ› ከሆነ መርሃ ትምህርቱና የመማሪያ መፅሀፉ ፅህፈት የሚዳብርበትን ዝርዝር ሃሳቦችና መመሪያዎች ይዘዋልን?

   ሀ. ሙሉ በሙሉ ይዘዋል
   ለ. በአብዛኛው ጊዜ ይዘዋል
   ሐ. በመጠኑ ይዘዋል
   መ. አልፎ አልፎ ይዘዋል
   ሠ. ምንም አልያዙም

6. ለክፍል ደረጃው በቀረበው የመማሪያ መፅሀፍ ላይ ያለው ፅህፈትን የሚመለከቱ መልመጃዎች ተማሪው ፅህፈቱን በምን አይነት መንገድ እንዲፅፉ ያደርጉታል?

   ሀ. ቃላትን ከቃላት አገጣጥሞ ዐ.ነገር እንዲፅፉ በማድረግ
   ለ. ዐ.ነገር ከዐ.ነገር አገጣጥሞ አንቀፅ እንዲፅፉ በማድረግ
   ሐ. አንቀፅን ከአንቀፅ አገጣጥሞ ድርሰት እንዲፅፉ በማድረግ
   መ. የተፃፉ ድርሰትን አሳጥሮ እንዲፅፉ በማድረግ
   ሠ. አስተዋፅኦ እንዲፅፉ በማድረግ

7. በክፍል ውስጥ ፅህፈት በሚያለማምዱበት ጊዜ ስለ ቃላት አመሰራረትና የዐ.ነገር አገነባብ አስተምረው የውቃሉ?

   ሀ. ዘወትር አስተምራለሁ
   ለ. አብዛኛው ጊዜ አስተምራለሁ
   ሐ. በመጠኑ አስተምራለሁ
   መ. አንዳንድ ጊዜ አስተምራለሁ
   ሠ. እንደሁኔታው አስተምራለሁ

8. ተማሪዎችን ስለ ድርሰት አፃፃፍ ደንብ አስተምረው ያውቃሉ?

ሀ. ዘወትር አስተምራለሁ　　መ. አንዳንድ ጊዜ አስተምራለሁ

ለ. አብዛኛውን ጊዜ አስተምራለሁ ሠ. እንደሁኔታው አስተምራለሁ

ሐ. በመጠኑ አስተምራለሁ

9. ድርሰት /ፅሀፈት/ በሚያስተምሩበት ጊዜ የሚጠቀሙበት መንገድ የትኛው ነው?

ሀ. ርዕስ ሰጥቶ አንቀፅ እንዲመሰርቱ ማድረግ

ለ. አንቀፅ ሰጥቶ ተማሪዎቹ አንቀፁን እንዲመረምሩት ማድረግ

ሐ. አስተዋፅኦ ነድፈው ድርሰት እንዲፅፉ በማድረግ

መ. ተማሪዎቹ የራሳቸውን ርዕስ መርጠው እንዲፅፉ በማድረግ

ሠ. ሁሉንም መንገድ በመጠቀም

10. ተማሪዎቹን የፅሀፈት /የድርሰት/ ትምህርት ለማስተማር የትኛው ዘደ የተሻለ ይመስልዎታል ?

ሀ. የድርሰት አፃፃፍ ህጎችን አስቀድሞ ማስተማር

ለ. በመጀመሪያ ተማሪዎቹ እንዲፅፉ ማድረግ

ሐ. ተማሪዎቹ ራሳቸው ከፃፉት ድርሰት በመነሳት የድርሰት አፃፃፍ ህጎችን እንዲያወጡ ማድረግ

መ. በተማሩት ህግ መሰረት አንቀፅ ብሎም ድርሰት እንደፅፉ ማድረግ

ሠ. አስተዋፅኦ ነድፈው በነደፉት አስተዋፅኦ መሰረት እንዲፅፉ ማድረግ

11. ለቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት በተለይም ፅሀፈትን ለማዳበር የሚያስችሉ የተጓዳኝ ትምህርት እንቅስቃሴዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ይካሄዳሉን?

ሀ. ዘወትር ይካሄዳሉ　　ሐ. አልፎ አልፎ ይካሄዳሉ

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ይካሄዳሉ　　መ. ተካሂዶም አያውቁም

ሐ. በመጠኑ ይካሄዳሉ

12. ቋንቋውን በሚያስተምሩበት ጊዜ በፅሁፍ የሚመለስ የክፍል ወይም የቤት ስራ ሰጥተው ያውቃሉ?

ሀ. ዘወትር እሰጣለሁ ሐ. በመጠኑ እሰጣለሁ

ለ. አብዛኛውን ጊዜ እሰጣለሁ መ. አልፎ አልፎ እሰጣለሁ

ሠ. ከሁለት ወር ከሶስት ወር አንድ ጊዜ እሰጣለሁ

13. በተራ ቁጥር ‹12› ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ ሐ፣ መ፣ ሠ ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልዎታል?

ሀ. ፅህፈትን ማስተማር አስቸጋሪ በመሆኑ

ለ. ፅህፈትን ማስተማር ጠቀሜታው አነስተኛ በመሆኑ

ሐ. የተማሪዎቹ የመፃፍ ፍላጎት አነስተኛ በመሆኑ

መ. በፅሁፍ የሚመለስ ጥያቄ በመማሪያ መፃህፍ ውስጥ ስለማይዘጋጅ

ሠ. ፅህፈትን ለማለማመድ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ አነስተኛ በመሆኑ

14. ተማሪዎችዎ የሚሰጣቸውን የክፍልና የቤት ስራ ሰርተው ይመጣሉ?

ሀ. ዘወትር ይሰራሉ መ. አንዳንድ ጊዜ ይሰራሉ

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ይሰራሉ ሠ. በወር በሁለት ወር አንድ ጊዜ ይሰራሉ

ሐ. በመጠኑ ይሰራሉ

15. በተራ ቁጥር 14 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ ‹ሐ›፣ ‹መ› ወይም ‹ሠ› ከሆነ ምክንያቱ ምን ይስልዎታል?

ሀ. ተማሪዎቹ ት/ቱን ስለሚንቁ

ለ. የፅህፈት ስራ አስቸጋሪ በመሆኑ

ሐ. የፅህፈትን ጠቃሚነት ባለመረዳታቸው

መ. ተማሪዎቹ የመፃፍ ፍላጎት ስለሌላቸው

ሠ. በመማሪያ መፅሀፍ ለፅህፈት የሚመረጡት ርዕሶች የተማሪዎቹን ፍላጎቶች ባለመያዛቸው

16. በክፍልም ሆነ በቤት ስራ ተማሪዎቹ ድርሰት እነዲፅፉ የሚያደርጉት ምን ጊዜ ነው?

ሀ. በሳምንት አንድ ጊዜ መ. በየሶስት ወሩ

ለ. በየሁለት ሳምንት ሠ. በሴሚስተር አንድ ጊዜ

ሐ. በወር አንድ ጊዜ

17. ተማሪዎቹ ድርሰት እንዲፅፍ በሚደረግበት ጊዜ ርዕሱ በማን ይመረጣል?

ሀ. በመምህሩ ይመረጣል

ለ. በተማሪዎቹ ይመረጣል

ሐ. በመምህሩና በተማሪዎቹ ይመረጣል

መ. በመማሪያ መፅሀፉ ላይ የቀረበው ርዕስ ተግባራዊ ይሆናል

ሠ. ከላይ በተዘረዘሩት በሁሉም ይመረጣል

18. እንደየክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራ የሰጡትን መልመጃ አርመው ያውቃሉ

ሀ. ዘወትር አርማለሁ

ለ. አብዛኛውን ጊዜ አርማለሁ

ሐ. በመጠኑ አርማለሁ

መ. አንዳንድ ጊዜ አርማለሁ

ሠ. በወር አንድ ጊዜ አርማለሁ

19. በተራ ቁጥር 18 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ አርማለሁ የሚል ከሆነ እርማቱ በማን ይካሄዳል /መልሱ ከአንድ በላይ ሊሆን ይችላል?

ሀ. የመምህሩ ግለ እርማት

ለ. የቡድን እርማት

ሐ. የቢጤ እርማት

መ. የተማሪው ግለ እርማት

ሠ.የጥቂት ተማሪዎችን አስነብቦ ማለፍ

20. በተራ ቁጥር 18 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ ‹መ› ወይም ‹ሠ› ከሆነ ችግሩ ምን ይመስለዎታል?

ሀ. የተማሪዎቹ ቁጥር በርካታ በመሆኑ

ለ. የተማሪዎቹ መልመጃውን ሰርተው ስለማይመጡ

ሐ. የማረም ስራ አድካሚና አሰልቺ በመሆኑ

መ. በታረመው መሰረት ተማሪዎቹ ፅሀፈታቸውን ለማሻሻል ስለማይጥሩ

ሠ. በቂ ክፍለ ጊዜ ባለመሰጠቱ

21. እንደ የክፍልም ሆነ የቤት ስራ የመስጠትን የፅሀፈት መልመጃ በሚያርሙበት ጊዜ አብዛኞቹ ተማሪዎች ይበልጥ ስህተት የሚፈፅሙበት በየትኞቹ ላይ ነው/መልሱ ከአንድ በላይ ሊሆን ይችላል/

ሀ. ስርአተ ነጥብ ላይ

መ. የፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ላይ

ለ. የቃላት አገባብና አጠቃቀም ላይ ሠ.በመስተዋድድ አጠቃቀም ላይ

ሐ. የዐ.ነገር አመሰራረትና የአንቀጽ አፃፃፍ ላይ

22. ለተማሪዎቹ ስህተት መፈፀም ምክንያቱ ምን ይመስለዎታል?

ሀ. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ

ለ. የተማሪዎቹ ግዴለሽነት

ሐ. የሁለተኛ ቋንቋው ሰዋሰዋዊ ስርአት አስቸጋሪነት

መ. የመምህራን የአስተራረም ጉድለት

ሠ. የመርሃ ትምህርቱና መማሪያ መፅሀፉ ብቃት ማነስ

ረ. ተማሪዎቹ ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው አመለካከት

23. ተማሪዎቹ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሙትን ስህተቶች ከተማሪው ድክመት የመጡ ናቸው ብለው የሚገመቱ ከሆነ ድክመቱ ከምን የሚመጣ ይመስለዎታል?

ሀ. ከተማሪው ውስጣዊና ውጫዊ ችግር

ለ. የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ የተማሪውን ፍላጎ የማይስብ በመሆኑ

ሐ. የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ ለት/ቱ ያልተመቻቸ በመሆኑ

መ. የድርሰቱ ርዕስ የተማሪዎቹን ፍላጎትና ዕድሜ የማይመጥን በመሆኑ

ሠ. በድካምና በሰውነት መዛል በሚፈጠር ዝንጋታ

## መመሪያ ሁለት

ከዚህ በታች አምስት አማራጭ መመዘኛዎችን የያዙ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ አንድ ብቻ ሲሆን ከቀረቡት መልሶች መካከል ከሁሉም የበለጠ ተገቢ መልስ ነው ብለው የመረጡትን መመዘኛ በተሰጠው ባዶ ሳጥን ውስጥ የ ‹√› ምልክት ያስቀምጡ·

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መመዘኛዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| 1 | የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለቋንቋው ት/ት ያላቸው አወንታዊ አመለካከት ምን ያህል ነው | | | | | |
| 2 | የመማሪያ መፅሀፍ የመልመጃ ይዘት ፅህፈትን ለመለማመድ ያለው አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው | | | | | |
| 3 | እርስዎ ተማሪዎቹን ፅሁፈትን ለማለማመድ የሚሰጡት ጊዜ ምን ያህል በቂ ነው | | | | | |
| 4 | ለቋንቋው ት/ት የተፈቀደው ሳምንታዊ ክፍለ ጊዜ ፅህፈትን ለማለማመድ የሚኖረው አፍራሽ ተፅእኖ ምን የህል ነው ብለው ይገምታሉ | | | | | |
| 5 | ፅህፈትን ለመለማመድ ተማሪዎቹ በግልና በቡድን የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው | | | | | |
| 6 | እርስዎ ፅህፈትን ለማለማመድ የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው | | | | | |
| 7 | ተማሪዎቹ የፅህፈት ችሎታቸውን ለማሻሻል የተለያዩ ነገሮችን የማንበብ ልምዳቸው ምን ያህል ያዳበረ ነው | | | | | |
| 8 | በፅህፈት ልምምድ ላይ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚኖረው አፍራሽ ተፅዕኖ ምን ያህል ነው | | | | | |
| 9 | ተማሪዎቹ ድርሰት /ፅህፈት/ በሚለማመዱበት ጊዜ የሚፈፅሙት የስህተት መጠን ምን ያህል ነው | | | | | |

# ክፍል ሶስት

*መመሪያ*

በዚህ ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች የእርስዎን ነፃ አስተያየት የሚጠይቁ ናቸው ስለሆነም ከስራ ልምድዎ፣ በስራ ሂደት ካጋጠመዎ ተሞክሮና ከተመለከቱት በመነሳት ይሆናል ብለው የሰጡትንና የገመቱትን ሃሳብ እንዲሰጡ በአክብሮት ይጠየቃሉ?

1. በት/ቤቱ አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩት የኦሮሞኛ ቋንቋ አፍ ፈቺ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አወንታዊም ሆነ አሉታዊ አመለካከት ምን ይመስለዎታል?

   ...........................................................................................................

2. ለክፍሉ ደረጃ ተዘጋጅቶ የቀረበው መርሃ ትምህርትና የመማሪያ መፅሀፍ አዘገጃጀት የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎችን የፅህፈት ክሂል አለማዳር ያለው አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው ብለው ይገምታሉ?

   ...........................................................................................................

3. በክፍል ውስጥ የሚካሄደው የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎችን የፅህፈት ክሂል ለማዳበር የሚኖረውን አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዴት ይመለከቱታል?

   ...........................................................................................................

4. ሁለተኛ ቋንቋ አፈ ፈት ተማሪዎች በፅህፈት የሚመለስ እንደየክፍልም ሆነ የቤት ስራ ያለውን በአብዛኛው ሰርተው የሚመጡ ከሆነ ለመስራታቸው ምክንያቶች ናቸው ብለው የሚገምቷቸውን ቢገልጿቸው?

   ...........................................................................................................

5. እርስዎ የሚሰጡትን እነደየክፍልዎ ውስጥ ሆነ የቤት ስራ ያሉትን ተማሪዎቹ ሰርተው የማይመጡ ከሆነ በአብዛኛው ሰርተው የማይመጡ ተማሪዎች የትኞቹ ናቸው? ብለው ይገምታሉ? / የአማርኛ ቋንቋ አፍ ፈቺዎች ወይስ የኦሮሞኛ ቋንቋ አፍ ፈቺዎች ?/ ምክንያቱ ምን ይመስለዎታል?

   ...........................................................................................................

6. እንደ የቤት ስራም ሆነ የክፍል ስራ የሰጡትን የፅህፈት መልመጃ በሚያርሙት ጊዜ በአብዛኛው ስህተት የሚፈፅሙት ተማሪዎች የትኞቹ

ናቸው / አማርኛ ቋንቋ አፍ ፈቺዎች ወይስ የኦሮምኛ ቋንቋ አፍ ፈቺዎችና ሌላ /ለምን እንደሆነ ያለዎትን አስተያየት ቢገልፁ?

................................................................................................................................

7. ተማሪዎቹን ፅህፈት በሚያለማምዱበት ጊዜ የሚፈፅሙት የስህተት አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ ቢገልጿቸው?

................................................................................................................................

8. በፅህፈት ልምምዱ ወቅት በተደጋጋሚ የሚፈፀሙት የስህተት አይነቶች የትኞቹ ናቸው ብለው ይገምታሉ? ለምንስ የሆነ ይመስለዎታል?

................................................................................................................................

9. ተማሪዎችዎ ፅህፈትን በሚለማመዱበት ጊዜ ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጮች ይሆናሉ ብለው የሚገምቱትን ቢጠቅሱልን?

................................................................................................................................

10. በጥቅሉ የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎችን የፅህፈት ክሂል ለማዳበር ሊደረግ ይገባዋል ብለው የሚገምቱትንና የስህተት ምንጮች የሚሏቸውን ለማስወገድ የሚወሰደውን ርምጃ ቢገልጹልን?

................................................................................................................................

[illegible]

አበሀ
ለ

የትምህርት ጥቅም

የትምህርት ጥቅሞችን ተንገልፅም ኢገጨርሰም ግን የትምህርት ጥቅም
በጣም ብዙ ነው ቁጥ ገን ትምህርት በጣም አሰፈላጊ ነን
ጥቅም ነው ኢገም ሰው ሰውምር ሙንር ኢያስችለው
ኣሰተማሪነው ተማር ገኣሰተማሪ ፶ን በቁሚ የለተማር ናን
የሰማር ኢገዉ ሰመው ኣሞኾ የደርገል.
ኣዚ ገን ተማሪ ነን የለተማሪው ኢሰርዕተ ኢገብን
ኢገነው ንም ተማርትር ሰርተቺ የፀግኸንው ሰያማር
ኣፀዴገም ገን ኣዴው መኑማር ኣገብን

ትምህርት በጣው ኣስፈላጊ ነው ስ

ኢለም በው ግን የሰምሙር ኣስቀቀ ኣዋዜታ ስርቶቺ
ኢጹኙን በቾ ሰዩ ኣን ኣኅውቀትን ኢጹ ኣጹሰር ነዉ.
ኣ ትምህርትን ሙር ዋን ወደ ትምህርት ሰቶ
የሙንምዉ ኣዉቀት ኣንዳትቃዊ ነው.
ኢገለው ሰው ደገተርው፣ ኢሰተማሪ ነው. ተማር
ገው የኢንዲ በር የሙዋሚቃ
ኣዚ ግን ኡተምሮቺ ሰር ኣንደሚቺንሚቺ ዋንበርን
ሙሃሙግር ኣገብን ዋን ዓገ ተማርን ግን የኣንዲ
ኢገ መኸን ኣቅቶገም ግን ትምህርትን መማርዋ
ኣውቀትን መማሪዋ ነው.

3. የዐሯት ምትም   አዘር   እቶ፣ የሰነድ   ለተሮ ሙን
ሰ

የዐሯት ምትም ተገለፆ ተሹሞ በሠራተኞችን ያነተቃል እሷምሪቻችን ቀስበእንባል። እንደ ስራ ዐሯት ቃልቃ በዐ እሉ በዐስሩት ያሹተቀል
ዐሯት ጉጎት የስራም [illegible] ግን እሰሙ።
ዐሯት የወሪ ሾመ እሮ ክበበቀር በሰፈ በታመደ ሠሰሉ ሁቻናል።
ዐሯት የሞገሾወርበር እንዲለፋቻን እንዳንደ በበግ ሼሙ።
ለምሳሌ ፡ ዐሯት ክፈበረፉቻ ደ እሰበታታን
እስበበያገበሸበር እናቶ እንደፖ ቀን ናልቃምሹን ለቃቻ እለን ቀጸስለስናል።
እምለዘሀ ዐሯት ምትም እስራ ክቡ ጎሙ በሟምሰሙ።
ሰፊ በበልሱ እንደፖ ባስሌ ዐሯት ተሻስ ክሰቀለ
ስሁሩ ዐሯትን ቶርስ ቋቶግሩ
ሽዘያም የተሸጠር ዐሯት ለሠስረተሰበ ቀሽፋፋናል
እናም ግስሌተሰበ ያገን ዐሯት ለሰምሃት ሣጠቀምበተል።
(ቀሹሟኣል) ዐሯት የሰበረቐናል!
- የኢትዮጵያ ሰሁ በሀሁለ ሽሞ ግበ ቀርቻ
ለዐሯት የሰራ እሰበለያሽ
ለቀአቋሬ የሚሰዕለባሽ ሃም 100 - 90%

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

# የትምህርት ጥቅም

የትምህርት ጥቅም ብዙ ነው። [illegible] የትምህርት [illegible] ጥቅም [illegible] የትምህርት ጥቅም [illegible]

[illegible] የትምህርት [illegible]

[illegible]

[illegible] የትምህርት ጥቅም [illegible]

[illegible] ነው።

[illegible] የትምህርት ጥቅም [illegible]

[illegible]

[illegible] የትምህርት ጥቅም [illegible]

123

[illegible]

የወንጀሉ የአፈጻጸም ስልት ድርጊት ፈፃሚ

የወንጀሉ በአዲስ በሃገር ደረጃ የሚደርስ ስለሚያስከትሉት ጉዳቶች የወንጀሉ ከባድነት አንፃር ስለሚፈጸመው ወንጀል

የወንጀሉ በአጠቃላይ የወንጀሉ ከህብረተሰቡ ጋር ያለው ትስስር የህብረተሰቡ የሀገሪቱ

ሰላም የወንጀሉ ተጠቂዎች ከወንጀሉ ጋር ያላቸው የወንጀሉ ስልት ድርጊት ፈፃሚ

ሰላም ከህብረተሰቡ ተጋላጭ ነው

ይህ ሰላማዊ ሰዎች ሰላም ከማጣት ባለፈ ሁለት ወገኖች ያሉ ሲሆን የሚገልጹት የወንጀሉ የፀጥታ ሁኔታ

ሁኔታ ያለው የሚያስከትለው የሰላም ስጋት ያለበት ሁኔታ የመከላከል ሃገራዊ

ሊሆን ይገባል ሁኔታ ያለው ሰላማዊ ሰዎች ሰላም ከማጣት ባለፈ ሆኖ

ቤት ለቤት የሚደረገው ፍለጋ አዲስ የወንጀለኞች ፍለጋ ተጠናክሮ

መንግስት ~~በህዝቡ~~ ገንዘብ ተጠቃሚነት ከህዝቡ ጋር ሰላማዊ ሁኔታ መጠበቅ

ለዚህ መፍትሄ የተመለከተው ሀገር ሊያጋጥመው የሚችል ሁኔታ ላይ መንግስት ደህንነቱን

(ሰላም) መጠበቅ ነው ይህ የመንግስት ሃላፊነት ነው!!

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible] (Dubious) [illegible]

[illegible]

# የወባ በሽታ

የወባ በሽታ፡ ማለት አንድ የሚያስተላልፍ በሽታ፡ የአንድ ሴት ወባ ትንኝ በመንከስ የሚያስተላልፈው ነው።
በሰውነታችን ውስጥ ባሉት በሽታዎች መካከል የወባ በሽታ ነው።

በበጋ ወቅቶች, በዝናብ ጊዜ ውሃ ያቆረባቸው ቦታዎች የሚራባበት ናቸው።

የወባ በሽታ ምልክቶች ብርድ ብርድ ማለት
ከፍተኛ ትኩሳት በሰውነት ውስጥ በመሰራጨት ማንቀጥቀጥ።

- የወባ በሽታ የሚያጋጥመው ጊዜ
  ከፍተኛ ራስ ምታት ነው
  ውሃ ጥም ራስ ምታት ነው

## የሚተላለፍበትና መከላከያ መንገዶች

- የወባ በሽታ የሚተላለፍበት መንገድ ሴት ወባ ትንኝ ናት። ስለዚህ ውሃ ያቆረባቸውን
- የወባ በሽታ የሚከላከለው ... ቦታዎች ውሃ በማፋሰስ መድፈን።
- ... ውሃ ማቆር የለበትም።
- የወባ ትንኝ ለማጥፋት መድኃኒት
- የወባ ትንኝ ... የሚያስከትል ...
- ... ውሃ ማፋሰስ።
- ... ...
- ... በመድኃኒት ...
- ... የሚያስከትሉ ... ማድረግ።

የትምህርት ዓላማ   ኢሬ የቁሳ ህብት ቋንቋ ኢዮፔ

ትምህርት ከአንዱ ሰው ወደ የሚተላለፍ ለሌላ ለሆነ ለአንዱ የሰው እውቀት ነው እንደዚህ
ተፈጥሮት ለሆነ እንዲ ሰው ትምህርት አይታወቅ የለው እንዲህ ገብቶ የሚገባውን ሆኖ
ከሆነ ፋይዳ ያሆነ ለአንዱ ትምህርትን እንደአለ ሰው እንደሆነ በአለ የሚወስ
በሀገራዊ እውነት ነው ማለትም እንዲ ሰው ከምሥክ ያሆነ ገባሽ ለሆነ እንዲህ
ሀገሩ ቀለበ ህብተም ለሆነ ከሀገር ፋይዳ ዘመርት በላን ከሙተ የሚፋጀው ከመሪ
ከሀገር የሚፋጅ ሀገሩ ወደ ሀገራዊ እውነት ነው:: እርስን ሥልተ ጠቃሚነት ከሀገር
ፋይዳ ዳሩ በሆን [illegible] ትምህርትን ላይ ትም ለበዘ መወገድ ከገሀራ ፋይዳ ከምሥክ ያሆነ
ሰቋንም ነገሮት : ለሰው ጋር ከመሰረጥ ቋንቋትን ከመደበር የሃገወት ገፋታን
ፈ.ተሰቦ ~~እንደሆነ~~ እንደሆነም - እንዲ ሰው ትምህርት ለተወለ እንዲያመን ሁሉ
ዓለ መስጠት ፋይዳ መካከል ተሰው ሰዎ ህይወ እንዲ የተሰየ ነው ለሀገሩ ዘዘ
አገልግ ዋና ነው ም ሂደት ከሆነ የሚያሰው ትምህርት ለእውነር ነቻ ነው
ትምህርት በሰው ሰዎ ሀተወት ሰላም ተለቅ ሆኖና ፋይዳ ማለትም ለትምህር
እንደ ኑቱ ያለ ሰዎና የለበ ሰው እንዲ እንዲሆን እንደ ተገበለ እንደሆነ
ብ ወለል ፋይዳ ፡ ትምህርት የሚያሰው ሰው ሰምም ያለው አይደለ ያለው
እንዲ እንደ ለትምህርት እንዴ ኑቱ እንደዚ ዘዘ ለተሰማ ፋይዳ ለተወደ እንዲህ
ሠራ ጉልበ እንደ ሁሉ ወሰብሰ ሰብ ተግሌ ለሆነም ከሆነ ፋይዳ
ያለውም ሰው ሁሉ የሆነ ዘሆነ አለ [illegible] ያለሆነ ሰው ለዘዘ
ነገሮች ከሚሆን ፋይዳ ተተያለው ለን ጋለት እንዲሆን ከያጠ ያሆ ዝር ለለ
እያማም ለዘ ለእንተዘር ፋይዳ ያለሆነ ሰው [illegible] ለዘዘ አፋፋችግር እሱ
ከጤና ፋይዳ ከምሥክ ያሆነ መሆኑም? ጸዘገ ፀሐይ እየተሰከ የሆኑሙሁን
ያለም ለከ ፋይን ሁሉ የሆኑሰው ፋይዳ ያለሆነ ህዝቡ ነገ ነው
የተጠያቂነት ነው እንዲህም [illegible] ጎሬጋዎቹ ነገ የሙሮት እንደ ቀኝዉ
እንዲህ ነገሩ ማለት ነው ሰሁዘ የትምህርት ጓደኛ ተገልፆ እያለቀም ሚኒተው
ትምህርት ወዳጁ ሰላም ከዘዘ ገር የጣቀልብ እንዲሁን ወገ ከመም ተን
የቢተለገን ህብረተ ከወደንም ሰላ ሰሁ ነቀ ከመለሆኑት እንዲሆንና ከዋ
ሁኔ ወሲ.ተ ሀና ሰሁዘ የትምህርት ኃላፊ ገዘ ዝሆን መሆኑ
ሆነ ወደ ዕማ የሮ የሀገም እንዲ ገር ቀ ሀሳ እንደሆን
ሙ እዲርት ከመሮ ለገኝ

[illegible]

[illegible]

[illegible]